# ፫

# "ያቺ ቀን ደረሰች!"

ጥበቡ ኃይለሥላሴ የእግዚአብሔር ሰው እንደመሆኑ መጠን የምድር ዘመኑ እየተጠቃለለ እንደሆነ የገባው ሰው ነበረ። እኔን የሚገባኝ ግን አሁን ነው፤ መለስ ብዬ ሳስበው። ኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሞት በኢየሩሳሌም እንደሚጠብቀው እያወቀ የሚገሰግሰው ግን ወደዚያ ነበር። 'አምላኩን መሳዩ' የኔ ጥበቡም የምድር ጉዳዩን ለማጠናቀቅ የሚገሰግስ ሰው ነበር። የእግዚአብሔርን ቤትና አገልጋዮችን በሚመለከት፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ለልባችን ተናግሮን ለጌታ የለየነው ማንኛውም ነገር ባስቸኳይ ከእጃችን እንዲወጣና ወደ የስፍራው እንዲደርስ.. የውዴ ልብ ይጣደፋል! ተሳክቶም ሲያየው በልቡ የሚፈጠረውን እፎይታ ሳይ እኔም አብሬው "እፎይ!" እላለሁ። እግዚአብሔር በልቡ ሞልቶ ያትረፈረፈለትን ፍቅር ለቤተሰብ ለእህት ለወንድሞች በሚችለው ሁሉ በመግለጥ፤ እንደቤተሰብ መቀጠል ስላለበት ጉዳይ ፈር ለማስያዝ ራዕዩንና ኃላፊነቱን ወደኔና ወደ ልጆቹ ለማስተላለፍ..

ሌላም የቀረው አሳብ አለው፣ አምላኩ እግዚአብሔር እንዲያደርግለት የተመኘው። እሱ በሌለበት እኔ ግራ እንዳይገባኝ ራሴን የማስጠልልበት አድራሻ እንዳላጣ፤ ልጆቻችንም አገር ሲገቡ



ምስጋናና አምልኮ ጌታ በሠራልን ቤት

የሚሰባሰቡበት እንዳያጡ ጥበቡ ባሰቸኳይና በጥራት እንዲሰራ የሚፈልገው መኖሪያ ቤት ነው፤ እናም እሱ በአካል ተገኝቶ ሊያሰራው ባልቻለበትና በትልቅ የጤንነት ግብግብ ላይ በነበርንበት ወቅት ይሄን ሃሳቡን የሚያስፈጽምለትን ሰው እግዚአብሔር አስነሳ፤ ታላቅ ወንድሜ ገብሩን። ያልነበረውን ጤንነትና ጉልበት ማስተዋልንም እግዚአብሔር ሰጥቶት! በሁለት የተለያዩ ወቅቶች የእኛን ቤት ሊሰራ በተነሳበት ጊዜ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎታል። "ይሄ አገልግሎት ነው"፤ ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ፡- "እሮጌ መዝገብ ከምታገላብጥ ይሄን አገልግሎት አድርጌ ሰጥቼሃለሁ"፤ ሲል የእግዚአብሔር ድምጽ እንደገና ወደ ወንድሜ መጥቶለት ነበር። ስለዚህኛው የእግዚአብሔር ድምጽ የተረዳውን ወንድሜ ሲናገር፡-

"ባንድ በኩል ከሂሳብ ኦዲተርነት ሥራዬ ጋር በተያያዘ መልክ ዓይቼዋለሁ። ያው የቆዩ የሂሳብ መዝግብት ስለማገላብጥ። በሌላ በኩል ደግሞ ከአእምሮዬ 'አሮጌ ፋይል' እያወጣሁ ዘመኔን እንዳላሳልፍ ማለቱም ይመስለኛል፤ ይሄን ከጌታ ከሰማሁ ወዲያ እውነትም ልክ እንደአገልግሎት ቆጥሬው ነበር የምሰራው። ቤቱ በጥራትና በፍጥነት እንዲያልቅም የተጋሁት።"

ውዴ ጥበቡም የዚህን ቤት ፍጻሜ ለማየት ውስጡ ይጣደፋል! አስፈላጊና ወሳኝ በሆኑ ወቅቶች ሁሉ ወደአገር ቤት መምጣት አምላኩ እያስቻለው። በልቡ ያሰበውን ለቤቱ ሥራ ምርጥ ዕቃዎችን በመምረጥ... ቤቱን ለማስዋብ የኔን ምርጫና ከለር ሳይቀር በማክበር፡- "ሁሉ እሷ እንደምትወደው ይሁን" ሲል፤ እኔ አልገባኝም ነበር። ሥራው እንዲቻኮል ሲያደርግ፣ ሁሉ አልቆና አምሮ ባየ ጊዜ የወስጥና የውጭ መብራቶችን ሁሉ አስበርቶ እያየ የተሰማውን ደስታ አምላኩን በማክበርና በማመስገን ሲገልጽ፤ እኔ ገና አልገባኝም! ወንድሜን ገብሩን እየባረከ እግዚአብሔርን ደግሞ ደጋግሞ ፡ - "እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ! እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ! ያቺ ቀን ደረሰች! ያቺ ቀን ደረሰች!" እያለ በመንፈሱ ሃሴት ሲያደርግ... እኔ ግን አሁንም አልገባኝም። ምናልባት ጥበቡ የገባው እንዲገባኝ ውስጤ አልፈለገም ይሆን?!

በደህናው ቀን ያኔ ድሮ እግዚአብሔር የኔንና የጥበቡን ትዳር በገመደበት ምንጊዜም ሊላላና ሊበጠስ በማይችለው ፍቅራችን ውስጥ እያለን፤ ዐይኖቹ በእንባ እያቀረሩ እንዲህ ያለኝን አስታወስኩ! የዛሬ ሃያ ዓመት ገደማ፡- "ማሚዬ! መቼም በምድር ላይ ለዘላለም አንኖርም፤ በየተራችን ወደ እግዚአብሔር እንሄዳለን። አንቺ ሄደሽ ግን እኔን እዚህ ዓለም ብቻዬን እንዳይተወኝ፤ እንድቀድምሽ አምላኬን ለምኜዋለሁ"፤ ሲለኝ ደነገጥኩ፤ በአባባሉና በውስጡም በማነበው እውነተኛ ስሜት። ምን ማለቱ ነው? አልኩ።

ለራሴም ኑሮን ያለ ጥበቡ ብቻዬን ስለመኖር ላፍታ ያህል እንኳ ላለማሰብ ውስጤን ከለከልኩት። "ለምን እንዲህ ያለ አሳብ ታስባለህ ዳድ! አብሮ ማለፍም፣ ባየር ተንጥቆም ጌታንና መላእክቱንም መገናኘትም እኮ አለ፤ እኔስ ያን ያርግልን እላለሁ! አንተ በሌለህበት ዓለም ራሴን ማሰብ አልችልም ዳድ!" አልኩት። ነገሩን አሁን ደፍሬ አነሳሁት እንጂ ይ አባባሉ ዳግም በሃሳቤ ቃጭሉን ላያሰማ አእምሮዬ ጥግ በጫጭቁ ቀብሬው ነበረ። ያኔውኑ ነበር ከራሴ ጋር ቃል የገባሁት የዚህን አሳብ ትዝታ ደብዛውን ለማጥፋት። ስለዚህም እስከ መጨረሻ ድረስ የማስበውም ሆነ የምናገረው ስለጥበቡ መኖርና ገና በምድር ላይ ስለሚቀረው አገልግሎት ነው። አምስት ዓመት በፈጀው በዚህ የጤንነት ተግዳሮትም ለራሱ ለጥበቡ እንኳ የምናገረው እንደ ልማዳችን ልብ ለልብ፣ እጅ ለእጅ ተያይዘን ስለምንሮጠው የእምነት ሩጫ ነበር። "ከሞት ጋር አትስማማ" እያልኩ ማወጀም እንዲሁ።

ከነጣቂዎች ነጥቆ ግሩምና ድንቅ አድርጎ እግዚአብሔር የሠራልንን ቤት መደምደሚያ

ለመከታተልና እቃዎቻችንንም ቦታ ቦታ ለማስያዝ ወደ አገራችን ኖቬምበር 2011 ውስጥ መጣን። ሁሉ ከተስተካከለ በኋላ በቤቱ መኖር የጀመረነው ከወገኖች ጋራ እግዚአብሔርን በማመስገንና ለስሙ ክብርን በመስጠት ነበር። በዚያ የምስጋና መስዋዕት ለአምላካችን አቀረብን። አብረውን በጾም በጸሎት ከጎናችን የቆሙ የጸሎት አገልጋዮች በኮንትራት አውቶቡስ እየሞሉ መጥተው ክብር የሚገባውን እግዚአብሔር አብረን አከበርነው! የዚህን ቤት ውብ ፍጻሜ ለባሪያው እንደምኞቱ ስላሳየው፤ ይህ እግዚአብሔር የሠራው ቤት የራሱ መገልገያ እንዲሆን… በየእሁድና ቅዳሜው የቤት ክርስቲያን መሪዎችንና የተለያዩ አገልጋዮችን በመጥራት 'ክበር!' አልነው እግዚአብሔርን። ልጆቻችንም እግዚአብሔር የሰራልንን ቤት ዓይተው ለማመስገን ከአሜሪካ መጡ። ጥበቡ በወጣትነቱ ገና ተማሪ ሳለ ጀምሮ የሚከራየው ቤት ትዝ ይለኛል። ምንም ያህል ያማረና ጥሩ ክፍሎች ያሉት ቤት ይሁን፣ ወይንም ምንም ያህል ጎስቋላና ጠባብ ባለሰሌን ምንጣፍ ይሁን፣ ጥበቡ ቤቱን ሲያደራጅ አግዳሚ ወንበር ያለበት የጸሎት ክፍል ማዘጋጀቱ ግን አይቀሬ ነበር። ዛሬም በዚህ ውብ ቤት፣ በውስጡ ካሉት ክፍሎች መሀል የከበረና በጥራት የተሰራ፣ ለጸሎትና ለአገልግሎት የሰየው ልዩ ክፍል አምሮ ተዘጋጅቷል። ጥበቡ እግዚአብሔር ባደረገው ነገር ሁሉ አምላኩን አከበረ ደስም አለው።

እኔም ይህ እግዚአብሔር የሰራልን ቤት ነው፤ አገራችን ገብተን ከዚህ የእግዚአብሔር ሰው፣ ከ37 ዓመት ጓደኔ፣ ከውዴ ከጥበቡ ጋር አምላካችንን እያመለክን የምንኖርበት ቤት ነው ብዬ አሰብኩ። ሰልፍ ከተከፈተብን ጊዜ አንስቶ ከሰይጣንና ከከፋት ሰራዊቱ ጋር አምስት ዓመት የፈጀ ጦርነት ላይ ሳለን፣ እኛ በሌለንበት እግዚአብሔር ለኛ የሰራው ይህ ቤት… በዘመኑ ሁሉ ለሰው እንጂ ለራሱ ያልኖረው ጥበቡ፣ ከትግሉ ሜዳ በድል ወጥቶ እፎይ የሚልበት እንደሚሆን ገመትኩ። ለትዳራችንና ለሕይወታችን ጌታ የመጨረሻ ዘመን አገልግሎታችንን የምናበረክትበት ቤት ነው ብዬም አሰብኩ።

እንደገናም ከዓመታት በፊት ያኔ ድሮ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሳለ እግዚአብሔር የተናገረውን አሰብኩ። ትዳር ከጀመርንበት ጊዜ አንስቶም በልባችን እየሞላ የመጣውን። አዎን! ልጆቻችን ከድሮ ጀምሮ ሲሰሙና አብረውንም ሲጸልዩ የኖሩትን "የቤተሰብ ራዕይ" ለእግዚአብሔር ክብር በሥራ የምንተገብርበት ቤት ነው አልኩ! በዚህ ቤት ጣሪያ ስር ሆነን እግዚአብሔርን እያመለክነው ጥቂት ቀናት አሳለፍን።

****

*ያለፉ ብዙ ሞቶች!*

ጃንዋሪ 31 2012። ሌሊቱን በውስጤ ሲመላለስ ከነበረው ሐሳብ ጋራ ነው በዚህ ጠዋት የነቃሁት። በድንገት የእግዚአብሔር መንፈስ ጥበቡን ይዤው ወደ አሜሪካ መብረር እንዳለብኝ በልቤ ጠንከር ብሎ አሳሰበኝ። ሌሊቱን እየነቃሁ ይሄ ሐሳብ በተደጋጋሚ አእምሮዬን ሲያቆራርጥ ዓይቼዋለሁ። መሄዱንማ እንሄዳለን፤ ለፌብሩዋሪ 18 ቀን የሐኪም ቀጠሮ ስላለን ወደፊት። ወደ አሜሪካ ለመጓዝ ሉፍታንዛ ትኬት ቢሮ ተመዝግበናል። ግን ዛሬ ጠዋት ከመኝታችን ስንነቃ ያ ሌሊት ላይ ድንገት በውስጤ ብቅ ብቅ ይል የነበረው ሐሳብ አሁንም በልቤ ውስጥ አብሮኝ ነቅቷል። ትንሽም ጥበቡን ዳሰስ ሳደርገው ሰውነቱ ሞቅ ይላል። አብረውን የከረሙት ልጆቻችን እምነትና ባለቤትዋ ዮናስ ከነልጆቻቸው ወደ አሜሪካ የሚመለሱት ያን ዕለት ማታ ነው። እግዚአብሔር ያገራበተን ወገኖቻችን ዶ/ር ንጋትና ዶ/ር ቶሉ አሉ። ልጆቻችንን ልትሰናበት ዶ/ር ንጋት በጠዋት መጥታ ኖሮ

ሰላም ልትለን እኔና ጥበቡ ወደነበርንበት መኝታ ክፍላችን ገባችና ተሳሳምን። "ዶክተር ሰውነትህ ትንሽ ሞቅ አለ እንዴ?!" አለች። በልቤ የተቀመጠውን አሳብ እንደገና ቀሰቀሰው አባባሏ። "እኔም መስሎኛል፤ እስቲ የሙቀት መለኪያ ቴርሞሜትሩን ላምጣ"።

ሙቀት መለኪያው ጥበቡ በእርግጥ ትኩሳት እንዳለው አረጋገጠ። እኔም ከሌሊት ጀምሮ በውስጤ ሲመላለስ ያደረው አሳብ ከእግዚአብሔር እንደሆነ አረጋገጥኩ። "በቃ! ዛሬ ተነስተን ወደ አሜሪካ መሄድ አለብን! እንዲያውም ልጆቻችንም የሚጓዙበት ቀን ነው አብረን እንሄዳለን" አልኩ። ጥበቡ ይሄ ድንገተኛ አሳብ ምንም ሳንዘጋጅ የራሴ አሳብ መሰለው። በሥርዓት ተረጋግተን ለመሄድ የፌብሩዋሪ ቡኪንግ እያለን። "ማሚ ደግሞ ቶሎ ድንግጥ ትያለሽ! እኔ እኮ ደህና ነኝ፤ የሚያጣድፍ ምንም የለም። ትኬቱስ ባንድ ቀን እንዲህ ይገኛል እንዴ?!"
አልፎ አልፎ እንዲህ መርቶኝ ዓይቼዋለሁና አምላኬን፦ "አይዞህ ዳዲዬ ብንሄድ ይሻላል! የምንሄደው እኮ ትኬቱ ከተገኘ ነው ገና። የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑንም የማወቂያ መንገድ ይሆነናል!"

የሚጣደፈው ልቤ የሉፍታንዛ ትኬት ቢሮ እስኪከፈት መጠበቅ አልቻለም! እዚያ የምትሠራውን እህት ለማግኘት የሞባይል ስልኳን ዕረፍት ነሳሁት! አስቸኳይ ነገር እንደሆነ ብላ ሞባይሏን አነሳችልኝ!

"እየነዳሁ ስለሆነ ነው ያላነሳሁት! ምነው እህት ሊሻን?"

"የፌብሩዋሪውን ቡኪንግ እርሺው! ዛሬውኑ የምንጓዝበት ትኬት ካገኘሽልን ወደአሜሪካ መብረር እንፈልጋለን!"

"ምነው ዶክተር ደህና አይደሉም እንዴ?! እንዲህ በጥድፊያ ዛሬ የምትሄዱት?"

"አይ! ደህና ነው! ደህና ነው! ልጆቻችን ዛሬ ስለሚሄዱ አብረናቸው ብንሄድ መልካም ይሆናል ብዬ ነው"

ከጥቂት ቆይታ በኋላ ያቺ እህት ደወለች።

"ኢኮኖሚው ክላስ ሞልቷል። በተጠባባቂነት የተመዘገቡ ሰባት ሰዎች አሉ"

"ኢኮኖሚው ለሱም አይመቸውም! ቢዝነስ ክላስስ??"

"ቆይ እንግዲያው እሱን ደግሞ አጣርቼ ልደውልልሽ"

በቢዝነስ ክላስ የምንጓዝበት ሁለት ቦታ ተገኘልን! ይሄን ድንገተኛ ውሳኔዬን ልጆቻችን ሲሰሙ ደስ አላቸው! በሩቅ ሆነው ከሚያስቡ ሊለዩት የማይወዱት አባታቸውን ይዤ ወደ አሜሪካ በመመለሴ። ጥበቡ ድንገተኛው ሃሳቤ ከእምነት ሳይሆን ከፍርሃት እንዳይሆን ጥቂት አሰበ፤ የትኬቱ መገኘት እንደምልክት ሆኖለት አረጋጋው እንጂ። ያ ጠዋት ብቅ ብሎ የነበረውም ትኩሳት ቀኑን ሙሉ ሳይመለስ ቀረ። ይህን ያልታቀደ መንገድ እግዚአብሔር እንዲያ አቀናጅቶት አውሮፕላን ውስጥ ስፍራችንን ያዝን። የቀረበው ሙብልና መጠጥ ሁሉ ተስማምቶት በምቾትና በደህና ዴንቨር ኮሎራዶ ገባን። አሜሪካ በገባን በሁለተኛው ቀን ግን ጥበቡ ትኩሳትና ጠንከር ያለ ሕመም ይሰማው ጀመር። ሐኪሞቹ ባደረጉት ምርመራ መሠረት ጥበቡ ባስቸኳይ ሆስፒታል መተኛት ነበረበት! የድንገተኛው ጉዞ ምሥጢር ያኔ ነው የገባን! ልጆቹን ስለሚመራው የእግዚአብሔር መንፈስ ስሙ የተባረከ ይሁን።

የገጠመን የጤና ተግዳሮት እንደ እውነቱና ሐኪሞች ገና ከጅማሬው እንደተናገሩት ቢሆን ኖሮ ጥበቡ በሥጋ ሞት ከኛ መለየት የነበረበት ካናዳ የዛሬ አምስት ዓመት በዚያ አስጨናቂ ሌሊት ነበር። አምላካችን ' ይህ አይሆንልኝም አታደርገውም! ' ሲል ያን የሞት መልአክ ከለከለ። ሌሎችም

ሞት ያጠላባቸው ሊሊቶች ትዝ ይሉኛል። ቶሮንቶ ማውንት ሳይናይ ሆስፒታል ብቻ ሦስት የሞት ቀጠሮዎች በጸሎት ኃይል መሰበራቸውን አስታውሳለሁ። በተለይ የአንደኛው ምሽት ይገርመኛል። ተረኛ አዳሪ የነበረች አንድ ሐኪም ጥበቡ፡- "የተነሳው ኤክስሬይ አየር ከዳያፍራሙ በታች ያሳያል። በአስቸኳይ ኦፕራሲዮን መደረግ ሳይኖርበት አይቀርም" እያለች መሯሯጥ ጀመረች።

እርግጠኛ ለመሆን ለተጨማሪ የኤክስሬይ ምርመራ ስትልከው እኔም ለአስቸኳይ የጸሎት እርዳታ በየቦታው ደወልኩ። አንዱ የደወልኩት ኦሬገን ወደሚገኙት ወገኖቻችን ወደእነወይኒና እስገድ ሙላት ቦሲና ፍሰሐ ጉርሜሳ ነበር። በዚያን ምሽት የአንድነት የአዳር ጸሎት እንደነበራቸው እኔ አላወቅሁም፤ሁለቱም ቤት ብደውል ስልካቸውን ስለማያነሱ መልእክቴን በዝርዝር ተውኩላቸው። ኋላ የነገሩኝ እጅግ የሚደንቅ ነበረ። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምሥጢራትን ገልጾላቸው ከእኔ ላይሰሙ ይጸለዩ ኖሯል። "እግዚአብሔር አምላክ የሞት መንፈስን እንዲመታ ጸልዩ! የሞት መንፈስ ነው። ኦፕራሲዮን እያለ ወደያ ወዲህ ይሯሯጣል! እሰሩት ይህን መንፈስ!" - የእግዚአብሔር መንፈስ በሰጣቸው ምሪት ያን ክፉ ነፍሰ ገዳይ መንፈስ አስረው ጸሎታቸውን ከጨረሱ ወዲያ የተውኩላቸው መልእክት አስገርሟቸው ደወሉልኝ። እግዚአብሔር አምላክ ሥራችንን እንዴት እንደሠራልንና ዲያብሎስ አቅዶት ከነበረው አንድ ሌላ ሞት ባሪያውን እንደታደገልን አስተዋልን።

ከዚያም በኋላ በተመሳሳይ ሁኔታ የመጣውን ብዙ ብዙ ሞት እያሳለፈ አምስት ዓመት አስቆጥሮናል። አምላካችን ከሞትም ያድናል! እርሱ ብቻውን ተአምር አድራጊ ነው። አምላካችን ፈዋሽ ነው! ኢየሱስ ጌታ ነው! እነዚህና ሌሎች ሌሎችም የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት የሚያውጁት የወንጌል እውነቶችና አዋጆች ዛሬም በውስጤ ይሰተጋባሉ! አምላካችን በእኔና በጥበቡ ሕይወት በሀይነት በዐይነቱ አሳይቶናልና።

እናም የሂን እውነት ይዘን 'አውቀን ጨርሰናል' የሚሉንን ሐኪሞች ተቋቁመናል። ከእርሱ ዕውቀት ያለፈ ዕውቀት 'እግዚአብሔር' የሚባል እንዳለ እንዲያውቁም እግዚአብሔር በእኛ እንዳደረገ እነሱም ራሳቸው ምስክሮች ሆነዋል። መኖሪያቸው አንጀት እንጂ ደም ውስጥ ሲገኙ አደገኞች የሆኑ ባክቴርያዎች፣ የሰው ስህተት በሸነቆረው የጥበቡ አንጀት ውስጥ ያለከልካይ መውጪያ መንገድ ቢያገኙም ጥበቡን መርዘው ያለጊዜው ሊገድሉት አለመቻላቸው ድንቅ ነው። ከሁለት ዓመት በፊት ሐኪሞች ከትልቁ አንጀት ወደታች መጨረሻ ላይ በምርመራ የደረሱበት የካንሰር እጢ በውነቱ ውስጥ ተሰፋፍቶ ጥበቡ በዚያ አለመሞቱ ተአምር ነው።

የእስካሁኑ ተግዳሮት ሳያንሰው ለሦስት ሳምንት የገጠመው የአንጀት መቆላለፍ መፈታታትስ! የምንጠባበቀው ጌታ ድንገት መጥቶ ያደረገልን ተአምር! የሩቅ ታሪክ አይደለም እኮ! የጥበቡ ሕይወት በዚያም አለማለፉም ሌላው ተአምር ነው! በዚህ ሁሉ ላይ በእነዚህ አምስት ዓመታት ጥበቡ የተጎናጸፈው ጸጋ፣ በፊቱ ገጽታ የሚታየው አስገራሚ ፈገግታና ብርሃን፣ የሚያሳየው ትዕግስት የተሞላው እምነትና ተስፋ...ፍጹም ምድራዊ አለመሆኑ... ራሱን የቻለ አስገራሚ ተአምር ነው!

ሌላው የሚገርመውና የሚገርመኝ በእኔ በደካማዋ ውስጥ እግዚአብሔር ያኖረው ብርታትና ጸጋ ነው። ሐኪሞቹም ይደነቃሉ ስለማስረዳት ችሎታዬ (በተለይ ጥበቡ መናገር ሲያቅተው ወይንም እንቅልፍ ላይ ሲሆን) እነሱ የሚጠቀሙባቸውን ቃላት ስለምናገር፤ ሳይንቲፊክ መልስ ስለሚያስፈልጓቸው ጥያቄዎቼ! እኔም እንደጥበቡ ሕክምና የተማርኩ ሰው እስከመስላቸው፤ እርግጠኛም ሆነው እስኪጠይቁኝ። ከሐኪም ቤት ውጭ እቤት ስንሆን ሌትና ቀን የሚያስፈልገውን

ጥንቃቄ በትጋትና በፍቅር ለመፈጸም መቻሌ። በተለይ ሆስፒታል መግባት በሚኖርበት ጊዜ ሁሉ የሚያጋጥሙን ተቀባይ ሐኪሞችና የየጊዜው 'ፕራይሜሪ ቲም' የሚባሉት ባብዛኛው አዳዲስ ስለሚሆኑ ከሕመምተኛው መስማት ይፈልጋሉ።

በወቅቱ እየተሰማው ስላለው ሕመም መነሻም ሆነ አድራሻ . . ስለሚወስዳቸው የመድኃኒት ዐይነቶች. . ዝርዝር ኢንፎርሜሽን ያላንዳች ችግር ከኔ ይሰማሉ! እሱም መናገር ሲደክመው፣ "እሷን ስሟት ከእኔ የበለጠ ስለኔ ትነግራችኋለች" ይላቸዋል። ረዘም ላለ ጊዜም የሚያውቁን ሐኪሞች ደግሞ፡- "ለሚስትህ ቢያንስ የክብር ዶክትሬት መስጠት ይኖርብናል" ይሉታል። ሌሎች ደግሞ "አንተ አንድ የታደልክ ሰው ነህ! ያንተን ጭንቅላት/አእምሮ ሆና የምታስብልህ ሚስት አለችህ" በማለት ሲናገሩ እሱም በኩራትና ያለበጣ፡- "She is my better half; listen to her" (ግማሽ አካሌ ነች፣ እሷን ስሟት - እንደማለት ነው) ሲላቸው እኔ ደግሞ ሳስረዳ እሱ አዳማጭ ይሆናል።

ሐኪሞቹ ሰፊ ጊዜ ወስደው ከእኔ ጋር ይነጋገራሉ፤ ለጥያቄዎቼ መልስ መስጠት አስተያየቴን በአንክሮ ማዳመጥ ይወዳሉ፤ ስለሚያስቡት የተለያየ ፕሮሲጀርና ካደረጉለትም በኋላ ዝርዝር ግኝታቸውንም ሆነ የሰሩትን ሥራ የሚገልጹልኝ በአክብሮት ነው። የሐኪሞች ግምገማ ትክክል ካልመሰለኝና ካላረካኝ አንዳንዴም ተሰፋ ቆርጠን እጅ እግራችን አጣምረን የጥበቡን ሞት እንድንጠባበቅ ሲነግሩኝ ከሚመጡ ጋር ሙግት እገጥማለሁ።

ጁላይ አጋማሹ ላይ ነው 2011። ሊነጋጋ ሲል ጥበቡ ከወትሮው ለየት ያለ ሕመም ሆዱን ስለተሰማው እጆቼን ጭኜ በመጸለይ ላይ ነኝ። ሁሌም ባጠገባችን ሆኖ የሚያበረታን እግዚአብሔር እንደሚሰማን ስለምናምን መልሳችን ቅጽበታዊ ይሁን አይሁን እኛ ግን ነገራችንን ለአምላካችን እንነግረዋለን። አንዳንዴ ዳዲ እስኪገርመው የጸሎት መልሳችን ፈጣን ይሆናል፣ ከትግሉ ሜዳ እኔም እሱም አረፍ እንላለን። ሁሌ እደነቃለሁ በእግዚአብሔር ምሕረት! ፋታ ሲያገኝ የሚተኛው እንቅልፍ በእጅጉ ያጽናናኛል።

ዛሬ ግን ለየትና ጠንከርም ብሏልና አምቡላንስ ጠርተን ሆስፒታል መሄድ የማይቀር ሆነ። እንደደረስንም የተነሳው የሲቲስካኑ ወጤት ትንሹ አንጀቱ ውስጥ ችግር እንዳለ አሳየ . . ችግሩም ያንጀት መቆላለፍ ወይንም መጠላለፍ (ኦብስትራክሽን) መሆኑ ተደረሰበት። ትንሹ አንጀት ላይ ሄዶ ሄዶ በስተመጨረሻ ከትልቅ አንጀቱ ጋር ወደመገናኛው። ወዲያውኑ ጥበቡ ሆስፒታል እንዲተኛ ተደርጎ አስፈላጊና ተጨማሪ ምርመራዎች ተጧጧፉ። የሆዱንም ሕመም ለማስታገስ ወትሮው ይሰጠው የነበረው ሥቃዩን ሊመጥነው ስላልቻለ ያለማቋረጥ ለሰውነቱ አመጣጥኖ የሚሰጥና ከዚያ አልፎ ከመጣ ደግሞ ጥበቡ በእጁ በመጫን በደምሥሩ ወደውስጡ የሚልክ ኃይለኛ የሕመም (ፔይን) ማስታገሻ መድኃኒት ማቀበያ መሣሪያ ተገጠመለት። በአንጀት መጠላለፉ ምክንያትም ብዙ ወደላይ ስለሚያሰኘው ያን ለማስቆም፣ የሆዱንም ውጥረትና መጨናነቅ ለመቀነስ "ኤን ጂ ትዩብ" የሚባለውን አጎዥ ፕላስቲክ ቀጠን ያለ ቱቦ በአፍንጫው አስገቡ።

በዚህ መልኩ አንጀቱ ራሱ በራሱ ችግሩን ይፈታ እንደሆ ቢጠበቅም ምንም ለውጥ ስላልተገኘ በሐኪሞቹ ዘንድ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ሆነ። ሰው አንጀቱ ተጠላልፎ እንኳን 3 ሳምንት 3 ቀንም ከቆየ ያለው ዕድል መሞት ነው።

አሁን ለተከሰተው ችግር አንዱና ብቸኛ መንገድ ቀዶ ጥገና ነው። ያውም ባስቸኳይ! ዋናው የቀዶ ጥገናው ሐኪም ከነቡድኑ ጥበቡን ለማየትና ሊያማክረንም መጣ። ጥበቡ ግን ያንን

መሰል አፕራስዮን ሰውነቱ ፈጽሞ ሊቋቋም አይችልም፤ ለምን?

- በውስጡ ከተካሄደው የጤና ችግርና ተከትሎት ከመጣው አንድ ሺ አንድ ምክንያት የተነሳ።
- ከቁስል ለመሻር በጣም አስፈላጊ ከሆነው ‘አልብዩሚን’ ከሚባለው የፕሮቲን ከፍተኛ እጥረት የተነሳ። (ለቀዶ ጥገናው ቁስል ፈጣን ሽረት እጅግ አስፈላጊ የሆነው ይሄ ንጥረ ነገር በጥበቡ ሰውነት ውስጥ ከማነሱ የተነሳ።)
- የከናዳዎቹ ሐኪሞች ትልቅ አንጀቱን አልፈው መብሳታቸው ካስከተለው ችግር የተነሳ። (ከዚያ በሚወጡ አደገኛ ባክቴርያዎች ምክንያት ተደጋጋሚ ኢንፌክሽን ገጥሞታል። በዚህ ችግር ብቻ ሕይወቱን ሊያሳልፉ ይችሉ የነበሩትን ባክቴርያዎች እግዚአብሔር ተቆጣጥሮ ነው፤ እንኳንስ ይሄን መሳይ መራቢያ ኩሬ ተጨምሮላቸው።)
- ሰሞኑን ደግሞ በደምስሩ ከሚሰጠው በቀር በአፉ ይመገብ የነበረው ሁሉ ስለተቋረጠ ያለምግብ ብዙ ከመንዳቱ የተነሳ።

ስለዚህ ዋናው ሰርጂን ባጭሩ ያለው ነገር ቢኖር፡- “ልገልህ ካልፈለግሁ በቀር ይሄን ቀዶ ጥገና ባንተ ላይ ልሞክረው አላስብም!” ሐኪሙ ከንጓዙ ከፍሉን ለቆልኝ እስኪወጣ ነፍሴ ተጣደፈች። እሱ ግራ ቢገባው ግራ የማይገባው አምላክ አለን እኮ እለኝ ውስጤ! የማምለጪያ እለቴን ተተግኼ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ለስልፍ በጾም በጸሎት ወጣን። የውዴን የጥበቡን ሕይወት ለማትረፍ የሰው መላ ጠፍቶ በሚፈለግበት በዚህ ውድቅት ሌሊት፣ በሌሊት ዝማሬን የሚሰጠው እግዚአብሔር፣ ነፍሴ የምትዘምራቸው 3እና 4 መዝሙሮች ሰጥቷታል። የቆምኩበት የማይናወጠው ዐለቴ እግዚአብሔር ያለውን የሚያደርግ፣ ሲጠበቅ የሚመጣ፣ ቶሎም የሚደርስ አምላክ መሆኑን አስረግጬ የማመን ጉልበቴን አምላኬ በጠላቴ ላይ ኃይለኛ አደረገው። ይልቁንስ ሌላ ሌላውን ትቶሽ ለምስጋና ተዘጋጂ እያልኩ ነፍሴን የመከርኩባቸው ጉልበታም መልእክት ያላቸውን መዝሙሮች እግዚአብሔር በውስጤ አፈሰሰልኝ! ለአንዳንዶችም በየምባይላቸው ላይ ላኩላቸው። “ኧረ እሱ ይመጣል” “እጠባበቃለሁ” “ቶሎ ድረስ ጌታ” ነፍሴ ሆይ ተይ!” ከእነዚህ ከአራቱ በተለይ የአንደኛው አንድ ስንኝና አዝማች እንዲህ ይላል።

*ያድነናል ያልንህ ሆይ!*
*ይፈውሰናል ያልንህ ሆይ!*
*አትመጣልንም ወይ?*
*ኧረ እሱ ይመጣል!*
*ያሉን ቃል ያከብራል!*
*እንዳለው ያደርጋል!*
*ኃይል አለው ይችላል!*

የዴንቨሯ ኢትዮጵያ ወንጌላውያን ቤተክርስቲያን መሪዎች ከፓስተር እንደሻውና ከምእመናኑ ጋር የጸሎትና የምልጃ “ምጥ” ውስጥ አብረውኝ ገቡ። ኢትዮጵያ ላሉ በቅርብ ሁኔታችንን ለሚከታተሉ የጸሎት አገልጋዮች፣ ለቤተክርስቲያን እረኞችና ወገኖቻችን. . የሚችሉ ሁሉ አብረውን እንዲቆሙ መልእክት አስተላለፍኩ። “ሐኪሞቹ የሚሉትን ሰምተሃል። አንተስ ምን

ትላለህ እግዚአብሔር??"

ቀዶ ጥገናው ካልሆነ ሌላው መፍትሄ ምን ሊሆን እንደሚችል ሐኪሞች መወያየታቸውን ተያያዙት። በአፍንጫው የከተቱት ትዩብ ከሁለት ሳምንት በላይ ከቆየ የራሱ ችግርና ኢንፌክሽን ስለሚፈጥር እሱን መዘን ማውጣት ይኖርብናል አሉ ሐኪሞች። የሆዱን ውጥረት ለመቀነስ ግን በውጪ ሆዱ ላይ ቀዳዳ ሠርተን ሌላ ትዩብ (ጂትዩብ) ማስገባት አለብን ሲሉ መፍትሄ ብለው ያሰቡትን እስከሚያስከትለው ችግር ጭምር ይዘውልኝ ቀረቡ። ልቀበለው አልቻልኩም።

በሚሰጠው የሕመም ማስታገሻ መድኃኒት ምክንያት በዚህ ወቅት በብዛት ስለሚተኛ ውሳኔውን እኔ እንድወስን እጠበቃለሁ። የቀረበው አሳብ በጊዜው ሐኪሞቹ የታያቸው አማራጭ የሌለው ብቸኛ አሳብ ነው። እንድቀበላቸውና ያሉትን ትዩብ አስገብተው ወደቤት ሊልኩን አንዳንዶቹ ሐኪሞች ይፈልጋሉ። እኔ ግን "አሻፈረኝ አይሆንም" አልኩ። ለምን ሀሳቡን መቀበል እንዳልተመቸኝ ለማወቅ በጥያቄ አንዳንድ ሐኪሞች ያዋከቡኝ ጀመር። ምናልባት የኔ ግትርነት እንዳይሆን ብዬም ከልጆቻችን ጋር ሆኜ ሃሳቡን አውጥተን አውረድን.. ጸለይን። ጉዳዩ የሚመለከተውንም የኢንተርቬንሽናል ሬድዮሎጂ ሐኪም አእምሯችንን የወጠረውን ጥያቄያችንን ሁሉ ጠየቅነው። በተረዳነው መሠረት እኔና ልጆቹ አሁንም እሺ ለማለት አስቸገረን። ምክንያታችን፡- ጥበቡን

- ለኢንፌክሺን ስለሚያጋልጠው..
- ላንጀቱ መጠላለፍ ምንም መፍትሔ ስለማያመጣ፣..
- ያም ሁሉ ተደርጎ ምግብ መውሰድ ስለማያስችለው።

እኔም ለሚወተውቱኝ ሐኪሞች፡- "ያቀረባችሁልን አሳብ የቱም አልተመቸንም። አሁን የሚያስፈልገን ተአምራት ነው። እኛ ደግሞ ተአምር በሚያደርግ አምላክ እናምናለንና እንጸልያለን። ተዉን፤" ማለት ጀመርኩ።

****

*ኦገስት 5/2011* ዐርብ ጠዋት ከንጋቱ 12 ሰዓት ነው። የሆድ ዕቃን ሕመም በሚመለከት በተለያየ መልኩ እስፔሺያሊቲው ያላቸውና ሌሎቹም በዚህ አስቸጋሪ ጉዳይ ለመምከር እኔና ልጆቻችን ባለንበት ሊመከከሩ ኮንፍረንስ ጠሩ። ጥበቡን ለረጂም ጊዜ ሲያክም የነበረ ዶ/ር ፋካሚ የሚባል አንድ ጎበዝ ጃፓናዊ በጊዜው ሌላ ከተማ ስለነበር መላ ፍለጋ ከርሱ ጋር ቴሌኮንፈረንስ አደረጉ። ዶ/ር ፋካሚ አንድ የሆነ የመሣሪያ ስም ጠቅሶ አሜሪካ ውስጥ እቃው ይገኝ አይገኝ እንደሁ ጠየቃቸ፤ የመሣሪያውንም አገልግሎት ሲናገር እለዩ ካሜራ የተገጠመበት በጣም ረጂም ነገር እንደሆነና በኢንዶስኮፒ ወደ አንጀቱ በመላክ የተጠላለፈውን አንጀት መፍታት ይቻላል! መሣሪያው አሜሪካ ውስጥ እንደሌለ ሐኪሞቹ ተናገሩ። ዶ/ር ፋካሚም መልሶ፡- "እንግዲያው መሣሪያው ጃፓን ውስጥ አለ" አላቸው። የሐኪሞቹ ውሳኔ ባንድ ድምፅ፡- "ቶሎ ባስቸኳይ ይሄን ያልከውን መሣሪያ እዘዝና አስመጣለት!" ኮንፍረንስ የተቀመጡት ሐኪሞች ለዚህ ችግር የሚሆን የተስፋ ጭላንጭል ስለታየ ደስ አላቸው። "ዶ/ር ኃይለሥላሴ ስፔሺያል ሰው ስለሆነ መሣሪያ ከጃፓን ድረስ ልናስመጣለት ነው! በእውነት መልካም ዜና ነው" በማለት አንዳንዶቹም ደስታቸውን እኔንና ልጆቻችንን በማቀፍ ገለጹ! ይህን መሳይ አስገራሚ ውሳኔ በዚህ ዓርብ ማለዳ በነዚህ አሜሪካውያን ሐኪሞች በመወሰኑ እኛም ተደስተን እግዚአብሔርን አመሰገነው።

የዳዲ ሁኔታ ግን ያን ዕለት ወደ አሳሳቢ ደረጃ ደረሰ። በጠዋቱ ኮንፍረንስ ያልነበረ ሐኪም በሩን ከፍቶ ወደ ክፍላችን ገባ። ሆዱ ላይ ቀዳዳ ፈጥረው ትዩቡን እንዳያስገቡ ለምን እንዳልፈለግን

ጠየቀኝ። ለሌሎቹ ስለው የከረምኩትን ደገምኩለት። "የተባለውን ነገር በዚህ በምወደው ባለቤቴ ላይ እንዲደረግና ሌላ ችግር ውስጥ እንዲገባ አልፈልግም። እኛ ተአምር በሚያደርግ አምላክ ስለምናምን ጊዜ ስጡንና እንጸልይ"። "ጊዜ...?? እሺ! እስከ ሰኞ እንጠብቃችኋለን! ከሰኞ በኋላ ግን ያቀረብንላችሁን አሳብ ካልተቀበላችሁ እቤት ሆናችሁ የጃፓኑን መሣሪያ ትጠባበቃላችሁ!" ይገርማል፣ ጠዋት ደስታ አሁን ደግሞ ግራ መጋባት? ውስጤ ከጃፓኑም ዕቃ ይልቅ የአምላኬን ኃይል ይጠባበቃል! ምሽቱን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና ፓስተር እንደሻው መጥተው በመቃተትና በእምልነ የጌታን ራት አካፈሉን። ለጸሎት ፕራይቬሲያችንን እንዲጠብቁ ሐኪሞቹንና ነርሶቹን በመንገር በራችን ላይ ማስታወቂያ ለጠፍን። ሕክምናን በሚመለከት ምንም ሊያደርጉ አልቻሉም። በእርሱ ሁሉን ቻይነት ያመለጥናቸውን ብዙ ሞቶች እያስታወስን ዛሬንም የሚያሻግረን አንድና አንድ ኃይል እግዚአብሔር ብቻ ነው አልን።

****

*ሌሊቱ ነጋ!*

ኦገስት 6 ዐርብ ለቅዳሜ አጥቢያ፤ ሌሊቱን አምላኬን ጠበቅሁት። እግዚአብሔር "ዝም" ያለበት ሌሊት፤ ያም እንደማይነጋ የለምና ነጋ። ከናይሮቢ እህት ጓደኛዬ ውድነሽ እዚነ መጥታ ከእኔ ጋር አብረን አድረናል። ለጸሎት ስንነቃ፣ ምናልባት እሷ ከእግዚአብሔር የሰማቺው ካለ ፍለጋ፣ "ውድዬ እግዚአብሔር ዝም አለ አይደል?" አልኳት። መልሱ በእጇ ቢኖር በሙሉ ደስታ ልታደርግልኝ ትወድ ነበር። የምትለኝ ስለሌላት ግን በኀዘን እንደተሞላች አየኋት።

"አይዞሽ እህቴ!" አልኳት መልሼ። ለረድኤቴ በደመናት ላይ እየተረማመደ ደግሞ ደጋግሞ ደርሶ የታደገኝ እግዚአብሔር ትውስ እያለኝ! ሆስፒታል ከዳዲ ጋር ያደረውን ልጃችንን ኢያሱን ደውዬ እንዴት እንዳደረ ጠየቅሁት፤ "ምንም ለውጥ የለም" አለኝ። እኔ ግን ያን ቅዳሜ ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ ከምስጋና መዝሙር ጋር ነው የነቃሁት። "የአጥብቃችሁ ጸልዩልን" ጥሪያችን የደረሳቸው ወገኖች ስልኮች ጥሪ በተከታታይ ከኢትዮጵያ ተዥጎደጎዱ። እናም ወደ ሆስፒታል ተቻኩለን ደረስን። ጠዋት ተረኛ ከነበረው ሐኪም ጋር ምንም ለውጥ እንደሌለው ተነጋገርን። "የተለያዩ ሰዎች ከኢትዮጵያ ጭምር ለጸሎት ይደውላሉ። ስለዚህ ጸጥታ ያስፈልገናል"። "ከኢትዮጵያ ድረስ...?." አለ በመገረም። "አዎን! የሚያስፈልገን አሁን የአምላካችን እጅ ብቻ ነው!"

ፓስተር ፊቃዱ አፍጋ ፓስተር መርዕድ ለማ ወንድም ሳሙኤል ኃይሉ አከታትለው አብረውኝ ሊጸልዩ ከኢትዮጵያ ደወሉ። ከአሜሪካ ከካናዳ ከእስራኤልና ከአውሮፓ እንዲሁም በኢንተርኔት "ከፓል ቶክ መድረክ" .... ጸሎቱ ተቀጣጠለ። ምንም እንኳ በሚሰጠው መድኃኒት ምክንያት ባብዛኛው ጥበቡ እንቅልፍ ውስጥ ቢሆንም የሚጸልዩትን ጸሎት እንዲሰማው እንዳመቺነቱ ስልኩን በድምጽ ማጉያ ላይ አድርጌ በጆሮው ላይ አደረግሁት።

እኔ ቀኑን ሙሉ በአንድ መዝሙር ውስጥ ዋልኩ፣ ነፍሴ በውስጤ እሱን ስለሆነ የምታቀነቅነው እንደበቴም፡- "እወድሃለሁ እወድሃለሁ እወድሃለሁ የሚገባኝ ይሄ ነው.... እማውቀው ይሄን ነው"፤ ልቤ ይዘምራል፤ ሕይወት ስልፍ ቢሆንም፣ መከራውና ፈተናው ሁሉ ከዚህ ከምወደው ከጌታዬ ሊለየኝ እንደማይችል ለጠላቴ ነገርኩት። አምላኬን "....እወድሃለሁ.." እያልኩት ውያለሁ። በቅርብም በሩቅም ካሉት ወገኖች ጋር ሰለቱን በጾም ጸሎት ላይ ነን። እህቴ ውደም አብራኝ በዚሁ መንፈስ ሆና እዚያው ክፍል ውስጥ ያለው ሶፋ ላይ ጋደም ብላለች።

ድንገትም ጥበቡ ከእንቅልፉ ነቃና። "ማሚዬ ወደ መታጠቢያ ቤት ውሰጂኝ" "እሺ ዳዲዬ!" ከልጋው ደግፌው አወረድኩት። አጠገቡ የነበረውንም ግሉኮዝ የተንጠለጠለበትን የቆመ ብረት እየገፋሁ ወደ መታጠቢያው ቤት ልወስደው አልጋው ግርጌ ደርሻለሁ። "እወድሃለሁ እወድሃለሁ.... ሚገባኝ ይሄ ነው ...የማውቀው ይሄን ነው" . . .

ድንገትም ሰይጣን፡- "እንግዲህ ዛሬ ቅዳሜ ነው ... እሱ በዚህ ሁኔታ እያለ፣ ምንም ነገር ሳይሆን፣ ያም ሰኞ ሊደርስ ነው! እንግዲህ የጸሎታችሁ ውጤት ሊታይ ነዋ!" ሲል ሹክ አለኝ። እንዲህ ያለ ነገር ወደኔ ሲመጣ የማደርገው፣ በቃ ተነስቶ የሰይጣንን አሳብ በጌታ ስም መገሰጽ ነው. . ማሰር ነው። ዛሬ ግን የሚሰማኝን ሹክሹታም ሆነ ጫጫታ ነፍሴ እየጣሰች በእንባ አምላኳን ልቤን በሞላው በዚያ መዝሙር ማምለክ ነው። መታጠቢያ ቤቱ ደርሰን እንደተቀመጠ የሆነው ግን፣ አስደናቂና መ-ለ-ኮ-ታ-ዊ ነው! ሦስት ሳምንት ሙሉ የተቆላለፈውን አንጀት እግዚአብሔር ተረተረው! እንደልቡ! ሃሌሉያ! . . .

ኦ! የጠበቅሁት ጌታዬና አምላኬ! ወደእነዚያ የጭንቅ ሳምንታት በአድራሻችን መጣ። በግንባሬ ወለሉ ላይ ተደፋሁ! "ጌታዬ ሆይ! መጣህልኝ እንዴ? ከሰኞ በፊት ዛሬ ቅዳሜ መጣህልኝ እንዴ? . . . ደረስክልኝ እንዴ!?" ... እንደ እብድ ደጋግሜ ይሄን ነው የምለው! ብቻውን ይሄን ታላቅ ተአምራት ያደረገልንን የጌቶቹን ጌታ ክብር እንዲሰጡልኝና በምስጋና እንዲያጅቡኝ ቅዱሳን መላእክትን ተጣራሁ።

ጓደኛዬ ውዴ እዚያው ጋደም ባለችበት ሶፋ ላይ እያለች የኔ ድምፅ ተሰምቷታል። ይሄን ተአምር ከሚያደረግበት ከዚያ ክፍልና ከተደፋሁበት ካምላኬ እግር ሥር እኔ ግን መነሳት አልቻልኩም! ውድዬ ሲያመው እንደከረመ ዓይታለችና ያው ጠንከር ያለ ሁኔታ ገጥሞት እያለቀስኩ መጸለዬ ስለመሰላት ባለችበት ሆና የጌታን ስም እየጠራች ነው። ጠላት ከለጠጠው የሞት ፍላጻ እየታደገ፣ ለዚህኛውም አዲስ ተአምር ያበቃንን እግዚአብሔር፣ እያቃሰተም ቢሆን፣ የኔም ውድ ጥበቡ፣ ከትልቅ ጦር ሜዳ ቆስሎ፣ በድል እንደተመለሰ አርበኛ አምላኩን፡- "ተ-መ-ስ-ገ-ን! ክ-ብ-ር!" ሲለው ጆሮዎቼ ሰሙት!

ጥበቡን ይዤ ስወጣ፣ የጸሎት ድምፅና እንባ የመሰላትን ጓደኛዬን፣ "ውድዬ እግዚአብሔር እኮ መጣልን! ከሰኞ በፊት ቅዳሜ ደረሰልን እኮ ! ጌታ እኮ ድንቅ አደረገልን!" ብዙ እልልታ! ምስጋና! ስግደት! የምናደርገው ጠፋን!

አብረውን በጸሎት ለከረሙት ወገኖች ሁሉ ስልክ እየደወልኩ የምናገረው ቃል፡- "ጌታ እኮ መጣልን!" ብቻ ሆነ! ይህም ድንቅ በቅዱሳን ሁሉ ዘንድ ተሰማ! ይሳካ አይሰካ ባይታወቅም ልዩና ዓይነተኛ ተብሎ ከጃፓን እስኪመጣ ይጠበቅ ከነበረው መሣሪያ በፊት በማንም የማይቀደመው የሠራዊት እግዚአብሔር አምላካችን ደረሰልን!

ልጆቻችን እግዚአብሔር ባደረገልን ትድግና የሚሉት ጠፋባቸው! ጥያቄ ግን ነበራቸው። "ማሚዬ ሐኪሞቹ ሰሙ? መጡ? ምንስ አሉ??" ሐኪሞቹማ "አይውጡት አይተፉት" ዓይነት ጉድ ሆኖባቸዋል። ጉዳዩን ባያነሱት ዓይተው እንዳላየ ሰምተው እንዳልሰማ መሆንን መርጠዋል። ቢወዱም ባይወዱም ግን አንድ እውነት ተገልጧል! መላው ጠፍቶ እንዲያ በምክክር የሰነበቱት ሐኪሞችም ሆኑ.... "እሺ. . እስከ. . ሰኞ። ከሰኞ በኋላ ግን..." ሲሉ የዛቱብን ሁሉ የምናመልከው አምላክ በእርግጥም ሕያውና፣ ድንቅ አድራጊ መሆኑን ሊያስተባብሉት በማይችሉት መንገድ ዓይተውታል! ሃሌሉያ!

****

*"እኔ በካንሰር በሽታ አልሞትም!"*

ኤፕሪል 2012 ጥበቡ ሆስፒታል ከገባባቸው ባንዱ ወቅት ነው። ዶ/ር አሊስኪ ይባላል፤ የጊዜው የሜዲካል ፍሎሩ ተቀባይ (አቴንዲንግ) ሐኪም። የጥበቡን የሲቲ ስካን ውጤት የተረዳውን ሊያረዳኝ ነው አመጣጡ። ጥበቡን እስከ ዛሬ በተቀባይ ሐኪምነት ከተቀበሉት"ፕራይሜሪ ቲም" መሀል አይደለም። በመጠኑም ቢሆን ስለጥበቡ መዝገብ አገላብጦ የሚያውቀው ኢንፎርሜሽን አለው። ጁላይ 2010 ውስጥ ለኮሎኖስኮፒ ፕሮሲጀር ጥበቡ ገብቶ ሳለ እግረ መንገድ ስለተገኘ "ሬክታል ካንሰር" ያውቃል። እንኳን አሁን ከሁለት ዓመት በኋላ፣ የግኝታቸው ዕለትም ሲነገረኝ አብረውኝ ለነበሩ፣ ሊጎበኙን ከናይሮቢና ከአዲስ አበባ ለመጡ እህትማማች ጓደኞቼና ሚዜዎቼ (ስንቁና ውዴ)፣ ያልኳቸውን በውል አስታውሳለሁ፡- "ካንሰር የበሽታ ስም ብቻ ነው። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ግን ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነና የሚፈውስም ነው! እግዚአብሔር እኛን ወደርሱ ለመሰብሰብ ካንሰር...አያስፈልገውም! ጊዜያችን ሲደርስ በቃ እሱ ሲፈልገን እንሄዳለን"፤ ነበር ያልኳቸው።

እናም ላለፉት ሁለት ዓመታት ያ የተባለ ካንሰር ወደቀረው ሰውነቱ እንዳይዘምት እኛ በእግዚአብሔር ታምነን ጸልየናል፤ አስረነዋል። እኔ የማውቀው እሱም ታዞ ካለበት ስፍር እንዳልወጣ ነው! ዶ/ር አሊስኪ ግን ይሄን ከመዛግብቱ ያነበበውን ግኝት አሁን ሲቲስካኑ ካቀረበው ሪፖርት ጋር በማቀናጀት ይመስላል 'መርዶ ሊያረዳኝ' ጥበቡ የተኛበትን ክፍል ከፍቶ ሲገባ፡- ራሱን እከክ እከክ እያደረገ፡- "ሲቲስካኑ እንደሚያሳየው አንጀቱ የመቆጣት መልክ ያሳያል (ኢንፍሌምድና ዳየሌትድ ሆኗል...)። ያው ይሄ ደግሞ የምንጠብቀው የካንሰሩ መስፋፋት ባሕርይ ነው። እንግዲህ ባለቤትሽ ከዚህ ወዲህ በሕክምና ረገድ የምናደርግለት ብዙ ስለሌለ ምቾቱ እየተጠበቀ ስቃይ እንዳይበዛበት ወደሚደረግበት ወደ "ሆስፒስ" (ተስፋ የሌላቸው ሕሙማን እስከዕለተ ሞታቸው የሚጠበቁበት ቦታ) ቢወሰድ ይሻላል" አለ። ደግነቱ ጥበቡ ጭው አርጎ እንቅልፍ ወስዶታል።

ትንሽ ዞር ሊልብኝ ጀመረ፤ እንባዬም ቅርዝዝ ...ዝርግፍ... አለ። ግን ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው ሆኜ ዶ/ር አሊስኪን ያገኙት፡-

"ዶ/ር አሊስኪ! የባለቤቴን ሁኔታ እንዲህ በቀላሉ ለእኔ በመንገርህ አዝናለሁ። የምትለው መልካም ዜና ስላይደለ። ስላየኸው የአንጀቱ መቆጣት ከሆነ እዚህ ግምጋሜ ላይ የደረስከው ... የምትነግረኝን ሪፖርት ለመቀበል ያስቸግረኛል። ምክንያቱም ከተጎዳው ቆሽቱ በሚፈሰው ፈሳሽና በሐኪሞች እጅ ከተሸነቆረው አንጀቱ በሚወጡት ባክቴሪያዎች ምክንያት የአንጀቱ ኢንፍላሜሽን ሁሌም ያለ ነው። ከተደጋጋሚ ኢንፌክሽን ጋር። ይሄ ደግሞ ካንሰር አለ ከመባሉ በፊት ጀምሮ የነበረ ለመሆኑ ከታሪኩ ታገኘዋለህ።"

አልኩትና፣ ሐኪሞች ያስረዱኝ እኔም እንዳቅሚ ያነበብኩት ትዝ ስላለኝ፣ ባልጠበቀው ሌላ ጥያቄዬ አፋጠጥኩት!

"ለመሆኑ የጉበቱ ሪፖርት ምን ያመለክታል? ካንሰር እዚያ አካባቢ ደርሷል? ካንሰሩስ በፊት አለው ከተባለው መጠን ምን ያህል ጨምሯል? ፊኛውስ? . . ."

ዶ/ር አሊስኪ ተደናገጠ! የካንሰር ደብዛውም እዚያ የለምና ምን ያውራ! ምንስ ይበለኝ!

"ለማንኛውም አሁን ሆስፒታል የገባንበት ዋናው ምክንያት ኢንፌክሽንና ድካም ስላለው ነው። እነዚህ ችግሮች መፍትሄ ሳያገኙ መውጣት አይችልም! ሙሉ የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው እንጂ የነጻ ታካሚም ሰው አይደለም!"

ጠንከር ያለውን ንግግሬን ገና አብላልቶ ሳይጨርስ፣ ሌላም ጨመረኩለት።

"ሌላም ደግሞ፤ የአንጀት ስፔሽያሊስቱ ፣ የኦንኮሎጂው (ካንሰር) ፣ እና በተለያየ ዘርፍ የባለቤቴን ጤና የሚከታተሉት ሐኪሞች ሁሉ አንተም ባለህበት ከእኔና ከልጆቻችን ጋር... የቤተሰብ ስብሰባ (ፋሚሊ ሚቲንግ ይሉታል) የማድረግ መብታችንን እንድታከብርልን ጥያቄ አቀርባለሁ!"

ፊጽሞ ያላሰበው መዘዝ ውስጥ ገባ! ሀፍረት እየተሰማው፣

"ይቅርታ ....ላበሳጪሽ ፈልጌ አይደለም! ከሲቲስካኑ የተረዳሁትን ነው የነገርኩሽ። ያልሻቸውን ሐኪሞች ለጠየቅሽው ስብሰባ እጠራለሁ፤ የነሱን አማካይ ሰዓት እንዳወቅሁ እነግርሻለሁ።"

"አመሰግናለሁ ዶ/ር አሊስኪ! ልጆቼም ስብሰባው ላይ እንዲገኙ ቀደም አድርገህ ብትነግረኝ ጥሩ ይሆናል።"

ቀኑንና ሰዐቱ ተነገረኝ። ዐርብ ጠዋት በ4 ሰዓት። ስበሰባው ላይ ጥያቄዬን አክብረው ከመጡት ሌሎች ሐኪሞች መሐል የኢንፌክሽስ በሽታ ስፔሺያሊስት ዶ/ር ሜዲትዝ እና ፕራይሜሪ ሐኪማችን ዶ/ር ሀይሰት ተገኝተዋል። ከእነዚህ መሐል ግን ዶ/ር አሊስኪ ወደ ስብሰባው ድርሽ አላለም! የስብሰባው ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቶ ይሆን እንዴ?? አሊስኪ በስብሰባው ላይ ተገኘም አልተገኘም፤ ስብሰባው ግን ቀጠለ! በዚህ ጉዳይ ላይ መልስ ሊሰጡ የሚገባቸው ሐኪሞች (የአንጀቱና የካንሰሩ ስፔሽያሊስቶች) ቃላቸውን ሰጡ።

"አሊስኪ በእርግጠኛነት ስለተናገረው የካንሰር መሰራጨት ሲቲስካኑን በማየት ብቻ ሙሉ መልስ መስጠት አንችልም። ነገር ግን ለምርመራ ያህል ከሆድ ውስጥ በሚወሰድ ውሃ (ፍሉድ) በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።"

ካሉ በኋላ የሆድዕቃው (ጂአይ) ሐኪም ደግሞ ወደ እኔ ዞር ብሎ

"አንቺ ያቀረብሺውን ጥያቄ ለመመለስ፣ ጉበቱ ውስጥም ሆነ ፊኛው ላይ የሚታይ ነገር የለም። የካንሰሩ ቱመርም ከዚህ በፊት ካየነው አልጨመረም። ከአካባቢውም ወጥቶ የሚታይ ነገር የለም። ለማንኛውም ከሲቲስካኑ ይልቅ ከሆዱ የሚወሰደው ፍሉድ ካይናችን ያመለጠ ነገር ቢኖር በእሱ እናገኘዋለን።"

ሐኪሞቹ ባዘዙት መሠረት ላስቸኳይ የላቦራቶሪ ውጤት ከጥበቡ ሆድ የተባለው ውሃ ተወሰደ። ሐኪም ሁሉ አሰፍስፎ የሚጠብቀው ካንሰር ዘሩም አልተገኘ! ያ ክርክሬም... በድል ተደመደመ!

ያ ብቻ አይደለም! ያን ዕለት እግዚአብሔር አምላክ ለቤተሰባችን የድሎች ሁሉ ድል የሆነ መንፈሳዊ ድል ሰጠን እንጂ! ውዴ የኔ ጥበቡ ያለፈበት የጥዝጣዜና የስቃይ ካሳ!

ጥሪያችንና ጥያቄያችንን አክብረው የመጡት ሐኪሞች የሚሉትን ለመስማት ከወትሮው ሁሉ ይልቅ ጥበቡ በዚህ ማለዳ ንቁ ነው። ሌላ ጊዜ ድካም ይሰማውና ከሚሰጠው የመድኃኒት ባሕሪም የተነሳ በብዛት ያንቀላፋ የነበረው ቀርቶ፣ ለዚህ አስገራሚ ቀን ነቅቷል። የዛሬው ሕመምተኛ... በወስጡ የሚፈራረቅበትን የሕመምና የጥዝጣዜ ጉልበት እየሰበረ ከሚወጣው ከፈገግታው ከትዕግሥቱና ከተስፋው በስተጀርባ ያለው ፣..ሁሌም ሲያዩት የሚገረሙበት የዚህ ሰው የሕይወቱ ምሥጢር ምን ይሆን??

ምናልባት ዛሬ በጥቂቱ የሚረዱበት መድረክ ሳይሆን አይቀርም! እኔና ልጆቻችን በልባችን

**ሞ**ልቶ የተረፈውን ለነዚህ ሐኪሞች ከማፍሰሳቸን በፊት ጥበቡ እንዲህ አለ፡-

*"ጥሪያችንን አክብራችሁ ስለመጣችሁ በቤተሰቤ ስም አመሰግናለሁ። ከሁሉ በላይ ደግሞ እናንተን የመሳሰሉ በፍቅርና በአክብሮት እንደ አንድ ጓደኛችሁ ስለጤናዬ ርብርቦሽ የምታደርጉልኝን ሐኪሞች የሰጠኝን አምላኬን አመሰግነዋለሁ! ስላደረጋችሁልኝና ስለኔ ከልባችሁ ስለምታስቡት ሁሉ ደግሞ እናንተንም አመሰግናለሁ። እንዲሁም ደግሞ፣ ስለምወዳትና ስለምትወደኝ ባለቤቴ፣ ባርኮ ስለሰጠንና ስለምወዳቸው ልጆቻችን አምላኬን ሁሌ አመሰግነዋለሁ። (እንባውን እያፈሰሰ) ባለቤቴ በዚህ ሁኔታዬ ምን ያህል መስዋዕትነት እየከፈለች እንደምታስታምመኝ ሳስብ 'ይህ እንዴት ሊሆን ይቻላል!' እላለሁ።*

*በተለይ ከሆስፒታል ውጭ እቤት በምንሆንበትና ሕመም በሚሰማኝ ጊዜ ሁሉ 'ጸልዩልኝ ሕመም ይሰማኛል' ስላት፣ ተንበርክካ ስትጸልይ ሕመሙ ወዲያው ይሄድና እኔ እንቅልፍ ይወስደኛል። ከረዢም ሰዓት በኋላም ነቅቼ ሳያት አሁንም ተንበርክካ ነው የማገኛት። እና እኔ በዚህ ጊዜ ልነግራችሁ የምፈልገው እኔም እንደናንተው ሐኪም እንደመሆኔ የሚሰጠው መድኃኒት ለአንድ ጤናው ለተጎዳ ሰው እንደሚረዳ አውቃለሁ።*

*ከዚህ በላይ ግን እኛ ሐኪሞች ልናደርግና ልንሰጥ የማንችለውን ፈውስ የሚሰጥ ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር እንዳለ ደግሞ አውቃለሁ፣ አምናለሁም። ስለዚህም እንደገጠመኝ የተወሳሰበ የጤንነት ተግዳሮት ቢሆን ኖሮ እኮ ሕይወቴ ማለፍ የነበረበት ያኔ ድሮ በመጀመሪያው ቀን ነበር። ከሚሰጠኝ መድኃኒት ጋር የጸሎቱ ኃይል ብዙ በሕይወቴ ሠርቶ ነው እንጂ። ባለፈው በገጠመኝ የአንጀት ኦብስትራክሽን የሆነውን እንዳንዶቻችሁ ታውቃላችሁ። በቀዶ ጥገና ዘዴ ምንም መፍትሄ በጠፋበት ወቅት የሆነ ተዐምራት ነው! ደግሞስ እናንተ ስታስቡት ይሄ ሁለት ዓመት ያለፈው የካንሰር ቱመር ካለበት አለመውጣቱ?! እስከሁን አለመስራጨቱስ?! ራሱ ተአምር አይደለምን? (ሁሉም በአዎንታ ራሳቸውን ነቀነቁ።)*

*የሰው ልጆች ሁሉ ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር አምላክ ለሐኪሞች፣ ለሳይንቲስቶች... በተለያየ መስክ ለተሰማሩ አዋቂዎችና ጥበበኞች ሁሉ፣ የዕውቀቱን ጠብታ ከፍሎ እንደሰጠ አምናለሁ። እና...ይሄን ሁሉ የምናገረው ጤናዬን ያስተጓጐሉትን የሕመም ዐይነቶች 'የሉም' ለማለት ሳይሆን፣ ከእነዚህ ሁሉ በላይ ኃይል ያለው የሚታደግ፣ ቢያስፈልግም ከሞት እንኳ የሚያስነሳ አምላክ አለ ለማለት ነው!"*

ካለ በኋላ ምናልባትም ዛሬ ላይ መለስ ብለው ሲያስቡት - "ያ ሰው በእርግጥ ነቢይ ነበረ" **የሚ**ያሰኛቸውን ነገር ተናግሮ ጨረሰ። እንዲህ ሲል፡-

*"..ደግሞ ይሄን አረጋግጥላችኋለሁ! እኔ በካንሰር በሽታ አልሞትም!"*

በክፍሉ ውስጥ የተገኙት ሐኪሞች በጥሞናና በአክብሮት ሲያዳምጡት መርፌ እንኳ

ቢወድቅ ሊያሰማ በሚያስችል ጸዋታና አንዳንዶቹ እንባቸውን በመቆጣጠር ነበር። ለእኔና ለልጆቻችን ደግሞ እግዚአብሔር ለእነዚህ ሐኪሞች የምንመሰክርበትን ተራ ሰጠን! በተለይም ደግሞ አባቷ ተማርኮ ወደ ሶማሊያ በተወሰደበት በዚያው ቀን የተወለደቺው መካከለኛዋ ልጃችን ረቂቅ፣ ከሕፃንነቷ እስከሁን በቤተሰባችን የሆነውን ሁሉ በሚያስገርም ጸጋና ኃይል ተሞልታ መሰከረቺላቸው! እንባቸው አቆርዝዞ ከነበሩት መሐል በተለይ አንደኛዋ ሐኪም መንታ መንታውን ትዘረግፈው ጀመር!

ያንን ቀን እንደ ቤተሰብ የምናመልከው ጌታ እግዚአብሔር በሕይወታችን ተገልጦ ስለሠራው አስደናቂ ታሪክና ታላላቅ ተአምራት ለሐኪሞቹ የምንመሰክርበት መድረክ አድርጎ ለወጠልን! የሰው ልጅ ምድራዊ የሕይወቱን ዘመን ለፈጣሪው ቢያስረክብ፣ ጌታ ክርስቶስ በገሃዱ ዓለም ሊያደርግ ስለሚችለው ታላቅ መለኮታዊ ሥራ! በዚያን ቀን . . በጥበቡ ጤንነት ዙሪያ እንደቤተሰብ የገጠመን ተግዳሮት የገዘፈና የተወሳሰበ ቢሆንም የጽናታችንና የተስፋችን ምሥጢር ሐኪሞቹ ገባቸው! ባለፈው ዘመን በእኛና በልጆቻችን ድንቅ ያደረገ አምላካችን ዛሬም እንደገና ሌላ ' ተዓምር ሊያደርግ ይችላል' ብለን የማመናችን ምሥጢር! ትላንት በቤታችን የገለጠውን ኃያል ክንዱን ዛሬም በዚህ ተግዳሮት ላይ ሊገልጠው ይችላል ብለን መጸለያችን...ሞኝነት እንዳይደለ...ሐኪሞቹ ገባቸው!

አዎን! የዛሬው ሕመምተኛ... ጥበቡ ኃይለሥላሴ . . እሱም እንደጌታው፣ በሸላቾቹ ፊት ዝም እንደሚል በግ የሆነ ቢመስልም፣ ጀግና አንበሳና የእምነት አርበኛ መሆኑ ሐኪሞቹ ገባቸው ... በአልጋው ዙሪያ የተሰበሰቡት፣ አንዳንዶቹ ቢያንስ ላለፉት አራት ዓመታት የጤናውን ሁኔታ ሲከታተሉ ነበርና... የዚህ ልዩ ሰው የሕይወቱ ምሥጢር አሁን ገባቸው! የፈገግታውና የትዕግስቱ ምሥጢር. . ከዚህ አስገራሚ ሰው ሰብዕና በስተጀርባም የጌታ የእግዚአብሔር ሕልውናና የመስቀሉ ምሥጢር... ብልጭታው ታያቸው። ይህ ሳያውቁት የወደዱትና ያደነቁት ሰው የሚያስደንቅ ባለታሪክ እንደሆነም ገባቸው።

እስቲ ለጥቂት ጊዜ ከሆስፒታል ላውጣችሁ። ላውጣችሁና መጀመሪያ ወደ ቤቴ ቀጥሎም ወደ ቤተሰቤ ልውሰዳችሁ። ቤቴ ሰላሳ ሰባት ዓመት ወደኋላ ይመልሳችኋል። ቤተሰቤ ደግሞ እናቴ የአራስ ቤት ክፍል ድረስ ያዘልቃችኋል። የእኔና የጥበቡ ኃይለሥላሴ የአንድነት ሕይወት ጅማሬ እንዲህ ነበር!

****

# [illegible]

## ክፍል ሁለት

*የጥበብ መጀመሪያ*
*እግዚአብሔርን*
*መፍራት ነው*
*ሰነፎች ግን*
*ጥበብንና ተግሣጽን*
*ይንቃሉ።*

*(መጽሐፈ ምሳሌ 1፥7)*

# 4

## እሥራቴ

መስከረም 10 ቀን 1968 ዓ.ም። ሙሽራው ሊመጣ ደቂቃ ቀርቶታል። ሠርጌን ለማድመቅ ለኔም ያላቸውን ፍቅርና ክብር በሚችሉት ሁሉ ለመግለጽ የሚያማምሩ የክትና አዳዲስ



እኔና ጥበቡ በሠርጋችን ዕለት

ልብሶቻቸውን ለባብሰው ቤተዘመድ ሁሉ ተሰብስቧል። ቤታችን ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ጢም ያሉት ቆነጃጅትና ጎበዛዝት፣ እህት ወንድሞቼና ጓደኞቼ ሽር ጉድ በማለት ይናኛሉ። ሙሽራዬ ወጣቱ የሕክምና ምሩቅ ዶ/ር ጥበቡ ኃይለሥላሴ፣ ከእድምተኞቹ ጋር መጥቶ ሊወስደኝ ነው። የጋብቻ ሥነ

ሥርዓታችን የሚከናወነውም በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ነው፤ ስለዚህም የሁሉም ሰው ዓይንና ጆሮ፣ ደጅ ደጁን የሚቃኝበት ቅጽበት ነው! ለዕለቱ በየልካቸው በተዘጋጁ ዐይነ-ግቡ ሮዝ ረዣዥም የሚዜ ልብሶች የተላበሱት አራቱ የሴት ሚዜዎቼ (ሁለቱ ታናናሽ እህቶቼ ሲሆኑ ከቅርብ ጓደኞቼ መኻል ደግሞ ሁለቱ) በግራና በቀኝ ቆመዋል። ሁለቱ ትናንሽ ወንድሞቼና ትንሿ የአክስቴ ልጅ ደግሞ በሻማ ያዡነት፣ ከፊቴ በተጠንቀቅ ይገኛሉ፤ በፍቅርና በእንክብካቤ ያሳደጉኝ ልጃቸውን በወግ በማዕረግ ለመዳር የበቁት ወላጆቼ፣ ወ/ሮ አልማዝ እንግዳወርቅና አቶ አንገፍር ሠይፉ ናቸው፤ ዕለቱ ከፈጠረላቸው ልዩ ደስታ ጋር ተደበላልቆ እንጀታቸውን የሚያላውሰው የመለየት እውነት ዐይኖቻቸውን በዕንባ ያራጨዋል። ልለያቸው ነዋ! ከተሞሸርኩበት ነጭ የሙሽራ ልብስ ቬሎ (ዐይነ-ርግብ) ውስጥ ሆነው የሚያዩዋቸው የእኔ ዐይኖች በፊናቸው በዕንባ መታጠብ ግን "ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ" ተብሎ ከሚተረተው ተረት የጠለቀ ልዩነት ነበረው።



ጥበቡ ከወንድ ሚዜዎቹ ጋር

ከተላበስኩት ብሩህ ንጣት ከነበረው የሙሽራ ልብሴ በስቲያ፣ በሠርጌ ዕለትም ከነበረው አጀብ፣ ፈንጠዝያና ግርግር ማዶ... ነፍሴ ከእኔ ፈቀቅ ብላ የቆመች ያህል፣ ...በታላቅ ተመስጦ በአምላኳ ዙፋን ሥር ተደፍታ፣ በጽኑ ሆድ መባባት ትንሰቀሰቃለች። እንዲህ ስትሆን ያያት የስጋ ዐይኔም ዕንባውን መቆጣጠር አቅቶታል! አሁን እንደገና አገርሽቶባት እንጂ ነፍሴማ መንሰቅሰቅ የጀመረችው ገና በማለዳ ነበር! በዚያ በሠርጋችን ማለዳ። ልክ ከጠዋቱ በአሥራ ሁለት ሰዓት ዕለቱን ለእግዚአብሔር አሳልፈን ለመስጠት የጸሎት ቀጠሮ ነበረን። የጸሎቱ ፕሮግራም ከሚዜዎቻችን፣ ከቅርብ ጓደኞቻችንና ከቤተክርስቲያናችን አገልጋዮች ከወንድም መርዕድ ለማ እና ወንድም ፍቃዱ እፍጋ (አሁን ፓስተሮች) ጋር ነበር። የተነጋገርንበት የጸሎት ርዕስም በውል ትዝ ይለኛል፤ በሠርጋችን ሥነ ስርዓት ላይ ለመገኘት ከሁለታችንም ወገን ስለሚመጡት በርካታ እንግዶቻችን ጸለይን፤ ቤተ ክርስቲያናችን



ከሴት ሚዜዎቼ ጋር

ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመጡ ከሚሰሙት የወንጌል ቃል የተነሳ ነፍሳቸው ድኅነትን እንድታገኝ። የአምላካችንም የእግዚአብሔር ታላቅ ክብር የሚገለጥበት ቀን እንዲሆን። እግዚአብሔርም በዚህ ዕለት በምንጀምረው የአንድነት ኑሮ እንዲከብር... ነበር የጸሎት ርዕሳችን። በእነዚህ ሀሳቦች በኅብረት ስንጸልይ ሳለ ግን፣ በድንገት መንፈስ ቅዱስ በውስጤ ልዩ በሆነ መንገድ መቃተት ሲጀምር ተሰማኝ። እኔም የጸሎቴ አቅጣጫ በእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ተቀየረ አስተዋልኩ። በጸሎት ውስጥ እያለሁ፣ መንፈስ ቅዱስ ነፍሴን በሚያጽናናው መገኘቱ እየደባበሰ የሚናገረኝ ጠንከር ያለ ጉዳይ



ከቤተሰብ ጋር

ነበረው። የአምላኬ መንፈስ የሚያመለክተኝ ትዳራችን ስለሚገጥመው ታላቅ የፈተና ዘመን እንደሆን ውስጤ ይገባዋል! . . . ከአርያም ስለሚያስፈልገን ልዩ የእግዚአብሔር ጸጋ . . .። ፀንተን ብንቆም ደግሞ፣ ከዚያ ባሻገር በሕይወታችን ሁሉ ስለሚገለጠው የእግዚአብሔር ክብር ቊላንቊሉን እያሳየኝ ነበር። ልኬን የሚያውቀው መንፈስ ቅዱስ ዝርዝር ሁኔታውን አልተረከልኝም እንጂ። በወቅቱ ልሸከመው በምችለው መጠን ግን የሚቃትትበት ምሥጢር ከበድ ስላለ ጉዳይ መሆኑ በከፊል ገብቶኛል። ስለዚህ በጸሎቱ አዳራሽ ካጀቡን ውድ ወገኖች መኻል ነፍሴ ብር ብላ ወደ አርያም ገብታለች። ሁሉን በሚችለውና በሚያስችለው በአምላከዋ ዙፋን ሥር ተደፍታ በዕንባ እግሮቹን ስታጥብ ዓይቻታለሁ! ውስጤ በታላቅ መባባት ይንሰቀሰቃል። ከውጭ ደግሞ ኃይለኛ የዝናብ ዶፍ ይሰማኛል። ሰማይም እንኳን አብሮኝ የሚያለቅስ መሰለኝ! የዝናቡ ጎርፍ ከዐይኖቼ እንባ ጋር ተቀላቅሎ የልዑል እግዚአብሔርን ጸጋና ልዩ ኃይል ጨመረልኝ። የልቦናዬን ወገብ የሰማይ እጅ ታስታጠቀኝ። ነፍሴ በዚህች ልዩ ማለዳ እንዲያ የምትቃትትበት የጸሎቷ ርዕስም ሆነ ዝርዝር ጉዳዩ ሙሉ ለሙሉ አልገባትም። በመንፈስ ሆና የተረዳችው አንድ እውነት ግን ነበር። በውስጧ እንዳለፈ ሲያፍ በሚቆራርጥ ሁኔታ እርሷና ጥበቡ በትዳር ዘመናቸው የሚያልፉበት የሕይወት መንገድ እንደሚኖር ገብቷታል! በጸሎቴም፥-

*"እግዚአብሔር ሆይ! ብቻ አንተ ከእኛ ጋር ሁን! አንተ የቤታችን ራስና የበላይ ባለሥልጣን ነህ! አንተ በመሠረትከው በዚህ ትዳር ውስጥ በስፍራህ እስከ ተገኘህልን ክፉውን አንፈራም! በዚች ዓለም ውስጥ እስካለን ድረስ መከራ እንዳለብን እናውቃለን። ዓለምን በድል አድራጊነት ያሸነፍከው አንተ አምላካችን በኑሮአችን ሁሉ ቅደምልን፣ ከአንተ የተነሳ እኛም በድል እንወጣዋለን። ኃይልን በምትሰጠን በአንተም ሁሉን እንችላለን!"*

ይህም ብቻ አይደለም! ሩህሩሁ የሰማይ የምድር አምላኳም ለተሸበረቺው ነፍሴ "አይዞሽ

"እኔ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ" ሲል የተስፋ ቃሉን አሰምቷታል!!

ትዝ ይለኛል ያ ማለዳ። ጸሎታችንን ደምድመን ስንነሳ ደጁ ከሰማይ በወረደው ጠል ረስርሷል፤ በልዩ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተዳበሰችው ነፍሴም ፀጥና እረጭ ብላለች፤ ዐይኖቼ ግን ካገረፉት ዕንባ የተነሳ አባብጠው ሊጋጠሙ የደረሱ ይመስሉ ነበር! የሠርጉ ሥነ ስርዓት የሚጀምረው ከቀኑ ስምንት ሰዓት የቤተክርስቲያን ፕሮግራም በመሆኑ ዐይኖቼ እብጠታቸውን ለመቀነስ ጊዜ ነበራቸው።

ከጸሎቱ በኋላ ወደ ቤት ስመለስ በዕለቱ አብሮኝ በጎኔ ለመቆም ወደ ቤታችን የሚጎርፈው የሰው ቁጥር እየጨመረ ግር ግሩ በዝቷል። እግዚአብሔርን በሚያከብሩና በሚያሞግሱ መንፈሳዊ መዝሙሮች ቤቱ ይነዋወጣል። የሥጋ ዘመዶቼና ተጋባዦቻችን በሕይወታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኙበት "የጴንጤ" (ለወንጌል አማኝያን ከኅብረተሰቡ በዚያን ዘመን የተሰጠን መጠሪያ) ሠርግ ነበርና መገረም ይታይባቸዋል! በባህላችን እንደተለመደው በዘፈን በእስክስታና በዳንኪራ ሊድሩኝ የነበራቸው ሃሳብ ሲሻርባቸው፣ በብዙዎች የተፈራውን ያህል ቀርቶ ጥቂትም እንኳን እንዳያንጎራጉሩ እግዚአብሔር በመገኘቱ ፍርሃት ዘመዶቼን ውጧቸዋል።



የቃል ኪዳን ሥርዓት በቤተክርስቲያን

በዘመኑ ከሥጋ ዘመዳሞች ፍቅር መኻል ፣ ለዓይነትና ለናሙና ከሚጠቀሱ እጅግ ከሚተሳሰቡ ቤተዘመዶች መሀል እግዚአብሔር ወደ ራሱና ወደ ሰማያዊው ባህል ያፈለሰኝ ነበርኩ፤ የጌታን መንገድ በመከተሌ ኅብረተሰቡ የሚሰጠኝ ትልቅ ክብር እንደ ቀረብኝ ራሴንም እንደጎዳሁ ከተቆጠርኩ ዓመታት አልፈዋል። የሠርጌ ቀን ሲወሰን የቤተ ዘመዶቼን ተፅዕኖ ስለማውቅ፣ አምላኬ በወላጆቼ ፊት ሞገስ እንዲሰጠኝ ከጥበቡ ጋር አጠንክረን ጸለይን። የሚያሰክሩ አልኮል መጠጦች፣ ዘፈን፣ ጭፈራ፣ ዳንኪራም ሆነ ኦርኬስትራ ተጫዋቾች (ዘፋኞች) እንዳይኖሩ፣ ወላጆቼን "እሺ" ለማሰኘት። በኀዘኑም ሆነ በደስታው የፍቅርና የወገናዊነት ስሜታቸውን በጋለ ሁኔታ የመግለጽ ልማድ በነበራቸው በብዙዎች የሥጋ ዘመዶቼ አስተሳሰብ የማይሞከር ሃሳብ ነው። የውሳኔዬን ጭምጭምታ የሰሙ ዘመዶቼ በተለይም አያቴ ወ/ሮ አሰለፈች ለብቻዬ ወስዳ ገስጻኛለች። "እና ጠላና ጠጅ ላይጠመቅ? አልኮል ላይጠጣ? ዘፈን ላይዘፈን? ሠርግ ነው ወይስ ለቅሶ? አባትሽን በብስጭት ልትገዪው ፈልገሻል!"

አምላኬ ግን ስለዚህ ነገር የለመንኩትን የልመናዬን ቃል ሰማ!! የተፈራውን የአባቴን ልብ ነካው። በእኔም ሆነ በጥበቡ በኩል በሠርጋችን ዕለት እንዲሆንልን የፈለግነው የትዳራችን አምላክ ጌታ እግዚአብሔር እርሱ እንዲታወቅልንና እንዲመለከልን ብቻ ነበር። ከአሥራ አንድ ሰዓት ተኩል እስከ አንድ ሰዓት ተኩል አዲስ አበባ በሚገኘው በናይል ሆቴል የኮክቴል ግብዣ በወላጆቼ፣ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ ደግሞ በሆቴል ዲ አፍሪክ የራት ጥሪ በጥበቡ ቤተሰቦች ተደረገ። ሁሉም እንደወደድነው ሊፈፀምልን ተወሰነ!!

አባቴ ይህን ታላቅ የለውጥ እርምጃ እኔን ልጁን ለማስደሰት ሲል ወሰነ፤ ሁሉም በተቻለው እንዳይከፋኝ ደፋ ቀና በሚልበት በሠርጌ ቀን የማለዳው መባባት አገረሸብኝ! የሚገርመው ዐይኖቼን ከዕንባ መግታት እንዲያ በተሳነኝ በዚህ ልዩ ቀን ሰማይም ሊያግዘኝ የቆረጠ መምሰሉ ነበር፤ ከዘለው ጥቁር ደመና አልፎ አልፎ ዝናቡን ሲያንገርቀኘርቀው። በመካከሉ ግን ጣልቃ በመግባት ዝናብ ያዘለውን ያን ደመና ሰንጣጥቃ ፀሐይ ደግሞ ብርሃኗን ስትፈነጥቅ ላስተዋለው የሚደንቅ ትዕይንት ነበር። ልናልፍበት ባለው የሕይወት መንገድ ላይ ጨለማችንን እርሱ በመገኘቱ እያበራልን አምላካችን የማታ ማታ ስለሚያጎናጽፈን ድል ተፈጥሮም እንኳን በታላቅ ድምጽ የሚተነብይልኝ መሰለኝ!! የዕንባዬ ድቅን ድቅን ማለት ግራ ያጋባኝ እንጂ ነፍሴ ከሰፈፈባት ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተነሳ ውስጥዋ በምሥጢር ሀሴት ያደርጋል። የሙሽራው መምጫ ሰዓቱ ሲቃረብ ከዚያ ሁሉ ሕዝብና ግር ግር ይልቅ በውስጧ ጎልቶ የሚያስተጋባውን ልዩ ዜማ ነፍሴ ታቀነቅናለች። ድንገትም ከውጪ የብዙ መኪናዎች ጥሩንባ ፏ! ፏ! ፏ!!! ሲል፥-

"ሙሽራው መጣ! ሙሽራው መጣ! . . . ምን እየዘመርን እንቀበለው? ...ሙሽሪት ትጠየቅ!!"

ውስጤ ሲስተጋባ የነበረው መዝሙር እንደበቴን ሰንጥቆ ወጣና፥-

"የድል መንገድ ነው ይህ ጉዞዬ
ማንም አይለየኝም ከጌታዬ"

እልኩ!! ወዲያውኑ በቤትና በውጭ የሞላው ሕዝብ በታላቅ ድምጽ የነፍሴን መዝሙር እየዘመረ ሙሽራዬን ጥበቡን ተቀበለው። ዘመናችንን ሁሉ አምላካችንን አስከብረን ለማለፍ ልበ ቆራጥነትና ጀግንነት የሚያስታጥቅ ልዩ የእምነት ጉልበት ጨመረልኝ።

ወላጆቼን የተሰናበትኩት በዚህ መንፈሳዊ ጀግንነት ነበር! አዲሱን የትዳር ምዕራፍ የሚያስጀምረንን ሥነ ስርዓት ለማጠናቀቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን አመራን። ጥሪ የተደረገላቸው ክርስቲያን ወገኖች፣ ዘመዶቻችንና እንዲሁም እንግዶቻችን ቀድመው በስፍራው ተገኝተዋል። በቃል ኪዳን ስነ ስርዓቱ ላይ የዕለቱ መልዕክት አቅራቢ ወንጌላዊ ታፈሰ ፋፋ ነበር!

"ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ ዕንቁ እጅግ ይበልጣል። የባልዋ ልብ ይታመንባታል ምርኮም አይጎድልበትም። ዕድሜዋን ሙሉ መልካም ታደርጋለች ክፉም አታደርግም።... እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት እርስዋ ትመሰገናለች" ሲል ሰበከ።

የነፍሴ መልስ ደግሞ፥-

"እግዚአብሔር ሆይ! ወደ ደካማነቴና አለመብቃቴ ፈጽሞ አልመለከትም! አንተን የምትፈራዋን ያቺን ልባም ሴት ሊያደርገኝ ጸጋህ ስለሚችል አመሰግንሃለሁ..."

በሠርጋችን ዕለት የመረጥናቸው ዘማሪያን ካገለገሉ በኋላ ፕሮግራሙን የሚመራው ወንድም ጋይም ድንገት፥-"ለመሆኑ የሙሽሮች መዝሙር ምርጫ ምን ይሆን?" ብሎ ጥያቄ አቀረበ። ጥበቡም ፈጠን አለና፥-

"ጌታ ቅደምልኝ በኑሮዬ ሁሉ
ያንተ ስለሆነ በመከራ ድሉ!" አለ።

መደነቅ አሜንታዬን አስተጋባሁ፤እንደ ልብ አንድ መንፈስ የሰጠንን አምላካችንን አመሰገንኩት፤ ዐይኖቼም የደስታእንባቸውን ዘረገፉት!

በእንዲህ ያለ ሁኔታ የቤተ ክርስቲያኑ ፕሮግራም ሲካሄድ ሳለ ያ በጥቁር ደመና አቆርዝዞ

የነበረው ሰማይ አሁንም እንደገና ለዕለቱ ተሸከሞት የነበረውን ዝናብ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አራገፈው። ወዲያውኑ ደግሞ ደስ የሚያሰኝ ብሩህ ፀሐያማ ጊዜ ተተካ። በዕለቱ በቤተ ክርስቲያን ከተላለፈው መልዕክት ሌላ በዘመኔ ሁሉ በልቤ ውስጥ ተቀርጾ የቀረው በሠርጌ ዕለት ተፈጥሮ ያስተላለፈልኝ አስደናቂ መልዕክት ነበር! በዘመናችን የሚገጥመንን ጨለማ የሚያሸንፍ ብርሃን ከሰማይ እንደሚላክልን አምላካችንም እግዚአብሔር በሰልፋችን ሁሉ ተሰልፎ ድል እንደሚያቀዳጀን ገባኝ!

በኀዘን ቢሆን በደስታ... በህመም ቢሆን በጤና... ሞት እስኪለየን ድረስ በባልና ሚስትነት ፍቅር የአንድነት ኑሮአችንን ለመኖር በሰውና በእግዚአብሔር ፊት የጋብቻ ቀለበቶቻችንን በመለዋወጥ አንዳችን ለሌላችን ቃል ኪዳን ገባን። እንደየቅደም ተከተሉ ወደ ሚቀጥለው ፕሮግራም ለመገኘት "ጌታ ቅደምልኝ በኑሮዬ ሁሉ ያንተ ስለሆነ በመከራ ድሉ" የሚለውን "የድል መንገድ ነው ይህ ጉዞዬ ማንም አይለየኝም ከጌታዬ" ከሚለው መዝሙር ጋር በማፈራረቅ ልብን በሚነካና የእምነት ወኔን በሚቀሰቅስ መንፈስ እየዘመርን ወጣን። በጌታ ያገኘኋቸው እህት ጓደኞቼ አደይ አበቦችና የሚበሩ ሻማዎቻቸውን ይዘው እየዘመሩ እንደተቀበሉን አሁንም በሁለት ረድፍ ቆመው በደማቅ ሁኔታ እየዘመሩ ሸኙን። በአገራችን የመስከረም ወር ሜዳ ሸንተረሩ እንኳን ሳይቀር በመስቀል አበባ የሚያሸበርቅበት ወቅት ነበር። ከቤተ ክርስቲያኑ ሥነ ስርዓት በኋላ ለአጭር የሽርሽርና የፎቶ ጊዜ ስንወጣ በውጭ ያሉት ተክሎችና አበቦች በላያቸው ያረፈባቸው ጤዛ ከፀሐይ ብርሃን ተቀላቅሎ እንደ ዕንቁ ሲብለጨለጩ ልዩ ደስታና የመጽናናት መንፈስ ሁለንተናዬን አጥለቀለቀው! አዎን! የኛም ሕይወት የሚያብበውና እንደ ውድ ዕንቁም የሚያንጸባርቀው መስቀሉን ተሸክመን መከራን ታግሠን ካለፍን ወዲያ ... ከፅንአት በስቲያ ነው! አልኩኝ በውስጤ!

በታቀደው ፕሮግራም መሠረት ሁሉ በመልካም ተጠናቆ እንደ አገራችን ባህል የዳቦ ስም ቀርቦ እንደተለመደው የስም ዓይነት መደርደር ተጀመረ። እንደ ባህላችን የዳቦ ስም የሚወጣው በባል ዘመዶች አለመሆኑ ሳያንስ ጥበቡ ግን "ዐሥራቴ" ተብዬ እንድጠራለት የመረጠልኝ ስም በድምጽ ብልጫ አሸነፈ። ግራ ያጋባቸው ቤተሰቦቻችን ስለዚህ ስም ክርክር አቀረቡ። የጥበቡም መልስ፡-

"እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ለአምላካቸው የሚያቀርቡት አሥራትና በኩራት እርሱ ከባረካቸውና ከሰጣቸው ከሁሉ የተመረጠውን እንከን የሌለውን ስጦታ እንደሆነ ሁሉ እኔም ለአምላኬ የማቀርበው አሥራቴ እርሱ የሰጠኝን ሚስቴን ነው፤" የሚል ነበር።



የሠርጋችን መልስ መስከረም 12 ቀን 1968 ዓ.ም

በሠርጋችንም ዕለት ካዩትና ከሰሙት መንፈሳዊ እውነት የተነሳ የብዙዎች ዘመዶቻችን አመለካከት ተቀይሯል። "የጴንጤዎች ሠርግ እንዲህ ደስ የሚያሰኝ መሆኑን መች አወቅን!" ከማለት አልፈው፡- "በእናንተ መካከል ያየነው ሕይወት ፍቅርና ሰላም እኛም እንዲኖረን እንፈልጋለን" በማለት ጌታን እንደግል አዳኛቸው የተቀበሉ እንዲሁም ለወንጌል ልባቸውንና ጆሯቸውን ከዚያን ቀን ወዲህ የከፈቱ ነበሩ።

****

*"ኃጣዊን ደህና ነች?"*

*"ይቺ ሴት የፀነሰቺውን ፅንስ መሸከምም ሆነ በሰላም መውለድ ስለማትችል ሕይወቷን ለማትረፍ ባስቸኳይ ፅንሱን ላስወርድላት ያስፈልጋልና አሁኑኑ ሆስፒታል መተኛት ይኖርባታል"*

አለ ረባውዲ በመሰኘት ይታወቅ ነበረው የዘመኑ የሕክምና ባለሙያ፡- ይህን መርዶ የሚነግረው የምርምሩን ውጤት ለመስማት በጉጉት አጠገቡ ተቀምጠው ለነበሩት ባልና ሚስት ነበር። ጣሊያናዊው ሐኪም ረባውዲ ይሠራ የነበረው በአዲስ አበባው የራስ ደስታ ሆስፒታል ውስጥ እንደ አገራችን አቆጣጠር በ1940 ዓ.ም. ነበር። ይህ አስደንጋጭና ያልተጠበቀ መርዶ በሐኪም ረባውዲ የሚነገራቸው የ37 ዓመት ዕድሜ የነበረው አባቴ አቶ አንናፍር ሠይፉና ኃይለኛ ንፋስ ቢነሳ የሚወስዳት የምትመስለው ቀጭኗ የ18 ዓመት ቆንጆ ወጣት እናቴ ወ/ሮ አልማዝ እንግዳወርቅ ነበሩ!! ምንም ገና ጨቅላ ብትሆን በእናቴ ውበትና ደምግባት የተሳቡ የብዙ ወንዶች አማላጆች ወላጆቿን አባቹ እንግዳወርቅ ገብሬንና ወ/ሮ አስለፈች ደምሴን ደጅ ጠንተዋል። አባቴ ግን የእናቴ ዘመዶች ተወዳጅ ጓደኛቸው ስለነበር ስለ እርሱ መልካም ሰውነት የተገኘው ምስክርነት (በዘመድ ስለገባ) አመዘነ። ትልቅ የዕድሜ ልዩነት ቢኖራቸውም እናቴ በሠርግ የተዳረችለት ገና የ14 ዓመት ትንሽ ልጅ ሳለች ነበር!! በተጋቡ በዓመቱ የመጀመሪያ ልጃቸውን ታላቅ ወንድሜን ገብሩ አንናፍርን ያለምንም ሐኪም እርዳታ ቤቷ በሰላም ተገላግላለች።

ይህ ከሆነ ከሦስት ዓመት በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ስትፀንስ ምግብ አልረጋ ይላታል። ሊያማክሩት ቢሄዱ ነው ሐኪሙ ረባውዲ (በወላጆቹ መካከል ያለውን የዕድሜና የክብደት ልዩነት በማየት ብቻ ይመስላል!) ያን አስደንጋጭ ዜና የሚነግራቸው። ስለዚህ በእርሱ ግምትና አስተሳሰብ ከግዙፉ አባቴ የተፀነሰው ፅንስ ግዙፍ ሆኖ የቀጭኗንና የትንሿን እናቴን ሕይወት እንደሚያሳልፍ እርግጠኛ ነበር። ከዚያም በላይ ያቺን ትንሽ ልጅ ለዚያ ትልቅ ሰው ስላጋቡትም ወላጆች፡- "የአበሻ ራስ ቀርቀሮ! የአበሻ ራስ ቀርቀሮ!" በማለትም ያፍ አላፊ ሁሉ ተናግሯል። "ባለአእምሮው ሐኪም ረባውዲ" ግን አስቸኳይ እርምጃ ለመውሰድ እጅጉን ተጣድፏል። ይህን የተመለከተው አባቴም ልጁንና ሚስቱን አሳልፎ ከመስጠቱ በፊት፡- "እሺ መልካም፤ ያልከውን አደርጋለሁ። ከዘመድ ተመካክረን ቤታችንን አስተካክለን ወዳንተው እንመጣለን"፤ ብሎት ተሰናብተውት ወደ ቤት ይመለሳሉ። ወዲያውኑ ሐኪሙ ያላቸውን ለቤተሰቦቻቸውና ለዘመድ አዝማዱ ሲያማክሩ የብዙዎቹ መልስ፡-

> *"እንደ እርሱ ሐኪም እንጂ እግዜር አይደል? የመጀመሪያ ልጅሽን በሰላም ወልደሽ አሁን እርሱ እንዲህ ቢል ማን ያምነዋል? ዝም በይ አትረበሺ! . . . መድኃኒዓለም አለ!! ... እንዲያውም ሁለተኛ የሐኪም ረባውዲን ዓይን አታዩውም! . . . ባይሆን ምጥ ሲይዝሽ እንዲረዱሽ፤ ያኔ ብቻ የሆስፒታሉን ደጅ ትረግጫለሽ እንጂ! ፈጽሞ ይህን ፅንስ አታስወርጂም! አይዞሽ!!"* በማለት የባባቹውን እናቴን አረጋጉት።

አባቴ ግን የልቡን *ሥጋት* እንዳታውቅበት ለእናቴ ጥንቃቄ ቢያደርግም ሐኪም ረባውዲ በተናገረው ነገር እርሱም በውስጡ ተደናግጧል። ስለሆነም በተቻለው መጠን የጤናዋን ሁኔታ በቅርብ ሁኖ ለመከታተል ወሰኗል። አባቴ በዚያን ወቅት በሥራ ሚኒስቴር ውስጥ ስለነበር የሚሠራው ከአዲስ አበባ ውጪ በሚወጣበት ጊዜ ሁሉ ለዘመድ ለወዳጁ የእናቴን ነገር አደራ ሰጥቶ የመሄድ ልማድ አበጅቷል። አሁን ደግሞ የመውለጃዋ ወር ስለገባ በጥቂት ቀናት ውስጥ ፈቃድ ወስዶ አብሯት

የመሆን ሃሳብ አለው። ዛሬ ግን በዚህ ረቡዕ ማለዳ አባቴ በጊዜው የአበልቲ ድልድይ ሥራ ኃላፊነት ስለነበረበት በሁለትና በሦስት ቀን ጊዜ ውስጥ ደርሶ ለመመለስ ተነስቶ ሄዷል።

እናቴ ምንም እንኳን ድርስ እርጉዝ ብትሆን ዛሬ ያለወትሮዋ እጅግ የቀለላት ቀን ነው! እቤት ውስጥ ከአንድም ሁለት ሠራተኞች አሏት። እንዲያጫውቷትና አብረዋትም እንዲሆኑ ተብሎ የእናቴ ታናሽ እህት ያባቴ የወንድሙ ሴት ልጅ... አሉ። ጠዋት ከረፋፈደ በኋላ፥- "ዛሬ የጽዳት ቀን ነው። ቤት ማጽዳትና ያበሻ ልብሶቼን ማጠብ እፈልጋለሁ" አለቻቸው እናቴ።

"አንቺ እረፊ እኛ እናደርገዋለን" ብትባልም እናቴ በዘጠኝ ወር የእርግዝናዋ ዘመን ሁሉ እንደዚያን ቀን ደስ ደስ ያላትና የቀለላት ቀን አልነበረም። በእርሷ አስተባባሪነትና መሪነት ቤቱ ሲጸዳና ልብሱ ሲታጠብ ዋለ! በቤተሰብ ሁሉ ዘንድ የዘንድሮው የእናቴ እርግዝና እጅግ ስለ ተፈራ ሁሉም ስጋቱን በየልቡ ሰውሮ በተጠንቀቅ የቆመበት ጊዜ ነበር። በዚህ ቀን ግን በእናቴ ውስጥ ተቀብሮ የነበረው ስጋት እንኳን ደብዛውም ስለሌለ ደስተኝነትና ጤነኝነት ይታይባታል!

በዚያን እለት ሁለቱም ሴት አያቶቼ (የእናቴና የአባቴ እናቶች) ውሎዋን ሊያዩ መጥተው በየበኩላቸው የተሰማቸው ነገር ያለ ይመስል፥- "ልደርልሽ አልማዜ" ቢሏት "አይ! እኔ በጣም ደህና ነኝ! እንደዛሬም ጤና ሆኜ አላውቅ! "ብላ ሸኘታቸው ጊዜው አሁን ጨላልሟል። ከእራት በኋላ ደከከሚቸው ተኝተው ሳለ ግን እኩለ ሌሊት ላይ ድንገት እናቴ ብርድ ብርድ ሊላት ይጀምራል! በዚህ ሌሊት ቤት ውስጥ ያሉት ከእናቴ አንስቶ ሁሉም ልጆች ናቸው። አልጋዋ ላይ ሳለች "ብርዱ" እስኪለቃት ዙሪያዋን ከበው ሲያጫውቷት እናቴ "ብርድ" የመሰላት ስሜት ድንገት ወደ ምጥ ሲለወጥ ሁሉም ይደናገጣሉ!

ጎረቤታችን የነበሩ አጥር ብቻ የሚለየን ከወላጆቼ ጋር እጅግ የሚዋደዱ ዘመዶቻችን ከቅርበታቸውም የተነሳ አባቴ ልዩ አደራ የሰጣቸው ቤተሰቦች አሉ። እነርሱም ከእናቴ ጋር አብረዋት ለሚውሉት ለትንሿ አክስቴና ለሌሎቹም ሁሉ የሰጡት ማስጠንቀቂያ ቢኖር፥- "አልማዜ ምጧ ከመጣ ሆስፒታል መውለድ ስለሚኖርባት ቀን ቢሆን ሌሊት ውድቅት ላይ እፍታም ሳትቆዩ ወደ እኛ እንድትሮጡ አደራ!!" የሚል ነበር። እናቴ ምጥ እንደያዛት ነገሩ ሲገባቸው የተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ትዝ ይላቸውና አጠገቧ ከነበሩት መኻል እርዳታ ፍለጋ ሩጫ ወደ ቅርቦቹ ጎረቤቶቻችን ይሆናል!

ሳታውቀው በድንገተኛ ምጥ የተያዘቺው እናቴ ሆስፒታል የሚወስዷት ዘመዶቿንም ሳትጠብቅ አልጋዋ ላይ እያለች ሐምሌ 28 ሌሊት 1940 ዓ.ም. በሰላምና በጤና ሁለተኛ ልጇን እኔን ተገላገለች! እናቴንም ጨምሮ ሁሉም ልጆች ስለነበሩና አዋልደው ስለማያውቁ በዓይናቸው ፊት ስለተወለድኩት ህፃን የሚያደርጉት ግራ ገብቷቸዋል። ትዝ ሲላቸው ሰዎች ስለዕትብት አቆራረጥ ሲነጋገሩ በጨረፍታና በተባራሪ የሰሙት አለ። ስለዚህ አሁን እትብቴን ስለሚቆርጡበት ቦታ በመመካከር ላይ ናቸው። በዚህ መኻል ነበር በእንቅልፍ ልባቸው የእናቴን በምጥ መያዝና "የቶሎ ድረሱ" መልእክት ጎረቤት ዘመዶቻችን የተነገራቸው። እነርሱም ሐኪም ረባውዲ ያወጀባት የሞት አዋጅ ትዝ ብሏቸው ልብሳቸውን እንኳን በቅጡ ሳያጠልቁ ደረታቸውን እየደቁ፥- "ወየው አልማዜ! ወየው አልማዜ! ጉድ ሠራሽን! አደራችንን በላን!..."

እያሉ ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ እያለቀሱ ወደ ተኛችበት ክፍል ሮጡ!! የአራስ ሕጻን የለቅሶ ድምጽ የሚያሰማቸውን ጆሮአቸውን ማመን አቃታቸው! እየተብረከረኩ እናቴ ወዳለችበት አቅጣጫ ቢሮጡ እውነትም የሰሙት የአራስ ሕፃን ድምጽ ብቻ አልነበረም!! እናቴ እንዲያ

የተፈራውን እርግዝናዋን በሰላም ተገላግላ ጭራሹኑ የልጇን ዕትብት ለመቁረጥ አብረዋት ከነበሩት ልጆች ጋር በምክክር ላይ ሆና አገኙዋት እንጂ! በዚህ ጊዜ ነበር በቤታችን አጥልቶ የነበረውን የሞት ጥላ የእግዚአብሔር ምሕረት ስለገፈፈው ዋይታው ወደ እልልታ ልቅሶውም ወደ ደስታ የተለወጠው!!

በፍጹም ጤንነትና የወላጆች ፍቅር አድጌ በእግሬ ድክ ድክ ማለት ስጀምር ሰውነቴ ድምቡሼ ወፍራም ሆኖ ስራመድ ዱን ዱን.... ስለምልና ጉድ ጉድ ማለት ስለማበዛ "ዱንዬ" የሚል የቤት እንዲሁም በአባቴ አያት ስም ደግሞ "ማሚት" የሚል የውጭ ስም እንደወጣልኝ ወላጆቼ ነገረውኛል። ዘመድ ሲሰባሰብ ከልጅነት ለዛዬ የተነሳ ለአፋጪዋችነት እፈለግ ነበር። በእናቴ ሆድ ውስጥ ከተረከገዙኩበት ጊዜ አንስቶ ታሪኬን የሚያውቁ ሁሉ ከሐኪም ረባውዲ እጅ ተርፌ ለዚህ መብቃቴ ያስደንቃቸው ነበር። በተወለድኩ በአምስት ዓመቴ አባቴ በአገረ ገገርነት ከፋ ክፍለ አገር ጨና በምትባል ስፍራ ስለተመደበ ቤተሰቡንና ጓዙን ከአዲስ አበባ ይዞ ለመንቀሳቀስ ወሰነ።

ከዘመድ ወዳጅ መለየቱ ለወላጆቼ ከባድ የነበረ ቢሆንም ታላቅ ወንድሜንና እኔን ይዘው ኑሮአቸውን ለመምራት ወደ ጨና ሲወርዱ ከአዲስ አበባ ኑሮ የመለየቱ ነገር የልጅነት አእምሮዬን አላስጨነቀውም። በዚያ ስፍራ የመንግሥት ትምህርት ቤት ስላልነበረ አንድ የቄስ አስተማሪ እግቢያችን ውስጥ በመቅጠር እኔና ወንድሜ እንዲሁም ፊደል ለመቁጠር ዕድሜያቸው የደረሰ የአካባቢው ልጆች ሁሉ የምንማርበት የግማሽ ቀን የቄስ ትምህርት ቤት አባቴ አቋቋመ።

የኔታ በግዕዝና በቃል የሚያስደግሙን ሁሉ ትርጉሙ አይገባኝም። ይገፔ የቀረሁትና ከልጅነት አእምሮዬ ትዝታው ያልጠፋው "ኃጣዊን" የሚለው ቃል ነው። አንዴ ከቦንጋ (የከፋ አውራጃ) የመጡ የአባቴ ጓደኛ "ኃጣዊን" ካልኩ በኋላ ወደ ቤት ለመድረስ የማደርገው ሩጫ አስቋቸዋል፤ ከዚያ ወዲህ ስለኔ ደህንነት ወላጆቼን ሲጠይቁ "ኃጣዊን ደህና ነች" ይሉ ነበር። በዚህ ወቅት የማልረሳው የልጅነት ትዝታ አለኝ።

ከየኔታ የማለዳ ትምህርት በኋላ የንባብ ችሎታዬን እንዳሻሽል ከእናቴ ጋር የማሳልፈው ጊዜ። እቤታችን ውስጥ ከነበሩት የአማርኛ መጻሕፍት መሀል "የዓለም ታሪክ" የሚል ትልቅ መጽሐፍና ከጥንቱ እንግሊዘኛ ቃል በቃል በጥንት አማርኛ የተተረጎመ መጽሐፍ ቅዱስ ነበር እዘውትራ እናቴ የምታስነብበኝ። የዓለም ታሪክንም ሆነ ሌሎቹን መጻህፍት ሳነብ በቀላሉ ሃሳቡን መከተል ስችል፣ የእግዚአብሔርን ታሪክ የሚናገረው መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሊገባኝ በሚችል መንገድ ስላልተጻፈ ለመረዳት ያስቸግረኝ ነበር። ስለዚህ ይህ መጽሐፍ ለቄሶችና ለትልልቅ ሰዎች ነው እንጂ ለእኔ አይገባኝም ብዬ በመደምደምና ገሸሽ በማድረግ በትንሿ አእምሮዬ ጥግ እንዳስቀመጥኩት አስታውሳለሁ።

ታላቅ ወንድሜ ገብሩ የመደበኛ ትምህርት ቤት ዕድሜው እንዳይተላለፍበት ሚዛን ተፈሪ ከዘመድ ጋር ሆኖ እንዲማር ተላከ። ወላጆቼ ሰስተኛዋን ልጃቸውን ታናሽ እህቴን ስንዱን ስለወለዱ ቤት ውስጥ ብቸኝነት አይሰማኝም ነበር። በ1950 ዓ.ም. አባቴ ጃንጀሮ (አሁን "የም") ወደ ሚባለው ስፍራ በአገረ ገገርነት ሲቀየር እዚያ ከነበረው የመንግሥት ትምህርት ቤት ወላጆቼ እኔንና ወንድሜን አስገቡን። በየኔታና በእናቴ አስተማሪነት ቤት ውስጥ ያሳለፍኩዋቸው ዓመታት ፍሬያማ ሆነው የተሰጠኝን ፈተና በጥሩ ውጤት በማለፌ ሁለተኛ ክፍል እንድገባ ተደረገ።

****

*"ኒሻን" ብዬሻለሁ!*

በአባቴ የሥራ ጸባይ ምክንያት ከቦታ ወደ ቦታ በተቀየረ ቁጥር የልጆቹ ትምህርት እንዳይተጓጎል ወላጆቻችን አሳሰባቸው። ስለዚህ ጅማ ከተማ ውስጥ መኖሪያ ቤት ሠርተው እናታችን በአብዛኛው አብራን እንድትሆን አባታችንም በየእሁድ ቅዳሜውና በየዓመት በዓሉ አብሮን እንዲሆን ወሰኑ። ወላጆቼ ለትምህርታችን ሲሉ መሥዋዕት ያደረጉት ምቾት፣ ፍቅርና እንክብካቤያቸው፣ ድካማቸውም ፍሬ አልባ እንዳይሆን፣ ገና በልጅነቴ ትጋትን ጨመረብኝ። በትምህርት ውጤቴ ወላጆቼን ለማስደሰትና በመልካም ጠባዬም ለማስከበር የምችለውን ነገር ሁሉ ለማድረግ እንደአቅሜ ቆረጥኩ። አባቴ ትጉ የሥራ ሰው በኃላፊነቱም የተመሰገነ ነበር። ለድሃ የሚቆም እውነት ለሆነ ጉዳይ አለቆቹንም ቢሆን እንኳን በሕግ ተሟግቶና ተከራክሮ የሚረታ ሰው ነበር። የሚገባውን ሹመትና ሽልማት ባያገኝም በማንነቱም የሚያከብሩትና የሚወዱት ብዙዎች ነበሩ። ታዲያ አንድ ቀን ትምህርት ቤት ተዘግቶ ዕረፍት ላይ ሳለን የአንደኝነትን ስፍራ በተደጋጋሚ ስላሸነፍኩ ደስ ብሎት እንዲህ አለ፡-

> "በሥራዬ የሚገባኝን ሹመትና ሽልማት ከሰው እጅ ባላገኝ እግዚአብሔር አንቺን ለእኔ ኒሻንና የክብር ሜዳልያ አድርጎ ሰጥቶኛል። ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ "ማሚት" የሚለው ስምሽ ቀርቶ "ኒሻን" ብዬሻለሁ!"

ከዚህ እለት ጀምሮ መጠሪያ ስሜ "ኒሻን" ሆኖ ተቀየረ። ትምህርት ቤት አንድ አስተማሪዬ "አንቺ ስምሽ ሊሻን ነው ኒሻን? አንዱን መምረጥ አለብሽ!" ብለው ቢጠይቁኝ ለእኔ ልዩነቱ ስላልታየኝ "ሊሻን" ነው አልኩዋቸው። ስለዚህ አሁን የምታወቀው "ሊሻን አንጎናፍር" በመባል ነው። ከስሜ በስተጀርባ ያለውን የአባቴን መሻት ላሟላለትና በምችለው ሁሉ እሱን ደስ ላሰኘው ፈለግሁ። እናም ከሰው ጠብቆ በተነፈገው ሹመት ሽልማት ምትክና ካሳ ልሆነው... በውስጤ ወሰንኩ። "አዎን! በተፈጥሮው ቅን ቸርና ቀጥተኛ ለሆነው አባቴ ይህን ላደርግለት ይገባል" አልኩኝ!

ወላጆቼ አቅማቸው በሚፈቅድላቸው ሁሉ ሰዎችን መርዳት እናት አባት ለሌላቸውና ለተቸገሩ ቤታቸውን ክፍት ማድረግ ልምዳቸው ነበር። በቤታችን ማዕድ ዙሪያ የሚቀመጡ ብዙዎች ነበሩ። አባቴ በተፈጥሮው ጨዋታ የሚያውቅ ከዚህ ባህሪው የተነሳ በቤተ ዘመዶቻችንና በጓደኞቹ እጅግ የተወደደና ዘወትር ተፈላጊ ሰው ነበረ። እናቴ ደግሞ አንደበተ ጨዋ ተናግራ ሰው የማታስቀይም ትዳርዋን የምትወድና የምታከብር ታማኝ ታጋሽና ባለሙያ ነበረች። ከዚህ ባህሪዋ የተነሳ ሚስቶቻቸው ከእናቴ ጋር እንዲውሉላቸው የተቻላቸውን ሁሉ የሚጥሩ ባሎች እንደነበሩ ትዝ ይለኛል። ስለዚህ የአባቴን ቸርነት የእናቴን ታጋሽነት ጨዋነትና ባለሙያነት ልቤ ስለወደደው ገና ትንሽ ሳለሁ ጀምሮ በወላጆቼ ዙሪያ መሆን ደስ ያሰኘኝ ነበር።

የወላጆቻችን ባህሪና መልካም ጠባይ በእኛም በወለዱን ላይ መታየት ጀመረ። አንዳንድ ወዳጆቻችን የልጆቻቸው ባህሪ መበላሸት ሲጀምርባቸው ወደ እኛ ቤት እንዲያዘወትሩ ይገፋፉአቸውም እንደነበር አስታውሳለሁ። ጅማ በቡና ሀብቷ የታወቀች በኦሮሚያ ክልል የምትገኝ ከተማ ናት። በጊዜውም አሉ ከተባሉት የኢትዮጵያ ከተሞች መሀል የታላላቅ ነጋዴዎችና ሀብታሞችም መናኸሪያ ነበረች። ከዚህም የተነሳ ወጣቶችን ከትምህርት አዘናግተው ወደ ጥፋት የሚነዱ የመጠጥ፣ የጫት፣ የዳንኪራና የቁማር ቤቶች በታላቅ ፍጥነት እንደ ፍል ፈልተው የተስፋፉበት ወቅት ነበር። ወላጆቻችን የሚሰጡን አጥንትን ዘልቆ የሚገባው ምክራቸውና ፍቅራቸው ከጊዜው የሕይወት እንቅፋት ሁሉ ጠብቆናል።

ስለዚህ በመልክም ምሳሌነታቸው ለእኔ እንደ ሞዴል የሆኑልኝን እነዚህን ወላጆቼን ማስደሰትና ማስከበርን ዓላማዬ አድርጌ ተያያዝኩት። መንግሥት ትምህርት ቤት ከገባሁበት 1950-57 ዓ.ም. በነበሩት ዓመታት ውስጥ 11ኛ ክፍል ደርሻለሁ። ይህም ሊሆን የቻለው ክፍሎችን ደርቦ የማለፍ እድልም ስለተሰጠኝ ነበር። በተለይ 1957 ዓ.ም. ሰኔ መጨረሻ እማርበት የነበረው የቀድሞ ጅማ ሚያዝያ 27 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎቹን ሲያስመርቅ የሆነውን አልረሳም! የክብር እንግዳው የክፍለ አገሩ አስተዳዳሪ ነበሩ። የተለያዩ ሽልማቶች በአንደኝነት ከእጃቸው ስቀበል አባቴን "እንኳን ደስ ያለህ ጃል! በእውነቱ ልትኮራ ገባሃል!" ባሉት ጊዜ አቤት ከፊቱ ላይ ያነበብኩት ደስታ!! አባቴ የትምህርት ደዘታዬንና ጉብዝናዬን ስለተማመነ በተደጋጋሚ፣ "የኔ ልጅ ሐኪም ነው የምትሆነው" ሲል ሰምቼዋለሁ።

ስለዚህ ህልሙን እውን ለማድረግ ዝንባሌዬን ወደ ሳይንሱ ዓለም ለማድረግ በውስጤ ወሰንኩ። በ1957 የትምህርት ዘመኔን ወላጆቼን ባስደሰተና ባኮራ ውጤት ተደመደመ። ያም ብቻ አይደለም! አሜሪካ ውስጥ የአንድ ዓመት የነጻ ትምህርት ዕድል ማሸነፌም የምሥራች ተከታትሎ ደርሶን የቤተሰቤን ደስታ ጨመረልን እንጂ! ስለዚህም ባስቸኳይ ወደ አዲስ አበባ ሄጄ የመጓጓዣ ፓስፖርቴን እንዳወጣና የጉዞ ዝግጅት እንዳደርግ ተነገረኝ!

ነገሩ የሆነው እንዲህ ነበር። በዚያን ዘመን በአገራችን የአሜሪካ የሰላም ጓድ ልዑካን መምህራን (Peace Corps) በየትምህርት ቤቱ የሚያስተምሩበት ዘመን ነበር። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የአሜሪካ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የልውውጥ ፕሮግራም (Exchange Students) ወይንም (American Field Service, AFS) በመባል የሚታወቅ የአንድ ዓመት የነጻ ትምህርት ዕድል ተጀምሮ ነበር። እድሉ የሚሰጠው ለአሥራ ሁለተኛ ክፍሎች መሆኑ ቢታወቅም በትምህርት ጉብዝናዬን ይከታተሉ የነበሩ አሜሪካውያን መምህራኖቼ አደፋፈሩኝ፤ እነሱ የድጋፍ ደብዳቤ ስለጻፉልኝ ውድድር ውስጥ ገብቼ ከኢትዮጵያ በአሸናፊነት ካለፉት ሃያ አምስት ተማሪዎች አንዷ ሆንኩኝ! ለጉዞዬ ዝግጅት ለማድረግ አዲስ አበባ በነበርኩበት ጊዜም ስለ ሰለጠነው ዓለም ስለ አሜሪካ ከመጻሕፍት ካነበብኩትና ከተረዳሁት በላይ በሥራና በትምህርት ምክንያት አሜሪካ ከነበሩ ዘመዶቼ ገለፃ ተደርጎልኛል። "ሥልጣኔን" ለመቅመስም የቤት ልጅነቴ ወደ ኋላ እንዳያስቀረኝ። የአሜሪካ ወጣቶች የደረሱበት ለመድረስ ክፍትና ፈጣን መሆን እንደሚገባኝ ጥብቅ የሆነ ምክር ተሰጥቶኛል። በእናቴ ማሕፀን ውስጥ ሳለሁ በዚያ ጣሊያናዊ በሐኪም ረባውዲ ውርጃ ሆኜ ከመቅረት አምልጬ ለዚህ ቁም ነገር መብቃቴ ለብዙዎች ድንቅ ነበር። ደስ በተሰኙትና ታሪኬን በሚያውቁት ዘመድ አዝማዶቼ እንዲሁም በወላጆቼ በተወለድኩ በ17 ዓመቴ ወደ አሜሪካ ሽኝት ተደረገልኝ።

****

## *ከውርጃ አምልጦ አሜሪካ!*

ከሃያ አምስታችን ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች መኻል አምስታችን ሴቶች ስንሆን ከዚህ ውስጥ ሶስቱ ሴቶች የአዲስ አበባ ወጣቶች፣ ሁለታችን ደግሞ ከጅማና ከአስመራ ነበርን። በዘመዶቼ የተነገረኝ "ስልጣኔና ቅልጥፍና" ዓይነት በተለይ በሁለቱ የአዲስ አበባዎቹ ወጣት ሴቶች በግልጽ ይታያል (በአለባበሳቸው፣ በደፋርነታቸው በተቀላጠፈ እንግሊዘኛ የመናገር ችሎታቸው ወ.ዘ.ተ.)፤ ሶስተኛዋ የአዲስ አበባ ልጅ ግን ጭምትነትዋንና የምትለብሳቸውን ረገፍ ቀሚሶችዋን ተመልክቼ

በእኔ በጅማዋ ልጅ አስተያየት እንኳን፣ "የከተማ ባላገር" አድርጌ መዝግቤያታለሁ። ስለዚህም ለ"ስልጣኔዬ" የሚረባኝ ትምህርት እንደማላገኝባት ቆጥሬ በተቻለ መጠን ከእርሷ ጋር የሚኖረኝን ግንኙነት በልኩ ለማድረግ ገና ከአገራችን ሳንነሳ ወሰኛለሁ። ትምህርቴንና መልከም ጠባዬን በሚመለከት ወላጆቼን ደስ ለማሰኘት እስከዛሬ ጥረት አድርጌአለሁ። አሜሪካ ደርሼ ስመለስ ደግሞ የሰለጠነውን ዓለም አንጸባራቂ "ስልጣኔ የገባት ወጣት" ሆኜ ላስመሰግናቸው ከራሴ ጋራ ተስማምቻለሁ።

ይህን ውሳኔዬን በልቤ እንደያዝኩ ከአዲስ አበባ ይዞን የተነሳው አውሮፕላን ካይሮ ከዚያም አቴንስ ግሪክ ይዞን ገባና አዳራችን በዚያ ሆነ። በወጣልን የጉዞ ፕሮግራም መሠረትም ጥንታዊቷን ግሪክንና ታሪካዊ ስፍራዎችን ጎበኘን። ከዚያም ከመላው ዓለም ይህን ስኮላርሺፕ ያገኙት ወጣቶች ወደ ሚሰባሰቡባት ወደ ሆላንድ ተጉዘን ወደ አሜሪካ የሚያጓጉዘንን መርከብ ለመያዝ ሮተርዳም ገባን፤ ሆላንድ ሮተርዳም ላይ ያሳፈረቻቸውን ወደ ሺህ የሚጠጉ ወጣቶችን መርከቧ ተሸክማ ኒውዮርክ አሜሪካ ስትደርስ ለማራገፍ ረጂሙን የአትላንቲክ ውቅያኖስን ጉዞ ተያያዘችው!! ከአዲስ አበባ ከለቀቅንበት ዕለት አንስቶ እግረ መንገዴን እስከ አሁን እንኳን ዐይኖቼ ባዩት የሥልጣኔ ምጥቀት ተገርሜያለሁ። በልቤ "ታላቋ አሜሪካ" እስከደርስ ቸኩያለሁ። ሆኖም ግን የተቻኮለውን ልቤን ፍጥነቱን የሚቀንስ "ልጓም" መርከብ ውስጥ ሳለሁ ገጥሞኝ ከዚህ ልጓም ለማምለጥ የውስጥ ግብግብ ተያያዝኩ!

ከዘጠኝ መቶ በላይ የነበርነውን ያን ሁሉ ወጣት ያካተተችው ያቺ ታላቅ መርከብ ማይ ሰቨን ሲስ (My Seven Seas) ትባላለች። መርከቢቷን ከረገጥኩባት ደቂቃ አንስቶ (መርከብ ላይ ስወጣም ሆነ ስጓዝ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው) መደነቅ ይዞኛል! ከተለያዩ ክፍላተ ዓለማት የመጡ ከ17-20 የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ትኩስ ኃይል የሚነዳቸውን ወጣቶች ጭናለች። መርከቧ ከወደቡ ልትንቀሳቀስ ስትጀምር የ"ደህና ግቡ" እጆቻቸውን ለሚያውለበልቡት ተሰናባቾቻችን ምላሽ ለመስጠት፣ ወጣቶቹ በሚዘምሩት መዝሙር ትናጣለች! መርከቢቷ ሁሉን የምታስተናግድበትና የምታዝናናበትም በቂ ስፍራም እንዳላት ስገነዘብ ገርሞኛል! ከዚያ ሁሉ በላይ የገረመኝ ግን በመርከቧ ውስጥ የመኝታ ክፍሎች ሲደለደል እኔ ለተመደብኩበት የመኝታ ክፍል የወጣውን የስም ዝርዝር ስመለከት ነው።

ከርሷ ጋር ያለኝን ግንኙነት በልኩ ለማድረግ ከወሰንኩባት ከዚያች ከአዲስ አበባዋ ልጅ ጋር አንድ መኝታ ቤት ተመድበናል! በክፍሉ ውስጥ ከተደለደልነው አራት ልጃገረዶች መኻል ሁለት ነጮች ከሁለት የተለያዩ አገሮች ሲሆኑ እኛ ሁለታችን ግን ከኢትዮጵያ ነን። እንዲያውም አልጋችን ታችና ላይ ሆኖ። በአንድ ክፍል ውስጥ ለሚቀጥሉት 12 ቀናት አብረን እያደርን ለመጓዝ ከእስዋ ጋር መመደባችንን ተረዳሁ! ከዚያ ሁሉ ወጣት መኻል ልርቃት ካሰብኩዋት ከዚች ልጅ ጋር መመደቤ አስገረመኝ! ሁኔታው ካስገደደኝ አይቀር ለሰለጠነው ዓለም ራሴን በማዘጋጀት ላይ እንደመሆኔ መጠን፣ እርሷንም በምችለው ሁሉ ልረዳት አሰብኩ!

ስሟ "እምነት አርዓያ" ይባላል። በባሕርይዋ ባነጋገርዋ ካየኋቸው ወጣቶች ሁሉ የሰከነና የረጋ መንፈስ የሞላባት ልጅ መሆኗን ከመቀበል ለማምለጥ አልቻልኩም። እውነቱን ለመናገር ከአገሬ ከወጣሁባት ዕለት አንስቶ የወላጆች ቁጥጥርና ምክር በሌለበት ሁኔታ ዙሪያዬን የከበቡኝ ወጣት ወንዶችና ሴቶች የሚያደርጉትን ማየቴ አስደንግጦኛል! "በእርግጥ ከአገሬ ስነሳ የአሜሪካውን "ሥልጣኔ" ለመቅሰም ራሴን ክፍት ለማድረግ ወስኜያለሁ። ቢሆንም እኮ የትምህርቱን ግስጋሴና

የተመሰገነውን መልካም ጠባዬን ከሚያኮላሽ ነገር ሁሉ የመራቅ አቋሜን መሻር የለብኝም" ስል ከልቤ ጋር መክሬያለሁ። ራሴን እስከጠበቅሁና እስከተቆጣጠርኩ ድረስ የሰለጡኑት ወጣቶች የሚሆኑትንና የሚያደርጉትን ከርቀት ለመሰለል ደግሞ ልቤ ፈልጓል። በአብዛኞቹ ባህልና አስተዳደግ የእድገት ደረጃ እንጂ ነውር ተብሎ ስለማይቆጠር፣ በዚህ ዕድሜያቸው ወጣቶች በገሃድ ያለመሸማቀቅ በየሜዳው የሚሆኑትን ሳይ ግን ለራሴም ብዙ አሳስቦኛል!!

በአንጻሩ ደግሞ መርከቢቷ ውስጥ በደረሰኝ የመኝታ ክፍል ለአሥራ ሁለት ቀናት ሙሉ አብራኝ እንድታድር የተመደበቺው የወጣቷ እምነት ነገርም ልቤን ይዞታል። የዚች ጓደኛዬን ማንነት "እስቲ እንግዲህ ካልቀረልኝ ተጠግቼ ልወቀው" በማለት ወስኗል። ይህን ባልኩበት በመጀመሪያው ቀን ግን ስታደርግ የተመለከትኩት ነገር ለእኔ ፍጹም እንግዳና የማላውቀው ጉዳይ ሆኖ ስላገኘሁት ተገርሜያለሁ! መርከቧ ጉዞዋን በጀመረች በመጀመሪያው ምሽት የተመደብነው አራታችንም በመኝታ ክፍላችን ነበርን። የሌሊት ልብሶቻችንን ቀይረን አልጋዎቻችንን ስንይዝ እምነት አልጋዋ ሥር በርከክ ስትል አየኋት። አልገባኝም! አደናቅፏት መሰለኝ በመጀመሪያ! ተደናግጬ "ምን ሆንሽ?" ብዬ ላናግራት ብሞክርም መልስ አጣሁ! እኔ ከላይኛው ድርብ አልጋ ላይ እርሷ ደግሞ ከታችኛው ላይ ነበረች። ጥቂት ጊዜ አልጋዬ ላይ ቁጭ እንዳልኩ መጨረሻዋን ለማየት ብጠብቃትም እንደተንበረከከች ብዙ ቆየች። አልጋዬ ውስጥ ገብቼም ጋደም ብዬ ማሰላሰል ጀመርኩ።

በሃሳቤ ነገሩን እያወጣሁና እያወረድኩ ሳለ እምነት ከተንበረከከችበት ተነስታ አንድ ከበድ ያለ መጽሐፍ ይዛ አልጋዋ ላይ ቁጭ እንዳለች ለረጅም ጊዜ ማንበብ ጀምራለች። "ወይ ግሩም! ይህቺ ደግሞ ምን ዓይነት ልጅ ናት?" ብሎ ጠየቀ እእምሮዬ። ሰሞኑን በተመለከትኳቸው ወጣቶችና በእምነት መካከል ያለው ልዩነት እጅጉን አስገርሞኝ ጥቂት ከሃሳቤ ጋር ቆየሁ። ከሃሳቤ ስነቃ ሁኔታዋን ለማየት አንገቴን ወጣ አድርጌ ቁልቁል ወደ አልጋዋ ብመለከት ያን መጽሐፍ አጥፋ እጠገቧ አስቀምጣው ተሸፋፍና ተኝታለች። መጽሐፉን ልብ ብዬ ሳስተውለው መካከሉ ላይ ወርቃማ መስቀል ያለበት ጥቁር ሽፋን መጽሐፍ ነው። ያ ድሮ ትንሽ ሳለሁ እናቴ ንባብ ስታለማምደኝ ሳለ በጥንት አማርኛ የተጻፈው መጽሐፍ። ስለማይገባኝ ላለማንበብ ገሸሽ አደርገው የነበረው መጽሐፍ ቅዱስ ነው! ስለዚህ እምነት በዚያን ምሽት ያደረገቻቸውን ሁለት ነገሮች ሳገናዝብ የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ሰው (ሚስዮን/ሚሽን) መሆኗን ደረስኩበት።

ስለ ጸሎት የነበረኝ አመለካከት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከነበረኝ አቋም የተለየ አልነበረም። ሁለቱም ጉዳዮች በሰው ልጅ የዕድሜ የመጨረሻ ዘመን አካባቢ ሊኑሱ የሚገባቸው እንጂ ወጣቶችን የሚመለከቱ ናቸው ብዬ አስቤ አላውቅም። በቤታችን ውስጥ ትዝ እስከሚለኝ ድረስ የማውቀው እናቴ "ቤተስኪያን ሳሚ ዳዊት ደጋሚ" በጾም በምጽዋቱ የሚደርስባት የሌላት ነበረች። አባቴ ግን የሃይማኖት መሪዎች ነን ከሚሉት የሚታይ መልካም ምሳሌነት ስላጣ፣ ስለ ሃይማኖት ጉዳይ ብዙም ፍላጎት አልነበረውም! ሆኖም ግን እኛን ልጆችን በተመለከተ በእናቴ ቀስቃሽነት ቤተክርስቲያን እብረናት የምንሄደው ትዝ ይለኛል። በግዕዝ የተጻፉት የማይገቡኝ የጸሎት መጽሐፍቶቿ... ቤታችን ውስጥ ከነበሩን መጽሐፍት መሀል ማንም ሳያነበው ለዓመታት አቧራ ሲጠጣ የኖረው ያ መጽሐፍ ቅዱስ ትዝ ይለኛል።

እናቴ ከምታስደግመኝ ከጸሎት መጽሐፍቶች ውጪ ግን (ጸሎት መሆኑ አልገባኝም እንጂ) የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሳለሁ በሕይወቴ ያደረግሁት አንድ ነገር ደግሞ ትዝ ይለኛል። ጊዜው ከሰዓት በኋላ ነው። እቤታችን ውስጥ የገባውን የፀሐይ ጨረር ለማግኘት ወለሉ ላይ በደረቴ

ተኝቻለሁ። ጥናቴንና የቤት ሥራዬን እዚያው እንዳለሁ ካጠናቀቅሁ በኋላ ድንገት ሳላስበው ስለ እግዚአብሔር አወጣና አወርድ ጀመር። ቀን ላይ ትምህርት ቤታችን ከሚማሩት መኻል "ሚሽን ናት" የምትባል ልጅ ስታዜም የሰማሁት አንድ ዜማ ውስጤን ሞልቶታል። ሳላውቀው መዝሙሩን በተመስጦ ከእንባ ጋር ስዘምረው፣ እንባዬም በተኛሁበት ጣውላ ላይ ሲወርድ አየሁት። መዝሙሩ በእንግሊዝኛ ነበር።

"Into my heart come into my heart oh! Jesus!
Come in today; come in to stay, Dear Jesus!" "ወደ ልቤ ና ወደ ልቤ ኦ የሱስ..." ማለትነው።

በዚያን ሰዓት እንባዬን እያፈሰስኩ መዝሙሩን ስዘምር በውስጤ የፈሰሰው ሰላምና ደስታ ትውስ ይለኛል። ከዚያን ቀን በኋላ ስለ ጸሎት ያለኝ ትዝታ ወይንም ለእግዚአብሔር እንዲህ በቀረበ ሁኔታ ነገሬንና ሃሳቤን መግለጽ የተለማመድኩበት ወቅት የለም። ዕድሜዬ እየጨመረ ሲመጣና ወደ ሁለተኛ ደረጃ ስደረስ ትኩረቴና ዝንባሌዬ ሁሉ ወደ ትምህርቴ ሆኗል። ቤተሰኪያን ሳሚነት ለሽማግሌዎችና ለአሮጊቶች ስለ መሰለኝ፣ ሳረጅ ልደርስበት በዘመኑ መጨረሻ ላይ ላነሳው አንድ ጥግ ሰጥቼዋለሁ።

ታዲያ እምነት ይህን እኔ የደረስኩበትን ግምጋሜ ገና ባትደርስበት ይሆናል ብዬ አሰብኩ። ከእውቀቱ ላካፍላት "ታላቋ አሜሪካ" ሄዳ መሳቂያ ከመሆኗ በፊት ላድናት ይገባል ብዬ በውስጤ ማውጣትና ማውረድ ቀጠልኩ። ሆኖም ግን በመርከቧ ውስጥ ያሳለፍናቸው አሥራ ሁለት ቀናት በብዙ ፕሮግራሞችና በአዳዲስ እንግዳ በሆኑ ነገሮች የተሞሉ ነበሩ። ከብዙ ሌሎች ወጣቶችም ጋር የመተዋወቂያ ጊዜ ነበር። እምነትና መንፈሳዊ ሕይወቷ ውስጤን የሚያስጨንቀው ቀኑ ተዋግዶ ማታ ለመኝታዬ ወደ ተመደብኩበት ክፍል ስሄድ ነው። በዚያ ታላቅ ውቅያኖስ ላይ ሌትና ቀን መሬት የሚባል ሳይታይ ለቀናት መጓዙ ራሱን የቻለ አዲስና ያስደነቀኝም ጉዳይ ነው።

ከመርከቧ ላይ ወጥተን በይናችን ማየት እስከሚችልበት ድረስ በአራቱም ማዕዘን ስናማትር ፍጻሜ የሌለውን ውኃ ስለምናይ ምድር ላይ እግራችን ዳግመኛ የሚረግጥ አይመስልም ነበር! አንዳንዴ እጅግ የሚያናውጥ ማዕበልና ሞገድ ተነስቶ ያቺን ታላቅ መርከብ በአስፈሪ ሁኔታ ሲያንገላታት ከነውጡ የተነሳ ብዙዎች "የባሕር በሽታ" (ፈረንጆች Sea sickness ይሉታል) ይዟቸው ራሳቸውን እያዞራቸውና እያስመለሳቸው ታመው አልጋ ላይ አስተኝቷቸዋል። በእነዚህ ቀናት የተዋወቅኋቸው አንዳንዶች ሲታመሙ የባሕር ነውጡ በሽታ ለነገሩ እኔን ስላልነካኝ ሌሎችን እንኳን የማስታመም ኃይል ነበረኝ።

የእምነት መንፈሳዊ ሕይወት በውስጤ የፈጠረውን ታላቅ ነውጥና ግብግብ ለመቋቋም ግን ጉልበት አጣሁ! መድረስ አይቀርምና እንዲያ በሞገድና በማዕበል ስትንገላታ የሰነበተቹው ያቺ ታላቅ መርከብ በአሥራ ሁለተኛው ቀኗ ከአሜሪካው ታዋቂና ዝነኛ ከተማ ከኒውዮርክ ወደብ ላይ አድርሳ አራገፈችን። በነውጡ ሕመም ለተንገላቱት ለብዙዎች ታላቅ የእፎይታ ጊዜ ነበረ! መንፈሳዊነትንና ጸሎተኝነትን ለሽማግሌዎችና ለአሮጊቶች የመደበው ልቤም፣ በወጣቷ እምነት "ድምጽ የለሽ" መንፈሳዊ እሩምታ እና ቦንብ የሆነ የሕይወት ምስክርነት፣ ሲተረማመስ ከርሟል። በየተመደበልን ስፍራና ቤተሰብ ስንሄድ እስከ ጊዜው ከእምነት የሚለይበትና እፎይ የሚልበት ጊዜም ያገኘ መሰለው።

****

# 5

# ታላቋ አሜሪካ

ከአፍሪካ ከአውሮፓ ከእስያ ከአውስትራሊያና ከኒውዚላንድ ተውጣጥተው የመጡት እነዚያ ሁሉ ወጣት ተማሪዎች በመላው አሜሪካ ልዩ ልዩ ከተማዎች ወደ የተዘጋጁላቸው ቤተሰቦች በተቀላጠፈ ሁኔታ ተሰራጩ! እኔም እስካሁን ድረስ በደብዳቤና በላኩልኝ ፎቶ የማውቃቸውን አሜሪካውያን ቤተሰቦች ለመጀመሪያ ጊዜ በአካል ልገናኛቸው ጉዞዬን ጀመርኩ። ዓመቱን በሙሉ አብሬያቸው እንድሆን ቤታቸውን ከፍተው እጆቻቸውን ዘርግተው ይጠብቁኛል፤ የሚኖሩት ኒውዮርክ ግዛት ቡፋሎ ከተሰኘው ትልቅ ከተማ አጠገብ ከምትገኝ ኦርቻርድ ፓርክ ከምትባል ትንሽ ከተማ ውስጥ ነበር። የተሳፈርኩበት ግሬይ ሀውንድ የሚባለው ትልቅና ዘመናዊ አውቶቡስ ከዝነኛው ኒውዮርክ ከተማ ተነስቶ የመጨረሻ መድረሻ ጣቢያው ቡፋሎ ከተማ ነበር። የሚቀበሉኝ አሜሪካውያን ቤተሰቦቼም በጉጉት የሚጠብቁኝ በዚሁ ከተማ ስለነበር ጉዞዬን ወደ ቡፋሎ ቀጠልኩ። ከተሳፈሩት ተጓዦች መኻል አንድ አካባቢም ባይሆን እንደኔው ኒውዮርክ ግዛት ውስጥ የደረሳቸው ጥቂት ወጣቶች ነበሩ። አውቶቡሱ ጎራ በሚልባቸው ልዩ ልዩ ከተማዎች ሲደርሱ ተሰነባበትን።ረዥሙን ቀሪ ጉዞዬን የአገሪቱን ልምላሜ ንፅህናና ስልጣኔ እያደነቅሁ ቀጠልኩ። ከአገሬ ስነሳ የክረምትና የዝናብ ጊዜ ሲሆን አውሮፓና አሜሪካ ውስጥ ግን የበጋና ከባድ የሙቀት ጊዜ ነው። የፀሐይ ጀንበርም እስከምሽቱ ሦስትና አራት ሰዓት የማይጠልቅበትና ብርሃን



እንደ እናት የሆነችኝ ሚስስ ፍላናጋን



ሞሪን እና ሼረን የአበሻ ልብስ ለብሰው

የሚታይበት ጊዜ መሆኑ እጅጉን አስደነቀኝ።

በመርከቡ ጉዞ ላይ ስሜቴንና መንፈሴን ሲያንገላታው ከከረመው ከእምነት ሕይወት ተለይቼ ዛሬ እምሽቱ ላይ የምገናኛቸው ነጭ አሜሪካውያን ቤተሰቦችስ ደግሞ ምን ዓይነት ይሆኑ? ባደረግነው የደብዳቤ ልውውጥ እንዲሁም በላኩልኝ ፎቶዎቻቸው እንደተረዳሁት የመጀመሪያ በኩር ልጃቸው የዕድሜ እኩያዬ ናት። የእርሷ ተከታይ ሌላ ሴት ልጅ ከዚያ በመካከል የወለዱት አንድ ወንድ ልጅ አለ፤ ከእርሱ በኋላ ደግሞ በተከታታይ የተወለዱ ሁለት ሴት ልጆች ያሏቸው ወላጆች ናቸው። አባትዬው የሳይኮሎጂ ምሁር ሲሆን እናትዬዋ ደግሞ የቤት እመቤት ናት። ኋላ ስንተዋወቅ ጊዜ እንዳይፈጅብኝ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከያዝኩት የእጅ ቦርሳዬ ውስጥ ያስቀመጥኳቸውን ፎቶዎቻቸውን እያወጣሁ ስማቸውንና መልካቸውን አጠናሁ። ወላጆቻቸው ሚስተርና ሚስስ ፍላናጋን ሲሆኑ እኩያዬ ስሟ ሞሪን ተከታይዋ ሼረን ወንዱ ጆን ሁለቱ ትንንሾች ፓትሪሽያና ካትሪን ይባላሉ። ኢትዮጵያ የተለየኋቸው የእኔም ውድ ወላጆች፣ ከነበርነው ከመጀመሪያዎቹ ሦስት ልጆች ሌላ በዓመታቱ መካከል የተጨመሩ ሕይወት የሚል መጠሪያ ስም የወጣላት አንዲት ሴት ልጅ፣ እንዲሁም እንግዳወርቅና ሠይፉ የተሰኙ (በሁለቱ ወንድ አያቶቼ ስም የተሰየሙ) ሁለት ወንዶች ልጆች አፍርተዋል። የእነዚህ አሜሪካውያን ቤተሰቦች ብዛት ከለመድኩትና ካደግሁበት የሚመጣጠን መሆኑ ደስ አሰኘኝ። ያም ሆነ ይህ፣ በባሕል በመልክ በኑሮ የማልመስላቸውን እንግዳ ኢትዮጵያዊት ከአምስት ልጆቻቸው በተጨማሪ ስድስተኛ ልጅ አድርገው እንደ እናትና አባት ሊቀበሉኝ ተዘጋጅተዋል፤ እነዚህን ቤተሰቦች ዓይን ለዓይን ለማየትና ሌላኛውን የሕይወቴን ምዕራፍ በአሜሪካ ለመጀመር ልቤ ቸኩሏል።

ከምሽቱ አራት ሰዓት አካባቢ አውቶቡሱ ቡፋሎ ከቲማ ውስጥ መድረሻ ጣቢያው ገባና ተሳፋሪዎች የእጅ ቦርሳዎቻቸውን እየያዙ ለመውረድ ተዘጋጁ። ከተቀመጥኩበት ስፍራ በመስኮት ስመለከት በትልልቁ በእንግሊዘኛ በተጻፉ "እንኳን ደህና መጣሽ ሊሻን" "እንወድሻለን ሊሻን!"

"WELCOME LISHAN!!"

"WE LOVE YOU LISHAN!!"

የሚሉ ፖስተሮች የያዙ በቁጥር ከሃያ የማያንሱ ሰዎች አየሁ! የደስታ ሲቃ እየተናነቀኝ ባልጠበቅሁት ደማቅ አቀባበል ሊቀበሉኝ ከኦርቻርድ ፓርክ ከተማ ነድተው ከመጡት አሜሪካውያን ቤተሰቦቼና ጓደኞቻቸው ጋር ተቀላቀልኩ።

ኦርቻርድ ፓርክ ከቡፋሎ ከተማ በስተደቡብ ወደ ሃያ ኪሎሜትር ርቀት ላይ ናት። ቤተሰቦቼ የሚኖሩባት ልጆቻቸውና እኔም የምንማርበት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኝባት ከተማ ናት። ምሽቱን ቤታቸው እንደደረስን ጥቂት የመተዋወቅና የመጨዋወት ጊዜ ነበረን። ከዚያን ዕለት አንስቶ አብረን ለአንድ ዓመት የምኖርበትን ቤታቸውንና በውስጡ የሚገኙትን ክፍሎች አስጎበኙኝ። ለአፍሪካዊው አስተዳደጌም ሆነ በጊዜው ለነበረኝ አመለካከት ምድሪቱን ከረገጥኩባት ከዚያች ከመጀመሪያዋ ዕለት ጀምሮ ተደንቄአለሁ። ታላቋ አሜሪካ ግለሰቦች እንኳን ተንደላቀው የሚኖሩባት በንጽህናዋና በዘመናዊነቷ ከገመትኩት በላይ ሆናብኛለች! እኔም ስለ አገሬ የምኩራበት የሥልጣኔ ዘመን ይመጣል ብዬ በውስጤ ተስፋ አደረግሁ። ይህን በልቤ እያብላላሁና "ምን ይሰማቸው ይሆን?" እያልኩ ለቤተሰቡ ያመጣሁላቸውን ያበሻ ልብስና ሌሎችም የባሕል የስጦታ ዕቃዎች አበረከትኩላቸው። እነርሱም በበኩላቸው የተሰማቸውን ደስታና አድናቆት ሳይ ልቤን ደስ አሰኘው! በመጨረሻም እኔም ሆንኩ እነርሱ ስለተዳከምን ከልጆቻቸው መኝታ ቤቶች አጠገብ ለእኔ ለግሌ ወደ ተዘጋጀልኝ ስፊ መኝታ ቤት

ወሰዱኝ። እነዚህ አሜሪካውያን ቤተሰቦች በኑሮአቸው መካከለኛ (ሚድል ክላስ) ከሚባሉት ሲሆኑ የሚኖሩበት ቤትም ሆነ ሠፈራቸው፣ ደስ የሚያሰኝ አካባቢ መሆኑን ከመጀመሪያው ቀን ማግስት ጀምሮ ተረድቻለሁ።

የበጋና የኃይለኛ ሙቀት ወራታቸው ስለነበረ የውጪውን አየር እስክለምደው ጥቂት ቀናት ተቸግሬአለሁ። የተመደብኩባቸው አሜሪካውያን ቤተሰቦች እኔን አገር ለማላመድ የሚችሉትን ሁሉ አድርገዋል። ትምህርት ቤት ከመከፈቱ በፊት ደስ ሊያሰኙኝ ብዙ ፕሮግራሞችን አውጥተው ሳይ ደነቀኝ! የተለያዩ ስፍራዎችን በማስጎብኘት እኔን ከወዳጅ ጓደኞቻቸው ጋር በማስተዋወቅ ሙሉ ጊዜያቸውንና ልባቸውን እንደሰጡኝ አይቼ ደስ አለኝ። የበጋውና የመዝናኛው ወር አልፎ ትምህርትቤት ተከፈተ። አገሬ ሳለሁ አስረኛ ክፍልን በከብር አጠናቅቄ ወደ አሥራ አንድ የተዛወርኩብትን የምስክር ወረቀት ይዤ ነው ወደ አሜሪካ የሄድኩት። ልመደብ የሚገባኝ 11ኛ ክፍል ሆኖ ሳለ ስኮላርሺፑ ለአሥራ ሁለተኞች ወይንም ያን ላጠናቀቁ ስለነበር የአሜሪካው ት/ቤቱ 12ኛ ክፍል እንድገባ ወሰነ። ቀድሞም ቢሆን ክፍል ደርቦ የማለፍ ታሪክ ስለነበረኝ ውሳኔውን በደስታ ተቀበልኩት።

በአገሬ የትምህርት አሰጣጥ ዓይነትና በአሜሪካው መካከል ያለውን ልዩነት አካክሼ የለመድኩትን ጥሩ ውጤት ለማምጣት ነበር ሀሳቤ። ነገሩ ግን ከአቅሜ በላይ ሆኖ ብዙ ሲያንገዳግደኝ ተመለከትኩ። የነጮች ቁጥር ይበዛበት በነበረው በዚህ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የመምህራኑም ሆነ የተማሪዎቹ የአነጋገር ዘይቤም አስቸግሮኝ ነበር። እስኪገባኝና እስካጠናው በመጀመሪያ ላይ ቀላል ሆኖ አላገኘሁትም። የአሜሪካኖቹ የትምህርት ዓይነትም ሆነ የአሰጣጥ ሲስተም ካደግሁበትና ከለመድሁት ውጪ መሆኑ አንድ ችግር ነው። አገሬ ብሆን ኖሮ ለማትሪክ የሚያዘጋጁኝንና አሥራ አንደኛ ክፍል ውስጥ ላጠናቅቃቸው የሚገቡኝን የትምህርት ዓይነቶች አሜሪካ ውስጥ ላገኛቸው አለመቻሌ ሌላው ችግር ነበር። አጥፌ ያለፍኳቸው ዓመታት በትምህርት ውጤቴ ላይ እስካሁን ችግር ባያመጡብኝም እንኳን ለማትሪክ የሚያዘጋጁኝን 11 እና 12 ክፍሎች በአገሬ አለመማሬ ችግር እንደሚያመጣብኝ ገመትኩ። አባቴ "የኔ ልጅ ሐኪም ነው የምትሆነው" እያለ ስለእኔ በትምክህት ሲናገር የነበረውን በማስታወስ እንዴት ሊሆን እንደሚችል ብዙ ያሳሰበኝ ገባ።

****

## "ግልገል አሜሪካውያን"

የአንድ ዓመት ኑሮዬ በአሜሪካ በትምህርቴ ላይ ብቻ ሳይሆን በአመለካከቴና በአስተሳሰቤም ላይ ትልህ የሆነ ለውጥ አስከተለ። አሜሪካውያን ወጣቶችን ለመምሰልና ለመለወጥ ራሴን ክፍት አድርጌ ስለነበር። በዚህ ረገድ ባሳየሁት ትልቅ እርምጃ ብዙዎች የሚያዩኝ ተደንቀዋል። ታዲያ አልፎ አልፎ የመርከብ ላይ ጓደኛዬን እምነትን አስባትና እርሷም ብትሆን ከዚህ የለውጥ ኃይል መቼም አታመልጥም ብዬ በዐይነ ህሊናዬ ልስላት እሞክር ነበር። አሜሪካ ውስጥ የተመደበልን የትምህርት ዓመት ሲያበቃ እያንዳንዱ ወጣት በገባው ውል መሠረት ወደየመጣበት አገር የሚመለስበት ጊዜው እየተዳረሰ መጣ። የትምህርት ውጤቴ እኔ እንደለመድኩት የሚያስደስት ሆኖ አላገኘሁትም። የአሜሪካውን አሥራ ሁለተኛ ክፊል (ሁለተኛ ደረጃን) ስላጠናቀቅሁ ይህንኑ የሚገልፅ ዲፕሎማ ተቀብዬ ወደ አገሬ ለመመለስ ዝግጅት ጀመርኩ።

ዓመት ያህል እንደልጃቸው አድርገው ከኖሩኝ አሜሪካውያን ቤተሰቦቼ የመለያያው ጊዜ ሲደርስ ለሁላችንም ቀላል አልነበረም። ሆኖም ግን መቼ እንደሁ ባይገባንም፣ አንድ ቀን ዳግም

እንደምንገናኝ አሰብን። እስከዚያው ቤተሰባዊ ግንኙነታችንን እንደምንቀጥል ተስማምተን በዚህ ተስፋ እርስ በርስ ተጽናንተን ተለያየን።

በወጣልን ፕሮግራም መሠረት ያ ሁሉ ወደሺ የተጠጋ ወጣት፣ ከመላው አሜሪካ ተጠረቃቅሞ ዋና ከተማው ዋሺንግተን ዲሲ ድረስ መጥቷል። ከዚያም ታሪካዊ ቦታዎችን እንዲሁም የየአገራችንን ኢምባሲዎች ከጎበኘን በኋላ በአውሮፕላን ወደ የአገራችን ልንሠራጭ ተሰባሰበናል። ከመርከብ ጉዟችን ወዲያ ለመጀመሪያ ጊዜ የማያቸውን የአገሬን ልጆች ዋሺንግተን ዲሲ ሳገኝ ሁሉም በአለባበስ በአነጋገር... ተለዋውጦ ከራሴ ጭምር "ግልገል አሜሪካውያን" መስለን ለመተዋወስ ግር እስኪሚለን ደርሰናል። ጓደኛዬ እምነት የሆነቺውን ለማየት እሯሯጥ ጀመር። ከጥቂት ፍለጋ በኋላ ዓይኖቼን ሳማትር ባለባበስዋ ቢሆን በጭምት አነጋገርዋ ካለፈው የተለየ አንዳች ለውጥ ሳታሳይ ባገኛት ከመገረም አልፎ እንደመበሳጨትም አደረገኝ ! የተቀረነው ሴቶች የመኳኳላችን የጌጡና የጆሮ ሎቲው ዓይነት ለታሪክ ሲታይ፣ እምነት ግን ወይ ፍንክች ! ! ሁኔታዋ በጣም ግራ አጋባኝ። ምናልባት አገር እስክንገባ በቀሩኝ ጥቂት ቀናት ውስጥ በምችለው ሁሉ ለለውጥ ላደፋፍራት ከራሴ ጋር ቃል ገባሁ ! ለእኔ በጊዜው የደረስኩበት የመሰለኝ መኳኳሉ መብለጭለጩ፣ ራሴንም እስከ ተቆጣጠርኩና እስከጠበቅሁ ድረስ ለዳንሱና ለጭፈራው መሰለፉ "ሥልጣኔ" ነው። ገና ከአገሬም ሳልወጣ ከተመከርኩት ምክር አንዱ ይሄው ነበር።

ስለዚህ ወጣትዋ እምነት አገር ገብታ ደግሞ መሳቂያ ከመሆኗ በፊት የጓደኝነቴን መሞከር ያለብኝ እኔ ነኝ ብዬ አሰብኩ ! ሆኖም ግን አሁንም ቀኖቻችን በፕሮግራም ብዛት የተሞሉ ስለነበሩ አንዳንድ ምሽት ላይ በሚኖሩን የመዝናኛ /የዳንስ/ ምሽቶች ላይ አብራኝ እንድትሆን ላደፋፍራት ሞከርኩ። ነገሩ የማወቅና ያለማወቅ ጉዳይ ሳይሆን ልጅቷ ፍላጎቱም ሆነ አምሮቱ ጭራሽ እንደሌላት ገባኝ። የእምነት ሁኔታ እጅግ እንደገረመኝ የአገራችንን ጉዞ በሚያስጀምረን ትራንስ ወርልድ አውሮፕላን ከዋሺንግተን ተነስተን ሌጎስ ናይጄሪያ ዐረፍን። ከዚያም በኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን ኢንተቤ ኡጋንዳ በመጨረሻም አዲስ አበባ ገባን ! ዘመድ አዝማዶችንና ወላጆቻችንም ዓመት ሙሉ የተለዩዋቸውን ከአማርኛ ይልቅ እንግሊዝኛ ልቅደም እያለ የሚቸገሩትን፣ የአሜሪካ ቅንጡ ልጆቻቸውን እየተቀበሉ ወደየቤታችን ገባን !

ስለሚቀጥለው የትምህርት ዘመናችን ስንመክር ከአሜሪካ ይዘነው የመጣነው የአሥራ ሁለተኛ መልቀቂያ ዲፕሎማ በቀጥታ ዩኒቨርሲቲ ሊያስገባን እንደሚችል ተረዳሁ። በተለይ እኔ የአገሬን 11ኛ እና 12ኛ ክፍልን ሳልማር የማትሪክ ፈተናንም ሳልወስድ ዩኒቨርሲቲ የመግባቱ እድል በወቅቱ ግሩም መሰለኝ ! ጊዜው ደርሶ ዩኒቨርሲቲው የሚመድበንን ስፍራ ስንከታተል የአገራችንን የማትሪክ ፈተና ያልወሰድነው ከአሜሪካ የተመለስነው ወጣቶች በሙሉ አርትስ ፋኩልቲ (የሕብረተሰብ ሳይንስ ትምህርት) ውስጥ ብቻ እንደተመደብን ተነገረን። የሳይንስ ፋኩልቲ (የተፈጥሮ ሳይንስ) ውስጥ የሚመደቡት የማትሪክ ፈተና በከፍተኛ ውጤት ያለፋት ብቻ ስለሆኑ። በየተመደብንበት መግባት ካልፈለግን ግን ወደየትምህርት ቤታችን ተመልሰን በሚቀጥለው ዓመት ለማትሪክ ፈተና መቀመጥ እንደሚኖርብን ተገለጸልን።

ሆኖም ግን ጂማ የተውኩዋቸውን የክፍል ጓደኞቼን አሁን ደግሞ በሌላ አንድ ዓመት ልበልጣቸው ያጋጠመኝ እድል አጓጓኝ ! የአባቴን ምኞት ላሟላለት ህክምና ለማጥናት የምችለው ሳይንስ ፋኩልቲ ብመደብ ብቻ እንደሆነ አውቃለሁ። ቢሆንም ግን አንዴ ዩኒቨርስቲ ውስጥ እግሬ ከገባ በኋላ ወደዚያ እንዲመድቡኝ እሞክራለሁ ብዬ አሰብኩ። ይሁን እንጂ ነገሩ እንደገመትኩት

ቀላል ሆኖ አላገኘሁትም። በምችለው ሁሉ ብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ ብገባም ከቶ የሚሆን ነገር ስላልሆነ ኀዘኔ ከፍተኛ ሆነ። ሁሉን ሞክሬ አልሆን ሲለኝ የአርትስ ፋኩልቲ ምድቤን ተቀበልኩና የክፍል ድልድሌን ልመለከት ሄድኩ። በወጣው የስም ዝርዝር ላይ የመርከብ ጓደኛዬ እምነት አርዓያ በተመዘገበቹበት ሁሉ እኔም ተደልድዬ አገኘሁት!! ወደ ልጃገረዶች መኝታ ቤት ሄጄ የተሰጠኝን ሰፍራ ሞግዚታችን ሲያሳዩን ደግሞ የእምነትም አልጋ እዚያው እኔው መኝታ ክፍል ውስጥ መሆኑን ተመለከትኩ!! ከዚህች ልጅ ጋር አሁንም አልተላቀቅንም! እንግዲህ የሚለይልን አሁን ነው አልኩ በመገረም።

****

*ሕይወት ምንድነው?*

በመጀመሪያዎቹ ወራቶች ዓለም ልትሰጣት ከምትችለው ደስታና ዝና ወጣትዋ እምነት ራስዋን በግድ ያገለለች መሰለኝ። በዓለም ውስጥ ያለነው ወጣቶች የምናደርገውን ሁሉ ለማድረግና ለመሆን እየጎመጀችና እያማራት በሃይማኖተኝነት ቀንበር ሥር ጎብጣ ሳይቸግራት የምትቆራመድ መሰለኝ። ስለዚህም እኔ ወደምጋብዛት ዓለማዊነት ሠፈር ላፈልሳት ስውርና ግልጽ የሆኑ እጅግ ብዙ ሙከራዎች አደርግ ጀመር። የከተማ ውስጥ ባህታዊ ሆና ያለ ሙዚቃ ያለ ጭፈራና ሆይ ሆይታ ወጣት ዕድሜዋን በኀዘንተኝነት ያሠረቻው መሰለኝ!! የእምነት ግትር አቋም በዛ እንጂ እኔም ብሆን፣ ሥልጣኔና ዘመናዊነት ብዬ በገባሁበት በዚያ ዓለማዊነት ሕይወቴ ውስጥ እኮ፣ የራሴ ወሰን ነበረኝ!! ላልለማመዳቸው በርቀትና በገደብ የያዝኩዋቸው። ዘማዊነትንና ጠጪነትን እንደምጸየፋቸው ገለጥኩላት። በቀረው ግን "ጤናማ በሆነ መንገድ" ራሳችንን ጠብቀንና ተጠንቅቀን በወጣትነታችን እንድንደሰት አግባባኋት። ከዕድሜ እኩዮቻችን ጋር ደስ ሊለን እንደሚገባ በከንቱ ሰብከቴ ለዓለም ኑሮ ላደፋፍራት ሞከርኩ።

ያልገባኝ ግን የሀሰት ፕሮፓጋንዳ እንዲያ የምለፍፍላት ዓለም ያልሰጠቼኝ ልዩ የሆነ አስደናቂ ሰላምና እርካታ በእምነት ሕይወት ውስጥ ሞልቶ መትረፍረፉ ነበር። ሰከናና ተረጋግቶ ያለመናወጥ የተቀመጠውን የእምነትን ልብ የአጥቂ ቆብ ደፍቼ ለማጥቃት ሞከርኩ። እንደሚንሿሿ ጽናጽል የጩኸት ድምፅ በሚያበዛው ሕይወት አልባ ከርከሬና የአነጋገር ስልቴ። ቢቻለኝ ላጠቃ ላውክና የእምነቷን መሠረት ላናጋ ... ታላቅ ጥረት ውስጥ ገባሁ! ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እንዲህ "እስራት" የመሰለኝን የእምነትን ዓይነት ሕይወት የሚመሩ ሌሎች ወጣቶችም መኖራቸውን ተረዳሁ። የእምነት ዝምታ ብዙም የልቤን አውጥቼ ነጥብ በነጥብ እንድከራከር አልፈቀደልኝም። ከአንዳንዶች ጋር ግን "እኔም - እንትኔን እነሱም እንትናቸውን" ይዘው እንዳችን ሌላችንን ለማሳመን ሰፊ የሃሳብ ክርክር የምናደርግበት ጊዜ ነበር። የኋላ ኋላ ግን ደረቅ ከርከሬ ያሰለቻቸው አንዳንድ አስተዋይ እህቶች "የእርሷን ነገር የሚፈታው ጸሎት እንጂ ውይይት አይደለም!" ብለው ትተውኝ ወደ ጸሎቱ አዘንብለዋል!

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሳልወድ በተመደብኩበት ፋኩልቲ ውስጥ ሐኪም የመሆን ሕልሜ ከእኔ እየራቀ በመምጣቱ ለግማሽ ዓመት ያህል ትልቅ ትርምስና አለመርካት ውስጤን ገጠመው። የደስተኝነትና የእርካታ ምንጭ ይሆንልኛል ብዬ የተከተልኩት የያዝኩትና የጨበጥኩት ሁሉ ሲደርቅ አየሁት። ከአሜሪካም አግበስብሼ ያመጣሁት ዓለማዊነትና የሕይወት አመለካከት፣ ውስጤ በመጠውለግ ላይ የሚገኘውን ተስፋ ሊያለመልመው ፈፅሞ አልቻለም። የአባቴን ምኞት ልሞላለት ለተነፈገው ሹመት

ሽልማት ካሣ ልሆነው የነበረኝ ውሳኔ ከእጄ ረግፎ ሲወድቅ ተሰማኝ። በአርትስ ፋኩልቲ ውስጥ ባለው በየትኛውም መስክ ስሰማራ ራሴን ማየት አቃተኝ። በትምህርቴ የገጠመኝን ብስጭት ለመርሳት ደስታን ይሰጡኛል ብዬ የገመትኳቸውን ነገሮች ሁሉ ሞከርኩ። በዓለማዊነቴና በዘመናዊነቴ ደስታን አተርፋለሁ ብዬ የተያያዝኩት የሕይወት አለመለከከት ኪሳራን ኀዘንን ብስጭትንና ተስፋ መቁረጥን ያሳፍሰኝ ገባ! ጓደኝነቴንና አብረውኝ መሆን የሚወዱ "አንቺ ከሌለሽ ፓርቲው /ጨዋታው/ አይደምቅም" የሚሉኝ አላጣሁም። በአለባበሴ በመጋጌጥና በመኳኳል ብዛት የውስጤን ጩኸትና ባዶነት ለመሸንገል ስለምሞክር ከውጭ ለሚያዩኝ፣ ሁሉ የተሟላልኝና ደስተኛም እመስል ነበርና የልቤን ነገር ለማን ላዋየው?

የኔ ሕይወት በእንዲህ ያለ ትርምስና ማዕበል ውስጥ ይናጣል። በጊዜው ገና ያላወቅሁት ትልቅ ኃይል ድምጽ የለሽ እሩምታውን፣ በእምነት አርዓያ ሕይወት አማካኝነት ይለቅብኝ ገባ!! ከማለዳ አንስቶ እስከማታ በካፊቴሪያው በክፍል ትምህርቱም ሆነ በመኝታ ቤቱ እምነት በገባሁበት ትገባለች። ላስተባብለው የማልችለውን የሕይወት ምስክርነትዋን በታላቅ ነውጥ ውስጥ ለምትገኘው ነፍሴ ታስተላልፋለች። ተጨባጭ ማረጋገጫ ፈላጊው ማንነቴ በሌሊትና በቀን ከሚያያት ከዚች ጓደኛዬ ሕይወት ሌላ ምን ማስረጃ ይምጣለት? በብዙ የጓደኞች አጀብና በዓለም ግርግር ውስጥ ነፍሴ ለማግኘት የተንሰፈሰፈችለት እርካታ ደስታ ዕረፍትና እፎይታ ከሰማውን የተከለው እምነትጋ ነው፤ እኔ የሆንኩትን ሁሉ መሆን ጭራሽ አላስፈለጋት ሰው ውስጥ! ይሄን እውነት ከመቀበል ፈጽሞ ማምለጥ አልቻልኩም! እንዲያውም ይግረምሽ ብሎ፣ በውስጧ ከሰፈነው ሰላምና ዕረፍት ጥቂት እንኳን ጨልፋ ብትሰጠኝ እያልኩ፣ የእምነትን ሕይወት በስውር መቀላወጥ ጀመርኩ!!

በዚህ የውስጥ ነውጥና ጩኸት መኻል ነፍሴ መልስ ያጣችላቸው ትላልቅ የሕይወት ጥያቄዎች ያስጨንቋት ገባ። "ሕይወት ምንድነው?"... "ከሞት በኋላ ወዴት?"... "በውኑ እግዚአብሔር አለ"... በተለይ የትምህርቴና የዓለማዬ መተጓጎል ብስጭትጭት ሲያደርገኝ ደግሞ፡ "ከእንግዲህ ለምን እኖራለሁ?".... "ራሴን ብገድልስ?"... ደግሞስ መኖር ካለብኝ "ዘለቄታ ያለው ሰላምና ደስታ ከወዴት ይገኛል? . . ." እነዚህንና እነዚህን ለመሳሰሉ የውስጥ ጥያቄዎቼ መልስ የማገኝ መስሎኝ ዓለምን አሰስኳት። ውጤት አልባ ሆኜ በኀዘንና በጥያቄ የተሞላውን ሰውነቴን በእንቅልፍ ለማባበል ራሴን እሹሩሩ የምልባቸውን ሌሊቶች አልረሳቸውም! አልጋዬ ላይ በመገለባበጥና ሲብሰብኝ በእንባዬ ትራሴን በማራስ ብዙ ሌሊቶች አለፉ። "መጽሐፍ ቅዱስና ሃይማኖት ለሽማግሌዎችና ለአሮጊቶች" የሚለው አቋም... በወጣትዋ እምነት ትርጉም ያለው የሕይወት ምስክርነት ፍርስርሱ ወጣ!! እስካሁን ተጠግቼ የእምነትን ሕይወት እንዳየሁት በውስጧ የሚፈልቀው ቃል ሕይወትና ኃይል የተሞላ ስለነበረ ይገፍ በምቀርበው የክርክር ነጥብ ሁሉ መረታቴን ልቤም ከወቀው ሰነበተ!!

****

*"ለማመን ማየት"*

ቀስ በቀስ ብሶቴንና ምሬቴን የልቤንም ጥያቄዎች ሁሉ ብዙ ከመናገር ይልቅ የማዳመጥ ተሰጥዖ ላላት ለጓደኛዬ ለእምነት በግልጽ እንድነግራት እግዚአብሔር የልቤን ትዕቢት ይመታው ጀመር። እርሷም ከተጠቂነት ወደ አጥቂ ደረጃ መምጣቷ ሳያኩራራት ምድረ በዳውን ሕይወቴን የሚያለመልመውን የክርስቶስ ኢየሱስን ወንጌል ትመሰክርልኝ ገባ። በስሙ ለሚያምኑትና ለተቀበሉትም ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅነትን ስለሚያስገኘው ታላቅ ዜና። ስለወንጌሉ የምሥራች። ስለ እግዚአብሔር ሕልውናና ኃይል። ጥንት በአብርሃም በነቢያትና በሐዋርያት ዘመን ብቻ ሳይሆን ዛሬም በእኛ ዘመን በድንቅና በተአምራት እንደሚሠራ። ድውያንን እንደሚፈውስ። አጋንንትን እንደሚያስወጣ። ሙታንን እንደሚያስነሳ። ሳይታክታት ትነግረኝና አንዳንድ የሚነበበቡ ጽሑፎችም ትሰጠኝ ጀመር። ከዚያም እርሷና በዩኒቨርሲቲው የሚገኙት ጓደኞቻችን ወደ ሚሄዱበት አንድ ጸሎት ቤት አብሬያት እንድሄድ ደጋግማ ትጠይቀኝ ጀመር። በእርግጥ እምነት ምትነግረኝ ሁሉ እውነት ከሆነ ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበል በስፍራው ተገኝቼ በገዛ ዓይኔ ሁሉን ማየት እንደሚኖርብኝ አሰብኩ። በአገራችን "ከምትሰማው ከፊሉን ከምታየው ሁሉን እመን" እንደሚባል ማለት ነው፤ የእኔም አስተሳሰብ ቢሆን "ማየት ማመን" ወይንም "ለማመን ማየት" ነበር። ስለዚህ በእውነት የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ዛሬም ከሠራ ባይኖቼ በማየት ላረጋግጥ አሰብኩ። ከብዙ የተላለፉ ቀጠሮዎች በኋላ እያቅማማሁና እያመነታሁም ቢሆን አንድ እሁድ አብሬያት ወደ ተባለው ጸሎት ቤት ለመሄድ ተስማማሁ።

ቦታው አዲስ አበባ ከሚገኘው ናዝሬት ትምህርት ቤት አጠገብ አንድ መኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥ ነው። በዓይነቱ ከዚህ በፊት ከማውቀው የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ጋር ምንም ተመሳሳይነት የለውም። መኖሪያ ቤት ቪላ ነው። ገና ግቢው መዳረሻ የብዙ ሰዎች የመዝሙር ድምጽ ተሰምቶኛል። እምነትን ተከትዬ ድምጹ ወደሚሰማበት ግቢ ስንገባ አዲስ መሆኔን የተመለከቱ ወደ ውስጥ ገብቼ ወንበር እንድይዝ አደረጉ። ገና ግቢው ከገባን አንስቶ እስከ ውስጠኛው ክፍል የሚታዩት በሙሉ ወጣቶች ብዙዎቹ ዩኒቨርሲቲው ውስጥ የማያቸው ነበሩ። ሌሎችም የማላውቃቸው ወጣት ተማሪዎች መሆናቸውን በማየቴ ተደነቅሁኝ! ግራና ቀኙን ብቃኝ አንድም እንኳን ሽበት ጣል ጣል ያደረገበት በዕድሜው ጠና ያለ ሰው የለበትም! በሕይወቴ ሰምቼ የማላውቃቸው መዝሙሮች በታላቅ ስሜትና ኃይል ይዘመራሉ። በጣም በከፍተኛ ድምጽ እየተጮኸና እየተለቀሰ ይጸለያል። ሁሉም አይቼም ሆነ ሰምቼ የማላውቀው ነገር ስለሆነብኝ ግራ ተጋባሁኝ። የፕሮግራሙ መሪ ጉባኤውን በደማቅ ሁኔታ ያዘምራል። ወጣቶች እግዚአብሔር ስላደረገላቸው ድንቃ ድንቅ ፍጹም እውነተኛነት በሚታይበት እንደበት ይናገራሉ። ያ በልጅነቴ ያልገባኝ "የአሮጊቶችና የሽማግሌዎች መጽሐፍ" ብዬ ከሕይወቴ ውስጥ ያስወገድኩት መጽሐፍ ቅዱስ በሚገርም ዓይነት ሁኔታ እየተተነተነ በትልቅ ኃይልና ሥልጣን ይሰበካል። "እነዚህ ልጆች ምን ዓይነት ትምህርት ቤት ቢገቡና መጽሐፍ ቅዱስን ቢከኑት ነው?" ብዬ ገረመኝ። ሰባኪው በመልዕክቱ ሰው ለኃጢአቱ ሥርየት ለማግኘት ኢየሱስ ክርስቶን እንደግል አዳኙ መቀበል እንዳለበት አስረዳ። ይህን ለማድረግ የሚወስኑ እጃቸውን በማውጣት ተነስተው እንዲጸለይላቸው ወጣቱ ሰባኪ ሲጠይቅ ሰዎች እያለቀሱ ንስሐ እየገቡ እግዚአብሔርን ሲቀበሉ አየሁ።

ለራሴ ግን በዚያን ዕለት ያልገቡኝ ብዙ ብዙ እንግዳ ጉዳዮች ስለነበሩ ከስብሰባው በኋላ እምነትንና ሌሎችንም የማወቃቸውን ለመጠየቅ ወሰኜ ወጣሁ። በተለይ የጩኸቱና የለቅሶው ነገር...

ደግሞ አንዳንዶች ለረዳው ባልቻልኩት ቋንቋ ሲናገሩ (በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተው በልሳን መናገራቸው መሆኑ ሳይገባኝ) መስማቴ... በሌላም በሌላም ብዙ ጥያቄዎች ተሞልቼ ነበር። ምንም እንኳን "ሃይማኖት ለአዛውንት" የሚል አስተሳሰብ ቢኖረኝና ልቤም በብዙ ጥያቄ ቢሞላም ከየሁት እውነት ማምለጥ አልቻልኩም! ያ ሁሉ ወጣት ያየውን እውነት ቢያይ እንጂ እንዲያው በእንከፍነት ዝም ብሎ እንዳልተሰበሰበ ገብቶኛል። ስብሰባው ሲበተን ልቤ የታጨቀውን ጥያቄዬን እንደያዝኩ ወደ መኝታ ቤቴ ስመለስ አጉል ክርክሬን ትቼ እጄንና ልቤን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ትልቅ የአቋምና የአስተሳሰብ ለውጥ ማድረግ እንደሚኖርብኝ ገመትኩ። ይሁን እንጂ የተከተልኳት ዓለም ዋሾ አርቲፊሻልና አታላይ... ለሰው የሚበጅ መድኃኒት የሌላት መሆኗን እያወቅሁ በመጣሁበት በዚህ ጊዜ እንኳን ልቤ መቁረጥ አቃተው። ባልሞት ባይ ተጋዳይነት ከእምነትና ከመሰሎቼ ጋር አደርገው የነበረውን ከንቱ ክርክሬን ለማቆም ጊዜ ፈጅቶብኛል። በዚህ ሁሉ ወቅት ግን ወደዚያ ጸሎት ቤት (የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን በሚል መጠሪያ አሁን የሚታወቀው) በተደጋጋሚ እየሄድኩ የነገሮችን እውነተኝነት ለማረጋገጥ ሙከራ አድርጌያለሁ። እግዚአብሔር ግን በፍቅሩና በምህረቱ እስከ መጨረሻው እንዴት እንደ ታገሰኝ ሳስበው እደነቃለሁ!

እስከዚህ የሕይወቴ ወቅት ድረስ በዓለም ያሉ ወጣቶች ከሚያደረጉትና ከሚሆኑትም እንኳን የሚመስለኝና የሚስማማኝን ብቻ እየለየሁ በከፊል የማድረግ ልማድ ስነበረኝ አሁንም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያንኑ ለማንፀባረቅ ፈለግሁ። የሚስማማኝን ይዤ የማይስማማኝንና ያልገባኝን ትቼ ዓለምንና የመጽሐፍ ቅዱስን እምነት በአንድ አቀናጅቼ መያዝ እችል እንዲሁ በውስጤ ለጥቂት ጊዜ ታገልኩ። ሆኖም ግን የጓደኛዬን የእምነትንም ሆነ ወደዚያ ለጸሎት ቤት የሚያዘወትሩትን ወጣቶች ስመለከት፣ ይህን የመኻል ሠፋሪነት የሚደግፍና የሚለማመድ ሕይወት አልነበራቸውም። ሸምጥጥ ያለ የክርስቶስና ለክርስቶስ የሆነ አቋም ነበራቸው እንጂ!!

****

*ከነውጥ ወደ ዕረፍትና ጸጥታ!*

መጋቢት 1959 በዋለ አንድ ሰበንበት ከጓደኛዬ ከእምነትና ከሌሎችም ጋር ወደዚያ ጸሎት ቤት ለመሄድ ስነሳ ልቤ አሁንም የዓለምን ነገር ቆርጦ ለምወሰን እንደተቸገረ ነው። የመዝሙርና የአምልኮው ጊዜ አብቅቶ መልእክቱን የሚያመጣው ወጣት ስፍራውን ሲይዝ ያቺ ሰንበት እኔን ወደ ልዩ መንፈሳዊ ሕይወት እንደምታሻግረኝ አልጠበቅሁም። እንደ ወትሮዬ በሀሳቤ ወዲያና ወዲህ ልዋዥቅ እንዳልችል ከወጣቱ ሰባኪ የሚወረወረው ነፍስን የሚመረምር የእግዚአብሔር ቃል ውስጤን እያለፈ ሲበረብረኝ አስደነገጠኝ!! ታሪኬን በአደባባይ የሚናገር የውስጥ ሙግቴን ገሃድ አውጥቶ ስለኔ የሚያወራ መሰለኝ። ክርክሬንና ማመንታቴን ጥዬ.. ሳይመሽብኝ እጄንና ልቤን ለአምላኬ እንዳስረክብ ተናገረኝ። የእኔ ነገር የታከታቸው ጓደኞቼ ስለማንነቴ ለሰባኪው የነገሩትም እስኪመስለኝ ድረስ! ለካስ የሚናገረኝ የውስጥን ነገር አራቁቶ የሚያየው እግዚአብሔር እንጂ ሰው አልነበረም! ነፍስና መንፈሴን በሰነጣጠቀው ህያው ቃሉ አማካኝነት የመዳኔ ቀን እንዳያልፍብኝ ሩህሩሁ መንፈስ ቅዱስ ስለ ኃጢአቴ ይወቅሰኝና ንስሀም ገብቼ ከአምላኬ ጋር እንድታረቅ ይመክረኝ ጀመር።

በፊት ሳይገባኝ.. አንዳንዴም በማሾፍ ሰዎች በንስሐና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡ

"ሕጻን ይመስል የሚያለቅሱት ማን ቆንጥጦአቸው ነው?" "...እጉል ስሜታዊነት ነው! . ." እያልኩ ባላወቅሁትና ባልደረስኩበት ጉዳይ በድፍረት ተናግሬያለሁ። አምላኬ ግን በምህረቱና በፍቅሩ ብዛት ታግሶ ሳይቀስፈኝ ለዚያች የመዳኔ ቀን ሲያበቃኝ የእኔም ዐይኖች በተራቸው እንባቸውን ማጉረፍ ጀመሩ!! የሰው ነፍስ በኃጢአቱ ሲወቀስ። ሁሉን ግልጥልጥ አድርጎ በሚያውቀው በኃያሉና በጻድቁ ጌታ በልዑል እግዚአብሔር ፊት የራሱን ማንነት ሲመለከት!! . .እንደ እኔ ላለ ከንቱ የማይገባውን ምሕረት ሊያጎናጽፈው ወዶ እግዚአብሔር አምላክ አንድያ ልጁን ለመስቀል ሞት አሳልፎ እንዴት እንደ ሰጠው ሲገባው... ለካስ ለዚህ ኖሯል የዚያ ሁሉ ለቅሶ ምክንያት!! የጌታ የእግዚአብሔር ምሕረት ለእኔም ይህን እውቀት በዚያች ሰንበት ቢገልጥልኝ እንባዬን ማን ያቁመው? የአምላኬን ይቅርታ ለማግኘት ከብዙ ለቅሶ ጋር እጅግ እየተንቀሰቀሁ እግዚአብሔርን ተማጸንኩት። ስለ ኃጢአቴ ደሙን ያፈሰሰልኝን የነፍሴን መድኃኒት ክርስቶስ ጌታዬን ወደ ልቤ ጋበዝኩት! የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሳለሁ በቤታችን ወለል ላይ ተደፍቼ "ወደ ልቤ ና ወደ ልቤ ኦ የሱስ!" ያልኩት ሁሉ ትውስ አለኝ!! በዓለም ተሯሩጬ አግኝቼና ተለማምጄ የማላውቀው ነገር ወዲያው በሕይወቴ ሆነ!! መለኮታዊና ሰማያዊ የሆነ አስደናቂ ሰላም... ደስታና ተስፋ ... ሁለተናዬን አጥለቀለቀው!! እስከዚያች እለት ድረስ በብዙ ሞገድና ማዕበል ሲነዋወጥ የነበረው ውስጤ እርፍና ጸጥ አለ!!

****

*ከዓለማዊነት ወደ መንፈሳዊነት*

እግዚአብሔርን ለመከተል ከወሰንኩባት ከዚያች ቀን በኋላ የነፍሴ ጠላት ዲያቢሎስ ቁርጤን እስኪያውቀው ድረስ የፈተናውን ዓይነት ሲደረድረው የጀመርኩት የጽድቅ ጎዳና ታላቅ ቆራጥነት እንደሚያስፈልገው መማር ነበረብኝ። በተለመደው የማባበል አቀራረቡ "...የጨሰድሺው እቋም ሳይነካ ከእኛ ጋር አብረሽን ብትሆኚስ? ... በዳንሱ በጭፈራው ባትሳተፊ እንዲያው በስፍራው ብቻ ብትገኚስ? ወ.ዘ.ተ." በሚለው ንዝነዛው ሲያስጨንቀኝ. . ያለቦታዬ ተገኝቼ ምን ያህል ደከማ እንደሆንኩም ተረድቻለሁ። የሚያውቁኝ የዓለም ጓደኞቼ "የሊሻን እንኳን ቀልድ ነው! ... በጥቂት ጊዜ ውስጥ እኛው ካምፕ ትመለሳለች..." እያሉ የለውጤ ነገር ዘለቄታ እንደማይኖረው በከፋ ሲተነብዩብኝ ሁኔታዬን ያዩና የተብሳጩብኝ ክርስቲያን እህቶች ሳይቀሩ እንኳን "...እርሷ የክርስትናው ነገር በውል የገባትም ስለማይመስል መተው ነው..." ሲሉኝ ፊቷን ሳታቀጭምብኝ በፍቅርና በትዕግሥት ይዛ በእግዚአብሔር ቤት በሁለት እግሮቼ እንድቆም ስለ ረዳቺኝ ስለ እህቴ ስለ እምነት አርዓያ አምላኬን ምን ጊዜም አባርከዋለሁ!!

ክርስቶስ ኢየሱስን እንደግል አዳኜ አድርጌ በመቀበል የኃጢአቴን ይቅርታ ከምሕረትና ከጸጋ ሁሉ አምላክ ከተቀበልኩ በኋላ ነፍሴ እንደቀሩት የጽዮን መንገደኞች የድል አርበኛ መሆን ናፈቃት! አሁን የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ሙልዐት ለምን እንደሚያስፈልግ ገብቶኛል! አንድ ምሽት ዩኒቨርሲቲው መኝታ ቤታችን በስተጀርባ እህቶች እጆቻቸውን ጭነው ሲጸልዩልኝ መሻቴና ናፍቆቴ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነፍሴ ተጥለቀለቀች! አዲስ መንፈሳዊ የድል ምዕራፍ በሕይወቴ ተከፈተልኝ! የዓለም አምሮትና ቅራሪ ሁሉ ከውስጤ ተንጠፍጥፎ በእግዚአብሔርና በሕያው መንፈሱ ሁለንተናዬ ተያዘ! ባሸነፈኝ ነገር ሁሉ ላይ አሸናፊ አድርጎ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ሲረዳኝና ኃይል ሲሆነኝ አየሁት! ያ ድሮ በልጅነቴ አልገባ ይለኝ የነበረውን መጽሐፍ ቅዱስ አስተውለውና እረዳውም ዘንድ አምላኬ የልቦናዬን ዐይኖች አበራልኝ! የቃሉ ደጆች ተከፍተውልኝ እግዚአብሔር

አምላክ ለየዕለቱ የሚሆነኝን ምሪትና አባታዊ ድምጹን ያለማምደኝ ጀመር!

ከእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም በመወለድ ከዓለማዊነት ወደ መንፈሳዊነት ከምድራዊነት ወደ ሰማያዊ አገር ወራሽነት የተሻገርኩባቸው የመጀመሪያዎቹ ወራት የፈንጠዝያና የደስታ የቡረቃም ወራት ነበሩ። ሆኖም ግን በምህረቱ ብዛት ልጁ ያደረገኝ ሰማያዊው አምላኬና አባቴ በዘመኔ ሁሉ የሚጠቅመኝን የቤቱን ስርዓትና የፈቃዱን ክቡርነት በማይረሳኝ መንገድ ሊያስተምረኝ ወደደ። ንስር በልስላሴውና በምቾቱ ብዙ የሚነገርለትን ጎጆዋን ከዘጋጀች በኋላ ጫጩቶቻዋን ትፈለፍላለች። ለንስር ጫጩቶች ይህ ጊዜ የምቾትና የደስታ... በእማዬ ንስር ምግብ አጉራሽነት አደን ወጥታ ያመጣቺውን የሥጋ ዓይነት ባፍ ባፋቸው የሚመገቡበት ልዩ ጊዜ ነው!! ሆኖም ግን እማዬ ንስር ለጫጩቶችዋ እንክብካቤ የምታደርግበት የሕፃንነታቸው ወራት እንዳበቃ አንድ ቀን በድንገት የሚገርም እንግዳ ነገር ማድረግ ትጀምራለች። እንደ ምቹ የስፖንጅ ፍራሽ አንዳች ሳይቆረቁራቸውና ሳይጎረብጣቸው ከምግብና ከጨዋታ በኋላ ጣፋጭ እንቅልፋቸውን የሚተኙበትን ያን ግሩም ጎጆዋን ቀስ በቀስ ስታፈራርሰው ይመለከታሉ! ሆን ብላ ምቾት አልባ ካደረገቺው ጎጆዋ ልጆቿን በክንፎቿ ተሸክማ ታወጣቸዋለች። ድንገትም እምዬ ንስር በክንፎቿ የተሸከመቻቸውን ጫጩቶች ወደ ታላቅ ከፍታ እየበረረች ከወጣቻቸው በኋላ ከሰማይ ወደ መሬት ትወረውራቸዋለች! በሞትና በሕይወት መካከል ሆነው፡- "ዋይ ዋይ እምዬ...!! አውቀሽ ነው ወይንስ አምልጠንሽ?" እያሉ የዋይታና የሰቆቃ ጊዜ ውስጥ ይገባሉ! እነዚህ ጫጩቶች ከሰማይ ከፍታ በታላቅ ፍጥነት እየተሽቆለቆሉ በምድር ላይ ተፈጥፍጠው ህይወታቸው ሊፈጸም በሞትና በእነርሱ መካከል አንድ እርምጃ እርቀት ላይ ሳሉ እምዬ ንስር በእነዚያ ሰፋፊና ፈጣን ክንፎቿ እየበረረች ከበታቻቸው ትደርስና ትቀልባቸዋለች! እምዬ አንዳንዴ ክንፎቿን ዘርግታ አየር ላይ በመሰፈፍ ልታሳያቸው ያደረገቻቸው ሙከራዎች በድንገት ትውስ ይላቸዋል! እግዚአብሔር የፈጠረላቸው ትናንሽ ክንፎች እነርሱም እንዳሏቸው አሁን ያስተውላሉ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እነዚህ ጫጩቶች እንደቀሩት ትላልቅ ንስሮች ሁሉ ለህይወታቸው ጠር ከሆነው ከማንኛውም ነገር በላይ እጅግ ከፍ ብለው ወደ ሰማይ በታላቅ ከፍታ ይወጣሉ። ክንፎቻቸውንም በመጠቀም ይከንፋሉ። ኃይላቸውንም በማደስ በምድር ላይ አስደናቂ የሆኑ 120 ዓመታት ይኖራሉ!!

****

# 6

# የጥበቡ ነገር !

አንደኛዋ፡- "እኔ የቄስ ሚስት መሆን ነው የምፈልገው!"
ስትል ሌላኛዋ ደግሞ፡-

"አይ! እኔ ግን የሀብታም ነጋዴ ሚስት መሆን ነው የምፈልገው" አለች።
እግረመንገዱን ባጠገባቸው የሚያልፍ አላፊ አግዳሚ ቢኖር፣ ሁለቱን የታናሽና የታላቅ ልጆች እንዲህ ሲባባሉ በሰማቸው ነበር። ገና ገና ትናንሾች ሆነው ጭቃ እያቦኩ ዕቃ ዕቃ ሲጫወቱ ጆሮውን ጣል አድርጎ ለሚያዳምጣቸው ሲያድጉ መሆን የሚፈልጉትን ነበር በአንደበታቸው ያስተጋቡት።



ጥበቡ ከቀድሞው ንጉሥ አፄ ኃይለሥላሴ ሽልማት ሲቀበል

"ለልጅ ይታየዋል" እንዲሉ፣ ከነዚህ የልጅነት ምኞት ዓመታት በኋላ ሁለቱም እንደየፍላጎታቸው ሰምሮላቸዋል፤ የቄስ ሚስት መሆን ፈላጊዋ መምህር ኃይለሥላሴ ስመኝን ያገቡት ወ/ሮ ፀዳለ ወርቁ የዛሬው ባለ ታሪክ የእኔው ውድ ባለቤት የዶ/ር ጥበቡ ኃይለሥላሴ እናት ናቸው። መምህር ኃይለሥላሴንና ወ/ሮ ፀዳለን በቃል ኪዳን ያስተሳሰረው ትዳር፣ የሁለት ሴቶችና የስድስት ወንዶች ልጆች እናትና አባት አድርጓቸዋል።

ታዲያ የእናቱ የወ/ሮ ፀዳለ ወርቁ ምኞትና ፍላጎት የካህን ሚስት መሆን ብቻ አልነበረም፤ ልጆቻቸው የቤተክርስቲያን አገልጋዮች እንዲሆኑም ጭምር እንጂ። ስለዚህም አብዛኞቹ ወንዶች በድቁና አገልግለዋል። አንዲት ሴትና አራት ወንዶች በየሦስት ዓመት ልዩነት ከወለዱ በኋላ ጳጉሜ 3 ቀን 1939 ዓ.ም. ስድስተኛውን ልጃቸውን ጥበቡ ኃይለሥላሴን ይወልዳሉ። ከጥበቡ

ቀጥሎ አሁንም በየሦስት ዓመት ልዩነት እንዲት ሴትና የመጨረሻውን ወንድ ወልደው የመምህር ኃይለሥላሴና የወ/ሮ ፀዳለ ልጆች ቁጥር ወደ ስምንት ከፍ ብሏል።

ስድስተኛውን ልጅ ሲወልዱ ይህ ሕፃን በምድር ዘመኑ ከሚገበየው ዕውቀት ሁሉ በላይ እውነተኛ ዕውቀቱና ጥበቡ የሥላሴዎች መለኮታዊ ኃይል እንደሚሆንለት የታያቸው ይመስል ስሙን "ጥበቡ" ኃይለሥላሴ ብለው ሰይመውታል። ሕፃኑ ለትምህርት ዕድሜው ደርሶ መድኃኒዓለም ትምህርት ቤት ሲገባ፣ ከዓመት ዓመት የሚያገኘው ውጤት የአእምሮውን ብሩህነት ገሃድ ስላወጣው፣ "የት ይደርሱ ይሆን?" ከሚባልላቸው ታዋቂ ተማሪዎች መኻል አንደኛውና ዋነኛው ሆኗል።

በዚያን ዘመን ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ኃይለሥላሴ ለጎበዝ የአዲስ አበባ ተማሪዎች ይሰጡ የነበረውን ሽልማትና ሥጦታ ጥበቡ በየዓመቱ መቀበል ልምዱ አድርጎታል። ከመላ ኢትዮጵያ ተወዳድረው እጅግ ከፍተኛ ውጤት ካመጡት 25 አሸናፊ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች አንዱ ጥበቡ ስለነበር፣ በዝነኛው ጄኔራል ዊንጌት ትምህርት ቤት ገብቷል። ጎበዞችንና የሃብታም ልጆችን ብቻ ያስተናግድ በነበረው በዚህ ሁለተኛ ደረጃ አዳሪ ትምህርት ቤትም ጥበቡ በሁሉም አቅጣጫ በስፖርትና በልዩ ልዩ ክለቦች ተሳትፎም ሆነ በቀለም ትምህርት ታዋቂነቱ ቀጠለ።

ጥበቡ ክፍል ውስጥ ለሚሰጡት ዐበይት የትምህርት ዘርፎችና በየክለቡ ለነበረው ተሳትፎ ሚዛኑን የጠበቀ ወጣት ሆነ። የወላጆችም ሆነ የአስተማሪዎች ጉትጎታ ያላስፈለገው ጥበቡ ከእኩያ ጓደኞቹ ጋር በቧልትና በቀልድ ጊዜውን እንዲፈጅ ልጅነቱ አላታለለውም። ከቤተሰብ ቁጥጥር ሥር በመራቁ በወጣትነት እጉል ምኞት ራሱን ልቅ የማድረግ ፍላጎት አላሸነፈውም። ስርዓት ባለው ሁኔታ የጨዋታ፣ የምግብ፣ የማጥኛና ሌሎች ትርፍ ነገሮችን የሚያደርግበትን ጊዜና ሰዓት የመስጠት ልማድ ያበጀው፣ ገና ወደ ዘጠነኛ ክፍል ከመግባቱ በፊት ነበር። የፎቶግራፍ ክለብ፣ የጂኦግራፊ፣ የኤሌክትሮኒክስና የሜትሮሎጂ ክለቦችም መሪ ተሳታፊ ነበር። ከስፖርት ደግሞ የውኃ ዋናና የቴኒስ ክለብ ኮከብ ተጫዋች ነበር። ጥበቡ የብዙ ክለቦች ዋነኛ ተሳታፊ ሆኖ ሳለ፣ በየትኛውም ዘርፍ ለሚቀርበው የትምህርት ፈተና ደግሞ አንደኝነትን ለማንም ላይለቅ የቆረጠ ትጉ ተማሪ ነበር።

የዘመኑ ሀብታሞችና "ስልጡን" የተባሉት የዊንጌት ተማሪዎች በትምህርት ቤት ደረጃም ሆነ በየግል ለሚያቀርቡለት የዳንስ ምሽቶችና የፓርቲዎች ግብዣ ጋጋታ ፍንክች ያለማለቱ ጓደኞቹን ይገርማቸዋል። ሮብና አርብ፣ ፍስክና ሁዳዴ ሳይባል መብላት ለሚፈልጉ ሁሉ ስጋውና እንቁላሉ ወተቱና ቅቤው በት/ቤቱ የምግብ አዳራሽ እንደልብ ይገኛል። ጾም አክባሪነቱን የሚያዩ የጥበቡ ኃይለሥላሴ ጓደኞች ግን "የአባቱን የክህነት ሥራ መቀጠሉ ይሆን?" ሲሉ እንዲጠያይቁ አድርጓቸዋል። የክፍል አንደኝነትን ልምዱ ያደረገው ጥበቡ የጄኔራል ዊንጌት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱንም ሲጨርስ በክብር ነበር። የማትሪክ ፈተናን ከመላው ኢትዮጵያ እጅግ ከፍተኛ ውጤት ካመጡት ጥቂት ተማሪዎች አንዱ በመሆን ነበር ያጠናቀቀው። ጎበዝ ተማሪዎች ከንጉሡ እጅ ሽልማት ሲቀበሉ ወላጆቻቸውም በስፍራው እንዲገኙ ግብዣ ይደረግላቸው ነበርና ጥበቡ ቤተሰቡን ያኮራና ደስ ያሰኘ ወጣት ሆነ።

1959 ዓ.ም የከንውንና የከፍተኛ ውጤት ዓመት የሆነለት ጥበቡ፣ የጎበዞቹ ተማሪዎች መናኸሪያ የአዲስ አበባው ዩኒቨርሲቲ የሳይንስ ፋኩልቲ በሩን ወለል አድርጎ ይጠብቀዋል። እስከዚያው ግን በመገባደድ ላይ የሚገኘውን የክረምት የዕረፍት ጊዜውን እያጣጣመ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ጓደኞቹ የሆነ ነገር አግኝቷቸው ወሬያቸው ሁሉ እንግዳ ሆኖበታል። የሚሉት ነገር አይግባው እንጂ ጓደኞቹ በእርግጥ የሕይወት አመለካከታቸው ከመቀየሩ ሌላ ተጨባጭ የሆነ የባሕርይ ለውጥም አይቶባቸው ውስጡን ሲደንቀው ሰንብቷል። ይህ የገጠማቸው አዲስ ሕይወት ወደ እግዚአብሔር

እንዳስጠጋቸው የሚነጋገሩት ጓደኞቹ፣ በእርግጥ በስነ ምግባራቸው ላይ ያመጣውን መልካም ለውጥ ጥበቡ በአንክሮ ታዝቦታል። እርሱ ግን በበኩሉ ቀድሞም ቢሆን በጨዋነቱና በመልካም ጠባዩ አኩሪ ደረጃ ላይ እንዳለ ራሱን አስቧል። በእነዚህ የቅርብ ጓደኞቹ ላይ ካስተዋለው ደስታና ዕረፍትን የተጎናጸፈ ሕይወት ሌላ ግን ሲናገሩ የሚሰማቸው አዳዲስ ነገሮች ጥያቄ ፈጥረውበታል። ጓደኞቹ ስለ "ዳግም መወለድ" ስለ "አዲስ ሕይወት" ስለ አገኙት ሰላምና ደስታ ያወራሩለት ነገር ትዝ ይለዋል፤ በጓደኞቹም መካከል ይህ ጉዳይ በውይይትም ሆነ በክርክር መልክ በተነሳ ቁጥር ጥበቡ በጥሞና አዳምጧቸዋል። እርሱ በበኩሉ ግን ስለእምነትና ስለ እግዚአብሔር ከተነሳ ጓደኞቹን ሁሉ የሚያጥፍ ዕውቀት እንዳለው ስለገመተ፣ ይህ "አዲስ ሕይወት" ጓደኞቹን እንጂ እርሱን እንደማይመለከት ደምድሟል።

በዚህ መኻል ነበር በነሐሴ ወር፣ አንዱን ቀን ገበየሁ ከሚባል ጓደኛው ጋር ሳለ ጥበቡ ላንዴና ለመጨረሻ ሥር ነቀል ለውጥ የሚያካሄድ ሁኔታ የገጠመው። ጥበቡና ጓደኛው ገበየሁ አብረው ሻይ ለመጠጣት፣ ያን ቀን ፒያሳ መኻል ናቸው። ሁለቱ በአንድነት ሳሉም ታደለ የተባለ ሌላ ጓደኛቸው ድንገት ያገኛቸውና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፣

"ወዴት እየሄዳችሁ ነው?"

"ወደ ቤተክርስቲያን"

የሚል ነበር ድንገት ከጥበቡ አፍ የወጣው፡ ገበየሁም የጥበቡ መልስ ለቀልድ ያህል እንጂ ቤተክርስቲያን ለመሄድ ሃሳብ አንድም እንዳልነበራቸው ስለሚያውቅ እርሱም የበኩሉን በቀልድ፣

"አዎን! ወደ ቸርች እየሄድን ነው ለምን አንተም አብረኸን አትመጣም?"

"አይ! እግዜር ይስጥልኝ ስለጋብዘኸው፣ ሌላ ፕሮግራም ስላለኝ አብሬያችሁ ልሆን አልችልም" በማለት ታደለ መንገዱን ይቀጥላል። ጥበቡ ግን በመዋሸቱ ደስ አልተሰኘም። ስለዚህ ጓደኛውን፡-

"ገበየሁ ውሸት መናገር አልነበረብንም! በእርግጥ ውሸቱን የጀመርኩት እኔው ነኝ። ግን እንዳልነው ለምን አንድ ቸርች እዚህ አካባቢ ፈልገን አንሄድም? የሚያስቸኩለን ጉዳይ እንደሁ የለብንም?"

ሲል ጥበቡ ይጠይቀዋል። ገበየሁ ጥቂት ካንገራገረ በኋላ፡- "መልካም እንደሱ ማድረግ ከፈለግህ እዚህ ቅርብ አንድ ቸርች አለ እዚያ እንሂድና ፕሮግራም ካላቸው እንይ" ይለዋል። በሃሳቡ ጥበቡ ይስማማና በገበየሁ ቀዳሚነት ከመሀል ፒያሳ ወጥተው የራስ መኮንንን ድልድይ አልፈው ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ ከሚገኘው የትራፊክ መብራት አጠገብ ወዳለው አንድ ትልቅ የመንገድ ዳር ቤት ይደርሳሉ።

ጥበቡ በአእምሮው ከሳለውም ሆነ ወትሮ ከሚያውቀው የቤተክርስቲያን ሕንጻ ጋር ጨርሶ ስለማይመሳሰል ግራ እንደገባው፣ ብዙዎች ወጣቶች ወደ ሚጎርፉበት መንገድ ዳር ወደሚገኘው ወደዚያ ትልቅ ቤት ገበየሁ ይመራዋል። "ታላቅ የመንፈሳዊ መነቃቃት ከስዊድን በመጡ በወንጌላዊው ማትሰን በዜ!" የሚል በትልልቁ ፊደል የተጻፈ ማስታወቂያ ግቢው መግቢያ ላይ ተሰቅሏል። ወደዚያ አዳራሽ ከሚጎርፉት ወጣቶች ጋር ተቀላቅለው ጥበቡና ገበየሁ ገቡ።

****

*"እግዚአብሔር ታላቅ ነው! በፊቱ ተንበርከክ!"*

የአዳራሹ መስኮቶች ወለል ብለው ተከፍተዋል። ከበረንዳዎቹ አንስቶ ውስጥ የተደረደሩት አግዳሚ ደረቅ ወንበሮች በፍጥነት በሰዎች እየተሞሉ ነው። ጥበቡና ገበየሁም እንደገቡ መቀመጫ ከገኙ በኋላ ዙሪያቸውን ሲቃኙ የሚያውቋቸውን ወጣቶች በዚያ ስፍራ መመልከታቸውም ጥበቡን ገርሞታል። ወጣቶቹ እርስ በእርስ ልባዊ ሰላምታ ሲሰጣጡ የተመለከተው ጥበቡ ያ ስፍራ ፍቅርና መተሳሰብ የሞላበት ስፍራ መሆኑ ስለገባው፣ ምንም እንኳ ለቦታው አዲስና እንግዳ ቢሆንም ባይተዋርነት እንዳይሰማው አድርጎታል። ከጓደኛው ጋር በደረሳቸው አግዳሚ ወንበር ላይ እንደተቀመጡ፣ ጥበቡ ሰምቶ የማያውቃቸው መንፈሳዊ መዝሙሮች በታላቅ ድምፅ በወጣቶቹ እየተዘመረ የአዳራሹ አየር ተቀጣጠለ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ድል አድራጊነት፣ ስለደሙ ኃይል "ሃሌሉያ!" ከሚለው ቃል ጋር እየተዘመረ አዳራሹ ብቻ ሳይሆን አከባቢው ሁሉ ይነዋወጣል፤ በጭብጨባና በእልልታ ዝማሬያቸው እንደታላቅ ማዕበልና የባህር ሞገድ ይተምማል። ለበጣ በሌለበት ከልብና ከነፍስ በወጣ ዝማሬ፣ አምላኩን ሲያመሰግን የቆየው ያ በወጣቶች የተሞላው ጉባዔ ከዚያው በላነሰ ከፍተኛ ድምጽና ጩኸት ከእንባ ጋራ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ የተመለከተው ጥበቡ፣ የሚያየውና የሚሰማው ነገር ሁሉ አዲስና ለየት ያለ ቢሆንበትም ሁኔታው አላስበረገገውም፤ ይልቁንም የዕድሜ እኩያዎቹ የሚሆኑ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ምሕረትና ቸርነት ተአምራዊ ፈውስም፣ በሰው ሁሉ ፊት ቆመው በእንባ ሲናገሩ የሰማቸው በታላቅ ተመስጦ ነበር።

ጸሎት ታላቅ መንፈሳዊ መሣሪያ እንደሆነ በመግለጽ የሰበከው ሰባኪ፣ የተማሩትን ሁሉ እዚያው በዚያው ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ጉባዔውን ለጸሎት ጋበዘ።

"እንዳመቻችሁ መጸለይ ትችላላችሁ!! ቆማችሁም ሆነ ተቀምጣችሁ፣ ወይንም ተንበርክካችሁ የምትጸልዩትን ጸሎት ሰምቶ፣ በድንቅ ወደሚመለሰው አምላክ ጸልዩ!! እግዚብሔር የሚያየው የልባችሁን ሁኔታና ዝግጅት እንጂ የአቀራረብ ዘይቤያችሁን አይደለም፣ ሲል መመሪያ ለሰጠው ሰባኪ ተግባራዊ ምላሽ፣ ጉባኤው በጸሎት ድምፅና ጩኸት መነዋወጥ ጀመረ።

ወዲያውኑ ከጥበቡና ከገበየሁ ግራና ቀኝ ከነበሩት ሰዎች አንስቶ፣ ብዙዎች በጉልበታቸው ተንበረክከው መጸለይ ጀመሩ። ጥበቡና ገበየሁ እዚያው ወንበራቸው ላይ እንደተቀመጡ ናቸው።ጥበቡም ለዓይኑ አዲስ የሆውን ይህን መሰል ታላቅ የጉባዔ ለጸሎት ግር ከመሰኘት ጋር መቃኘት ጀመረ። በዚያ ሁኔታ ላይ ሳለ ነበር በድንገት ጥበቡ ጥርት ያለ ድምጽ ከውስጡ የተሰማው። "እግዚአብሔር ታላቅ ነው! በፊቱ ተንበርክክ!" የሚለው።

ጥበቡ ፈጥኖ በትህትና ለመንበርከክ አላስቸገረውም። ይሄን ከመሰለ መንጋ ጋር ተቀላቅሎ ወደ እግዚአብሔር እቅፍ መግባት ምኞቱ ነው። ስለዚህ በዘላለማዊው እግዚአብሔር ዙፋን ሥር ፊቱን በእጆቹ ሸፍኖ በግንበሩ ተደፋ!! ድንገትም ዓይኖቹ በሙላት ድቅን ድቅን የሚልባቸውን እንባ እንደ ውኃ ማፍሰስ ጀመሩ። ቅዱስና ሕያው የሆነው የታላቁ የእግዚአብሔር በዚያ ስፍራ መገኘት ተሰማው። የእርሱ ታናሽነትና ኢምንትነት፣ የእግዚአብሔር ደግሞ ታላቅነት ሲገለጥለት፣ የፈጣሪው ምሕረትና ይቅርታ የሚያስፈልገው ኃጢአተኛ መሆኑ ጥበቡ በትክክል ገባው!!

****

*አዲስ ሰውነት*

የሰማይና የምድር ጌታ በሆነው በልዑል እግዚአብሔር ፊት እንዲህ በንስሐ ወድቆ ሳለ ነበር ድንገት ትከሻውን ነካ ነካ የሚያደርገው እጅ የተሰማው። ለማየት ቀና ቢል ጓደኛው ገበየሁ ነበር። ፊቱን በሁለት እጆቹ ሸፍኖ ሰውነቱ እስኪንዘፈዘፍ ይሰቃል። ጥበቡም በግንበሩ የተደፋው እንደርሱ በሰዎቹ ሊያሾፍ መስሎት። ጥበቡ ግን እንባ በተሞሉ ዓይኖቹ ጓደኛውን ገበየሁን ቀና ብሎ ካየ በኋላ ተመልሶ በዘላለማዊው አምላክ ፊት ተደፍቶ የንስሐ እንባውን ማፍሰሱን ቀጠለ። የእግዚአብሔርን ምሕረትና ይቅርታ ያላገኙ የሰው ልጆች ሁሉ፣ ፍፃሜያቸው ከዘላለም እስከዘላለም በሚነድ የእሳት ባህር ውስጥ መጣል እንደሆነ አሁን ጥበቡ በግልጽ ገብቶታል። በአንፃሩ ደግሞ እግዚብሔር አምላክ የሰውን ልጆች ከሚጠብቃቸው የዘላለም መከራ ለመታደግ ሲል የሰማይ ክብሩን ሁሉ ጥሎ አንድያ ልጁን እንዲልክ የተገደደበት፣ የእግዚአብሔር የፍቅሩ ጥልቀት፣ የቂላንቂል ያህል በርቶለታል። ስለዚህም ሁሉን አራቀቶ በሚያየው ቅዱስና ኃያል አምላክ ፊት በኃጢአት የተበከለች ነፍሱን ይዞ መቅረቡ የገባው ጥበቡ፣ የፈጣሪውን ምሕረት ለመቀበል ዐይኖቹ እንባ ያዘንባሉ። በእንባው ጎርፍ ወለሉ ታጠበ። በደቂቃና በሰዓት ቢለካ በውል ትዝ አይለውም። አስደናቂው የሰማይ ብርሃን በበራለት በዚያ ልዩ ቀን ግን ጥበቡ በግንባሩ ከተደፋበት የጸሎት ስፍራው ሲነሳ አዲስ ውስጣዊ ሰውነት፥- ዕረፍትና ሰላም፣ የሚያስፈነድቅም ደስታ ተጎናጽፎ ተነስቷል።

እነዚያ የንስሐ እንባን ያዘነቡ ዓይኖች የሚፍለቀለቁ የደስታ ምንጮች ሆኑ!! በውስጡ ከተከሄደው መለኮታዊ ለውጥ የተነሳም ፊቱ በብርሃንና በፈገግታ የተሞላ አዲስ ገጽታ ነበረው። ከመንፈስ የተወለደ አዲሱ መንፈሳዊ ሕይወት የጥበቡን ውስጣዊና ውጫዊ አመለካከት አስቀየረው፤ ከዚያች ልዩ ቀን አንስቶ በዚያ ትልቅ ቤት ይካሄድ የነበረውን መንፈሳዊ መነቃቂያ ፕሮግራም እስከ መጨረሻው ሲካፈል ሰንብቷል። በእግዚአብሔር ፊት ረዘም ላለ ጊዜ በጸሎት ማሳለፉ ተስማምቶት ወዶታል። ስለዚህም ጥበቡ ለሰዓታት በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት መንበርከክ የተለማመደው ገና በለጋ መንፈሳዊ ዕድሜው ነበር። በዚያ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው በሚደረገው የጾም የጸሎት ፕሮግራም ላይ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ በጸሎት ከሚተጉ ወጣቶች አንዱ ጥበቡ መሆኑ እየጎላ መጣ። ጥበቡ ከጸሎት ሕይወቱ በላነሰ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱሱን ጠንቅቆ የማንበብና የማስተዋል ጸጋውም ያድግ ጀመር።

****

*የምኞት ሬሳ!*

ወደ እኔው ታሪክ ልመልሳችሁና ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ሆኗል (1ኛቆሮ.5፡19) ከሚለው አምላካዊ ቃሉ የተነሳ ሕይወቴ አዲስነትን ተቀዳጅቷል። የጽድቁ ፀዳል በነገሰበት በአምላኬ ቤት ሳይቆረቁረኝ በሰላምና በደስታ መኖሩ እጅግ ጥሞኛል። ከድቅድቅ ጨለማ ወደሚደነቀው ብርሃኑ ያፈለሰኝ ያምላኬና የሰማይ አባቴ ቤት ተመችቶኝና ተስማምቶኝ እፈነጥዛለሁ፤ ስለ ኢየሱስ ፍቅርና ሰላም በእርሱም ስለሆነልኝ መዳን ለአላፊ አግዳሚው ሁሉ እመሰክራለሁ። በዚህ ወቅት ግን መንፈሳዊ እድገቴን በሚገታ አስተሳሰብ ውስጥ ሳላስተውል ገባሁ። አምላኬም ሰላምና እውነት ወደ ሆነው ወደ ጽድቅ መንገዱ ሊመልሰኝ ሲል በእኔ ላይ ስላለው የፍቅር ዓላማው እንደ ጨከኝ በህይወቴ ተገለጠ!

በዚህ ወቅት የምድር ወላጅ አባቴ "የእኔ ልጅ ሐኪም ነው የምትሆነው!" ሲል

በትምክህትና በተሰፋ ሲጠባበቅ ከነበረው ሕልሙ እጅግ እሩቅ ነኝ። የምገኘው ዩኒቨርስቲው በመደበኝ ምርጫዬና ፍላጎቴ ባልሆነው በአርትስ ፋኩልቲ ውስጥ ነው። ትምህርቴን በተከፋፈለ ልብ ከመከታተሌ ሌላ ከትምህርት አማካሪዎቼ ሃሳብ ውጪ ሳይንስ ፋኩልቲ ለመግባት በግሌ ከፍተኛ የሥጋ ጥረት በማድረግ ላይ እገኛለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ጉዳይ ላይ የሰማይ አባቴም የፈቃደኝነት ፊርማውን እንዲያኖርበት "በጸሎት" ደጁን የምጠናበት ጊዜም ነበር። ሆኖም ግን ልቤን የሚሞላልኝም ሆነ የሚያረካኝ መልስ አጥቻለሁ ! እንዲቀበለኝ ያቀረብኩትም ማመልከቻዬን ሳይንስ ፋኩልቲ ዋጋ እንዳልሰጠው የሚያረዳኝ ደብዳቤም ሰሞኑን ደርሶኛል። በደብዳቤው የደረሰኝን መልዕክት ከሰማይ እንደመጣ መልስ አድርጌ መቀበሉ አልተዋጠልኝም። በዓመቱ መጨረሻ ወደ ሁለተኛ ዓመት የተዛወርኩበትን የአርትስ ፋኩልቲን በፈቃዴ ተሰናብቼ "በዘመድ" (የአሮጌው ሰው ባህሪ) እንደገና በአንደኛ ዓመት ተማሪነት እዛ ሳይንስ ፋኩልቲ ውስጥ ገባሁ። በዚህ ወቅት ነበር እንግዲህ ጌታ እግዚአብሔር ስለአዲሱ መንፈሳዊ አካል ምንነት ሊያስተምረኝ የወደደው። ህይወቴ ከድል ወደ ድል የሚወጣበትን፤ ሰማያዊ የምሥጢር ቁልፍ ሊያስጨብጠኝ እንደ ጨካኝ ቆርጦ የተነሳው ! !

በብዙ የሥጋ ጥረት የገባሁበት የሳይንስ ፋኩልቲ ብዙም ሳይቆይ በትምህርት ዘመኔ ሁሉ ዓይቼ የማላውቀውን ጥቁር ነጥብ ሲጥልብኝ ተመለከትኩ ! በአገራችን በጊዜው ይሰጡ ከነበሩት ሳይንስ ነክ ትምህርቶች የተለየሁባቸው ያለፉት ዓመታት ፣ ከክፍል ጓደኞቼ ጋር እኩል እንዳልራመድ ያልጠረጠርኩትን ችግር አስከተሉብኝ ! ውስጤ የተተገነበት ያ እእምሮን ሁሉ የሚያልፈው የሰላሜና የደስታዬ አጥር አንድ በአንድ ተመዘዘ። በአምላኬ ቤት የተለማመድኩት ምቾቴና እረፍቴ ሲተንገል ድንጋጤ ያዘኝ ! በሰማይ አባቴ ቤት እንደ ተወለድኩ ስቦርቅበትና ነፍሴ ስትምነሽነሽ የነበረችበት ፍንድቅድቅ ያለው ህይወቴ በጥያቄ ተሞላ ! የእግዚአብሔር መንፈስ ከውስጤ ሲቆዝም ይሰማኛል ምክንያቱ ግን ሊገባኝ ስላልቻለ ልቤ በታላቅ ማመንታት ውስጥ ገባ። "አምላኬ ሆይ ! ምን በድዬ ይሆን?" የእለት ጥያቄዬ ሆነ። መድረስ አይቀርምና የመጀመሪያው ሴሚስተር ፈተና እየተቃረበ ስለመጣ የሞት የሽረት ዝግጅቴን በምችለው ሁሉ አድርጌ ለፈተናው ተቀመጥሁ። ዩኒቨርሲቲው ለገና በዓል (ልደት) ተዘግቶ ሲከፈት ውጤት የምሰማበት ጊዜ ነው። ውጤታችንን ወደ ምንቀበልበት ስፍራ ብቻዬን እንደደረስኩ የታሸገውን ፖስታ በጥድፊያ ከፈትኩ። በትምህርት ታሪኬ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ ሽንፈትና ውድቀት እንደደረሰብኝ ወረቀቱ ይዘግባል። የሚያዩት ዓይኖቼ ግን እውነታውን ለመቀበል ተሳናቸው ! ! ብቻ እንደሞተ በድን የሆነውን ሰውነቴን የተሸከሙት እግሮቼ ወደ መኝታ ክፍሌ ለመድረስ ተብረከረኩ ! እንከትክቱ የወጣውን "ሐኪም" የመሆን ሕልሜን... የምወደውን የዚያን የወላጅ አባቴን የምኞት ሬሳ ይገፔ እያለቀስኩ... ወደ መኝታ ቤቴ ስገባ ደግነቱ በክፍል ውስጥ ማንኛቸውም ጓደኞቼ አልነበሩም።

****

"የሚረባህን ነገር የማስተምርህ. . "

ፊጥኜ በአምላኬና በሰማይ አባቴ ፊት ተደፋሁ ! የታላቅ ዋይታና የሰቆቃ ጊዜ ሆነ !

"ወዮ አምላኬ ሆይ! ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ያውም አንተን የህይወቴ ጌታና መሪ አድርጌ በተቀበልኩበት በዚህ በአሁኑ ዘመን! አጥፎ ከማለፍና ከአንደኝነት ወርዶ የማያውቀው ታሪኬ እንዴት ይደመሰሳል?... አንተን መከተሌ ሞኝነትና ኋላ ቀርነት የመሰላቸው ቤተሰቦቼ እና ዘመዶቼስ ይህን ሲሰሙ ምን ይላሉ?... በቀድሞ የትምህርት ዘመኔ ያላየሁት ውርደትና ውድቀትስ እንዴት በአንተ ቤት ዛሬ ይደርስብኛል?..."

በሰማይ አባቴ እግሮች ሥር ተደፍቼ ዋይታዬንና ኡኡታዬን ለቀቅሁት ! ! ! እነዚያ ጫጩት ንስሮች በምቹው የእናታቸው ቤት እና በክንፎቿ ላይ ሲለማመዱ የቆዩት ያ የፊንጠዚያና የደስታ ወቅት ከክንፎቿ አሽቀንጥራ ከሰማይ ወደ ምድር በወረወረቻቸው ጊዜ በዋይታና በኡኡታ እንደተተኩው ዓይነት ። እኔም ከዛ ባላነሰ ስሜት ከፈራረሰብኝ ሕልሜ ጋር በምድር ላይ ተከስክሼ እንድወድቅ አምላኬ ከእጆቹ አራግፎ የለቀቀኝ... አሽቀንጥሮ የጣለኝ መሰለኝ ! ! "ምን በደልኩህ? ምንስ አድርጌህ ወደዚህ መራራ ፍጻሜ አመጣኸኝ? ?" እያልኩ ለረዥም ሰዓታት ካነባሁ በኋላ "እባክህ አምላኬ ሆይ ! ወደ ሞት በማሽቆለቁልበት በዚህ ቅጽበት ዝም አትበለኝ ! እንድትናገረኝ እለምንሃለሁ ! " አልኩት።

ወዲያውኑ መጽሐፍ ቅዱሴን እንደገለጥኩ በእንባ የሚታጠቡት ዓይኖቼ ትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ በምዕራፍ 48፥ 17-19 ላይ በረፉ !

"ታዳጊህ የእስራኤል ቅዱስ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል... እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድበት መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ። ትዕዛዜን ብትሰማ ኖሮ ሰላምህ እንደ ወንዝ ጽድቅህም እንደ ባህር ሞገድ በሆነ ነበር። ዘርህም እንደ አሸዋ የሆድህም ትውልድ እንደ ምድር ትቢያ በሆነ ነበር። ስሙም ከፊቴ ባልጠፋና ባልፈረሰ ነበር።"

የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ውስጤ በሚገባው መንገድ ተሰተጋባ። በሕሊናዬ ውስጥ ተቀብሮ የነበረውን አንድ የማልከደውን እውነት ቀስቅሶ ፊት ለፊት ጋረጠው ! ይኸውም እግዚአብሔር በከፈተልኝ በር አርትስ ፋኩልቲ መቀጠል ሲገባኝ የወሰድኩት የገዛ ራሴ ስጋዊ መንገድ። አይደለም የትምህርት አማካሪዎቼን ምክር የሚረባኝን ነገር የሚያስተምረኝን የምሄድባትንም መንገድ የሚመራኝን የአምላኬን ምክርና ትዕዛዝ እንኳን አሻፈረኝ ማለቴ። እናም በዘመድና በሥጋ ጥረት ሳይንስ ፋኩልቲ መግባቴ የአምላኬን ሳይሆን የራሴን መንገድ ይገፎ መንገዴን። የእግዚአብሔር መንፈስ ይህን ሁሉ ቁልጭ አድርጎ ቢያሳየኝ ወዴት ልግባ? ?

የገዛ መንገዴንና የዘራሁትን የሥጋ ምኞቴን መራራ ፍሬ ማጨዴ ታወቀኝ። የሚረባኝን ነገር ሊያስተምረኝ ስህተትና እንከን በማይገኝለት የጽድቅ መንገዱ ሊመራኝ ከሚወደው አምላኬ እጆቹን መንጭቄ ማውጣቴን ተረዳሁት። በጸጋውና በምህረቱ ልጁ ያደረገኝን አምላኬንና ጌታዬን ልዑል እግዚአብሔርን ምን ያህል እንደ በደልኩት ተገለጠልኝ። የውጤት ወረቀቴን መርዶ እንደ ተረዳሁ በአምላኬ ፊት ጸሎቴን የጀመርኩት። "...ባንተ ቤት ይህ እንዴት ይደርስብኛል? ለምን በእኔ?...ወ.ዘ.ተ" በሚል የመረረ ልቅሶ ነበር። አሁን ግን እውነተኛው የእግዚአብሔር መንፈስ የዚህ ሁሉ ነገር መሰረታዊ ምክንያት እኔው እራሴ መሆኔን ገለጸልኝ። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ይልቅ የገዛ ፈቃዴንና መንገዴን በመከተሌ መሆኑን ግልጽ አድርጎ አሳየኝ ! ! ይህ ግንዛቤና

እውነት ነፍሴ ሲገባትና ስትረዳ ደግሞ እንዲያ የወደዳትን በጥልቅ ምህረቱም የታደጋትን አምላኳንና ቤዛዋን በማሳዘኗ ፊቃዱን በመጣሷና በአሮጌው መንገዷ በመክነፏ... ወደ ክፉ ፍጻሜ መሽቆልቆሏን ተመለከትኩ። አምላኬ ከእጆቹ ያረገፈኝ የእኔ ነገር የበቃውና የተወኝ መሰለኝ! ጣዕር በተሞላው የእንባ ጩኸት በምሕረት እጆቹ ፈጣሪዬ ፈጥኖ እንዲታደገኝ ለመንኩት! ዓይኖቼን ወደ ሰማይ አንስቼ ለማየት እንኳን ከበደኝ! ምድር ላይ ተደፍቼ በብዙ ንስሐና እንባ የአምላኬንና የጌታዬን ይቅርታ እየለመኩ እንዲህ በተሰባበርኩበት ሁኔታ ውስጥ እንዳይተወኝ... ምሕረት እንዲያደርግልኝ ተማፀንኩት!!

ገልጬ ወደ ተውኩት መጽሐፍ ቅዱሴ ቃል ፍለጋ ዓይኖቼ ሲያማትሩ እዚያው ትንቢተ ኢሳያስ ውስጥ ምዕራፍ 49፣14-16 ላይ ዐረፉ! ከቁጣ ይልቅ ምሕረትን የሚወደው አምላኬ በፊቱ ያፈሰስኩትን እንባና የንስሀ ጸሎት ተመልክቶ ሕያው በሆነው ቃሉ አሁንም እንደገና ሊናገረኝ ወደደ! ተንቀሳቃሽ ነፍስ ያለው ፊደል መስሎኝ እስከደነቅ ድረስ። እንከትክቷ ወደ ወጣው ነፍሴ የጌታዬና የአምላኬ ቃል በፊቴ በተጋረጠው ሐኪም ያለመሆን ተራራዬ ላይ እየዘለለ እንዲህ ሲል መጣ!

> "ጽዮን ግን፡- እግዚአብሔር ትቶኛል ጌታም ረስቶኛል አለች። በውኑ ሴት ከማህፀንዋ ለተወለደው ልጅ እስከማትራራ ድረስ ሕጻንዋን ትረሳ ዘንድ ትችላለችን? አዎን እርስዋ ትረሳ ይሆናል። እኔ ግን አልረሳሽም። እነሆ በእጄ መዳፍ ቀርጬሻለሁ ቅጥሮችሽም ሁልጊዜ በፊቴ አሉ።"

መራራ ከሆነው ከዚህ ሁኔታዬ ውስጥ መንጥቆ የሚያወጣኝ የአምላኬ ሕልውና ወዲያውኑ ዙሪያዬን ከበበው! የፍቅር እጆቹ እንዲያ ተሰባብሬ ከወደቅሁበት ስፍራ አንስተው ሲገጣጥሙኝና ሲያበጃጁኝ ተሰማኝ! የአምላኬ የምሕረትና የይቅርታ አዋጅ በሁለንተናዬ ተስተጋባ! በዋይታና በጸጸት የተጀመረው ጸሎቴ የራራልኝንና ይቅር ያለኝን የሰማይ የምድር ጌታ በማምለክና በማመስገን ተደመደመ።

ታላቅ ተሃድሶና መጽናናት ውስጤ ተሞልቶ ከሥጋዬ ምኞትና ፈቃድ ይልቅ ከእንግዲህ የሚጠቅመኝን ክቡር የሆነውን የእግዚአብሔር ቅዱስ ፍቃድ በዘመኔ ሁሉ ለመርጠው ወስኜ ከጸሎቴ ስፍራ ተነሳሁ። የሰዓቱን መዋገድ ሳላውቀው ከአምላኬ ጋራ ነገሬን አስተካክዬ ስነሳ ቀኑ መሽቷል! በይኖቼም ካጎረፋት እንባ የተነሳ እጅግ አባብጠዋል! እንደበቴ ግን በብዙ ምስጋና ተሞልቷል!! በዚያን ምሽት ያገኙኝ ክርስቲያን ጓደኞቼ የፈተናዬን ውጤት ሰምተው በማዘናቸው እኔን የሚያጽናኑበት ቃል አጥሯቸዋል። ሰው ሳያገኘኝ በፊት አስቀድሞ ያገኘኝ አምላኬ የሚያስደንቅ መለኮታዊ ሥራ በሕይወቴ መሥራቱ አስደነቃቸው። ስለዚህም ከወገኖቼ ጋር የነበረን ምሽት የጸሎትና የኅብረት ጊዜ፣ ወደ እውነተኛ አምልኮና የምስጋና ጊዜ ተለወጠልን!! እንዲያውም የዚያን ሰሞን አገልገሎቴ እዚያው ዩኒቨርሲቲው ውስጥ የፈተና ውጤታቸው እንደኔው ዓይነት ሆኖባቸው መጽናናት የተሳናቸውን ክርስቲያን ወገኖቼን ማጽናናት አብሮ መጸለይና ማበረታታት ሆነ! በወረደባቸው የ ኀዘን ስሜትና በወቅቱ በገጠማቸው የጨለመ ሁኔታ ውስጥ፣ እኔም አልፌ ስላየሁት ጆሯቸው ለእኔ ክፍት ነበረ። ጌታ እግዚአብሔር ከእንደዚያ ዓይነት የሕይወት ሸለቆ አውጥቶ እርሱን የሚያመሰግነው ልብና እንደበት እንደሰጠኝ ራሳቸውን የዓይን ምስክሮች አድርጓቸው ነበርና። ስለዚህ የሰውን ፊት ዐይቶ የማያዳላው እግዚአብሔር እነርሱንም ሊረዳ በአጠገባቸው እንደሆነ በእርግጠኝነት ስመሰክርላቸው አብረውኝ ለመጸለይ ልባቸውም ጭምር ለእኔ የተከፈተ ሆነ። ወላጆቼም በሁኔታው እንዳይጎዱ

በብዙ ስጸልይ ነበርና ትምህርቴን በሚመለከት ስላገኘሁት ውጤት ሲረዱ፣ "የምትቺይውን ሁሉ እንደሞከርሽ እናምናለን። ይህ ባይሆን ሌላ ሌላም እድል ስላለሽ አይዞሽ!" ሲሉ እንዲያጽናኑኝ አድርጓል እግዚአብሔር!

****

*"እኔ ምንኛ ኅሰቃላ ሰው ነኝ!"*

ተሰባብሬ ልወድቅ ከነበረበት የመጀመሪያው ዙር የሕይወት ሽለቆ አምላኬ ፈጥኖ ደርሶ እንዲያ ስለታደገኝ በመንፈሳዊው ዓለም በከፍታዎች ላይ አሁን የምከንፍበት ጊዜ ነው!! ይህ ጊዜ ከቀለም ትምህርት የተለየሁበት ጊዜ ቢሆንም ለነፍሴ የሚጠቅሟትን ታላላቅ መንፈሳዊ ትምህርቶችና መሰረታዊ መመሪያዎች በእግዚአብሔር ቤት ወደ ተቀበልኩበት ሰፊ በር አስገብቶኛል። ከእንግዲህ በኋላ ዳግም በራሴ ምርጫና መንገድ ላለመሄድ በውስጤ ቆርጫለሁ። ስለዚህም አምላኬ አቅጣጫ እንዲሰጠኝና እንድሆንለት የሚፈልገውንም እንዲነግረኝ መጠየቅ የዘወትር የጸሎት ርእሴ ሆኗል።እስከዚያው ግን ጊዜዬን በአብዛኛው የማሳልፈው መጽሐፍ ቅዱሴን በግሌ በማጥናትና ሰፊ የጸሎት ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት በማሳለፍ ነበር። ለሰዎች መመስከርና ከወገኖች ጋር የኅብረት ጊዜ ማድረግም በዝቶልኛል። በዚያን ዘመን የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በመካከላችን ካፈሰሰው ታላቅ አንድነትና መተሳሰር የተነሳ ዛሬም ይህን ታሪክ ስጽፍ ከአርባ ስድስት ዓመታት በላይ በልብ ጓደኛሞችነት በቤቱ ያስቆጠረን በርካታ እህቶችና ወንድሞች አሉኝ!

ስለዚህ ውሎዬ ባብዛኛው በቤተክርስቲያን የጸሎት ክፍል ከአምላኬ ጋር በመነጋገር ነበር፣ አልያም መንፈስ እንደመራኝ በመመስከርና ቅዱሳንን በመጎብኘት። ወይንም በሳምንቱ መካከል የሚካሄዱትን ፕሮግራሞቹ መካፈልና በሳምንቱ መጨረሻ ላይ በሚኖሩን የአዳር ጸሎቶች ላይ መገኘት እወድ ነበር። የትምህርትም ሆነ የሥራ ውጥረት አልነበረኝም። ስለዚህ ሰፊ ጊዜዬን በማስተዋል ልጠቀም ከመሰል እህት ወንድሞቼም ጋር ጊዜው ሳለኝ የአምላካችንን ሥራ ልሠራ ቆርጬ ተነሳሁ! እግዚአብሔርም በጊዜው ካገናኘን ከተወሰኑ እህቶችና ወንድሞች ጋር በክርስቶስ ስለሚገኘው ደህንነት እንመሰክራለን። በአጋንንት የታሰሩት እንዲፈወሱ የታመሙት እንዲድኑ... የእግዚአብሔርን ሥራ በታላቅ ትጋትና ቅንዓት የምንሠራበት ጊዜ ሆነልን። በእንዲህ ያለ ትጉ መንፈስ በወቅቱ እግዚአብሔር አብሮ ጠምዶ ካሰማራን መሰል ወገኖቼ ጋር እግዚአብሔርን በፍጹም ፍቅርና በሙሉ ፈቃደኝነት ያገለግልንባቸው ጊዜያት እጅግ በርካታ ነበሩ!

ታዲያ በዚህ ሁኔታ ሳለን ነበር ሳናስተውል ከአንደኛው ወንድም ጋር እጅግ እየተቀራረብን መምጣታችን የገባኝ። እርሱም እንደኔው ሰፊ ጊዜ ነበረው። ለእግዚአብሔር ባለን የተቀጣጠለ ፍቅር ስለ መንፈሳዊ ሕይወትም ሆነ አገልግሎት ያለን አስተሳሰብና አመለካከት... የሚመሳሰል ሆኖ ስላገኘነው ሳናውቀው እንፈላለግ ጀመር። እኔ ባለሁበት እሱ፣ ደግሞም እሱ ባለበት እኔ መገኘት "ሳይታለም የተፈታ ሕልም" ዓይነት ነገር ነበር። ሰዎች ጥያቄ የሚኖራቸው አንዳችን በተገኘንበት ሌላችን ሳንገኝ ብንቀር ሆነ። ከሌሎች ጓደኞቻችን መሀል ሆነን የእግዚአብሔርን ቃል ስንከፋፈል ብዙ አብሮ የመፍሰስ ነገር አለን። ባሁኑ ዘመን በውጪው ዓለም ወጣቶች ለጓደኝነት ወይም ለጋብቻ ሲፈላለጉ እንደሚወስዱት የተሳሳተ ምልክት። "ክሊክ" እናደርጋለን ወይም "ኮምፓቴብል ነን" (we click or we are compatable) እንደሚሉት ዓይነት።

ባብዛኛው ያለን አስተሳሰብና አመለካከት.. የሚመሳሰል ሆኖ ስላገኘነው ሳናውቀው

እኛም እራሳችንን ለእርስ በእርሳችን እንፈልገው ጀመር። ለእርሱ ያለንን ቅንዓት ፍቅርና አክብሮት እግዚአብሔር ዓይቶ ከዚህ ወንድም ጋር የምንሰጠውን አገልግሎት ሲባርከው ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከዚህም ሰፋ ያለ ሃሳብ እንዳለውና ለትዳርም እንድንተጫጭ ያቀራረበን መሰለን። በብዙዎች ዓይን ፊትም የሚጠበቅና የሚታሰብ ነበር። ከሁለታችን ይፈልቅ የነበረውን ያን የእግዚአብሔር ፍቅር "እኛ" ደግሞ በትዳር ገምደን ብንቋጨው፣ ይበልጡን እንደሚቀጣጠል በራሳችንም ሆነ በሰዎች ዘንድ ተገመተ። ራሳችንን በትዳር መንገድ ላይ ስላስቀመጥን እንደ ፍቅረኞች እጅ ለእጅ ተያይዞ መሄድና መተያየት ስህተት አልመሰለንም። ብቻችንን ሆነን መውጣት፣ ማምሸት፣ ስለሚኖረን ትዳርም አልፎ ማውራትና ማለም፣ ስህተት አልመሰለንም። ለትዳር የሚያስፈልገው መዋደድና ፍቅር ከሆነ፣ እኛ ሞልቶ ተርፎናል ብለን አሰብን። ለቤተሰብ ሃሳባችንን አልተናገርንም እንጂ በእኛ በኩል በእጮኝነት ጥቂት ለመቆየት ተስማምተን በግልም ሆነ በህብረት የነበረንን መንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት ይበልጥ ለማጠናከር ቆርጠን ተነሳን።

ይህ በዚህ እንዳለ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ለሬድዮና ለቴሌቪዥን ጋዜጠኝነት ለማሰልጠን ተወዳዳሪዎች እንዲቀርቡ ስለጠየቀ፣ አንዲት ክርስቲያን እህቴ ለውድድሩ እንድቀርብ ገፋፋቺኝ። እኔም በጊዜው ...የእግዚአብሔር ፈቃድ ባልሆነ መንገድ ውስጥ እንዳልገኝ በአምላኬ ፊት በጸሎት ቀረብኩ። በቃል በጽሑፍ በድምጽና በተለያዩ የማጣሪያ ፈተናዎች ካለፉት አንዷ ተብዬ ለስልጠናው ስታደም አሳሰበኝ። ቦታው ለመንፈሴ አልተመቸውም። እርቄ ከመሄዴ በፊት ማንነቴን ለማስታወቅ ቆረጥኩ። በወቅቱ የኢትዮጵያ ሬዲዮና የቴሌቪዥን አገልግሎት ኃላፊዎች ለእጩዎቹ ባደረጉት የመጨረሻ ዙር ኢንተርቪው ላይ ራሴን ገለጽኩ። በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም ልደት ያገኘሁ ጥብቅ የመጽሐፍ ቅዱስ አማኝ መሆኔን በገሃድ አስታወቅሁ። ያም ሁሉ ሆኖ ግን ለስልጠናው ብቁና ተፈላጊ ሆነው ካለፉት ከጥቂቶቹ አንዷ መሆኔ አስገረመኝ። ይህን ሁሉ መሰናክል አልፎ የተከፈተ በር ነበርና እግዚአብሔር በሕይወቴ ላለው ዓላማ የዘገጀት ጎዳና መሆኑን አመንኩ። ከህዳር 1961 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ዓመት ስልጠናው ትምህርት ቤት ገባሁ።

ቀደም ሲል ወደ ጀመርኩላችሁ.. እኔና ያ ወንድም የትዳር ጓደኛሞች እንድንሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ መስሎን ወደ ተያያዝነው "የእጮኝነት" ጉዞ ልመልሳችሁና በዚያ መልኩ ጥቂት እንደሄድን የእግዚአብሔርን ሃሳብ በተሳሰተ መንገድ መተርጎማችን ውስጣችን እየገባው መጣ። ሃሳቡ የእኛና የሰዎች ብቻ ነበርና ብዙም ሳንቆይ ለትዳር ጓደኛሞችነት እግዚአብሔር እንዳላጣመረን ይታወቀን ጀመር። በሁለታችን ፍቅር ብቻ ልንሠራ ባለምነው የትዳር ሕልማችን ውስጥ እንዲያ የምንወደውን ጌታን አጣነው። እንደ ንጹህ ውኃ እየፈለቀ ለሌሎችም እንኳ ይትረፈረፍ የነበረው በረከት ከውስጣችን ሲደርቅ አየነው። እንደ ወንዝ ይፈስ የነበረው ሰላማችን ይደፈራርስ ጀመር። ለካስ ትዳር በሥስትዮሹ ገመድ በክርስቶስ ካልተገመደ ቀይ የአደጋ ምልክት ያበራል፤ የመጣ ይምጣ ብለን ካልሸመጠጥን! ከሰዎችም ሆነ ከራሳችን ይልቅ የሚበጀንን የሚያውቅልንን የሰማዩ አባታችንን ፈቃድ ጥሰን የገዛ ምኞታችንን ብንከተልም ፍፃሜያችን መራራ እንደሚሆን ተረዳን።

እውነቱ የገባው ልቤ ወደ ታላቅ መተረማመስና ድንጋጤ ውስጥ ገባ! አምላካችን ያልሠራውን ቤት በከንቱ ለመሥራት ከመቃጣት እንድንጠበቅ መንፈስ ቅዱስ ለልባችን ይመክረንና ይናገረን ጀመር። በብዙ ለቅሶ በብዙ ጸሎትና መወያየት፣ የአምላካችን ምርጫ እንደሚበጀን አምንን፣ እርስ በእርስም ተማመንን። በትዳር ለመጣመር የነበረንን የራሳችንን ምኞትና ፍላጎት ከውስጣችን ቆርጦ እንዲጥልልን እግዚአብሔርን ተማፀንነው።

እግሮቻችንን ካጣበቅንበት የሥጋ መንገድ አላቀን ጌታ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀልን ፍጹምና ክቡር ፈቃድ ለመመለስ በጊዜው ቀላል አልነበረም። ሆኖም ግን እኔም ሆንኩኝ እርሱ ጤናማውንና በድል የተሞላውን የክርስትና ሕይወት ለመኖር ከእግዚአብሔር ጋር መስማማቱ የሚበጀን እንደሆነ ጎልቶ ይታየን ጀመር። ስለዚህም በሚቆጠቁጥ የውስጥ ቁስል በብዙም የልብ ስብራት ውስጥ አለፍን። በእኔና በዚያ ወንድሜ መካከል እንዲያ ይፈስ የነበረውን ንጹሕ መለኮታዊ ፍቅርና በረከት የሚያደፈርስ የራሳችን ምኞት አድብቶ መግባቱ እጅግ አሳዘነኝ። ለዚህ ጉስቁልና ምክንያት እኔ ነኝ በማለትም ነፍሴን ድርብ ድርብርብ ወደ ሆነ የኀዘን ሸለቆ ውስጥ ከተትኳት።

ትምህርቴን በሚመለከት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጥሼ ትናንት የተከተልኩት የገዛ መንገዴ ያስከተለብኝ የልብ ስብራት በሻረ ማግስት አልሞት ባዩ ሥጋዬ በሌላኛው ምኞቴ ላይ አሳፍሮኝ እንዲያ ስከንፍ በመገኘቴ ራሴን ጠላሁት። ነፍሴ ወደ ሁለተኛው ጥልቅ የኀዘን ሸለቆ ውስጥ ገባች! እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! . . . ለዚህ ለሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ይለየኛል?" የሚለው ቃል የነፍሴ ሰቆቃ ሆነ! በዚህኛውም የህይወቴ ወቅት፣ ተንኮታኩቼና ስብርብሬ ወጥቶ በሞትና በሕይወት መካከል አሁንም አንድ እርምጃ እንደቀረ መሰለኝ። የአለማስተዋሌና የድካሜ መደጋገም ተስፋ አስቆርጦኝ "የኔ ነገር በቃ አለቀልኝ" አልኩኝ! ሆኖም ግን እንዲያ በሚያሽቆለቁለኝ የኀዘን ደመና ላይ አምላኬ እየተረማመደ ለረድኤቴ ደረሰልኝ። አሁንም እንደገና እጆቹን ከበታቼ ፈጥኖ ዘርግቶ ሲታደገኝ ተመለከትኩ! የውዴ ቃል ሁለንተናዬን ያተረማመሰውን ወጀብና ዓውሎ ነፋስ ሰነጣጥቆ ወደ እኔ ደረሰ! ነፍሴን ማነጋገር የሚችለው አምላኬም እንዲህ እንደሚለኝ ገባኝ፡-

> *"ልጄ ሆይ አይዞሽ! እኔ አልተውሽም አልጥልሽምም! በሕይወትሽ በተደጋጋሚ ከገጠሙሽ ከእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ግን የሚጠቅምሽን... እንደ ንሥር በከፍታዎች ላይ በክንፍ የሚያወጣሽን... ከሚጎዱሽና ከማይጠቅሙሽ ነገሮች በላይ የሚያራምድሽን... በፈቃዴና በቃሌ የመኖርን ታላቅ ምሥጢር እገልጽልሻለሁ። ከዚህ የሕይወት ሸለቆ በምሕረቴ ተሸክሜ ባወጣሁሽ ጊዜ ፍጹምና ክቡር የሆነውን ፈቃዴን ብቻ ለማድረግ የሚያስችልሽን ጸጋዬን እሰጥሻለሁ። ስለዚህም እኔ ባለሁበት በከበረው ሰማያዊ ስፍራ ወዳቀድኩልሽ ክቡር ፈቃዴ እግሮችሽ እንዲፈጥኑ ፈቃዴንና ሃሳቤን የሚጠማ ሕይወት እሰጥሻለሁ። በእናትሽ ማህፀን አንቺን ከመፍጠሬ በፊት ያልተሰሩ አካሎችሽ ገና በእኔ ዘንድ በነበሩ ጊዜ፣ ላንቺ ባወጣሁልሽ ሃሳቤና ዓላማዬ ውስጥ አስገባሻለሁ። በማሕፀን ካኖርኩሽ በኋላ እንኳን በሕይወት እንዳትኖሪ የነፍስሽ ጠላት ዲያብሎስ ምን ያህል ጥረት እንዳደረገ ታሪክሽን አስታውሺ! ውርጃ ሆነሽ እንዳትቀሪ የተከላከልኩልሽና የታደግሁሽ የሕጻንነት አምላክሽ ነኝ! ስለዚህ በሕያዋን ዓለም በምድር እንድትኖሪ ላውጣሁልሽ ዓላማ . . አዎን! . . . ለዚያ የከበረ ሃሳቤ የሚያበቃሽን ጸጋ ከእኔ ዘንድ አሁን ጠይቂ! ከዚህ ሸለቆ በሰቲያ በክንፎቼ ተሸክሜ ሳወጣሽ በፈቃዴና በዓላማዬ ውስጥ የመኖርን ታላቅ የምሥጢር ቁልፍ በእጅሽ አስጨብጥሻለሁ"*

የተሰባበረውን ልቤን ይገዝ መስቀሉ ሥር ሳነባ አምላኬ ፈጥኖ በመድረስ ዋይታዬን ወደ ታላቅ መጽናናት ለወጠልኝ። ለዘመናት ወደ ጠቀመኝ መረዳትና ማስተዋልም ውስጥ አስገባኝ። ቁስሌን ለመፈወስ ስብራቴን ለመጠገን፣ ከወደቅሁበትም ጥልቅ የኀዘን ሸለቆ ውስጥ እኔን ለማውጣት፣

አምላኬ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ውጫዊና ውስጣዊ የሆኑ ታላላቅ ሥራዎችን ይሠራ ጀመር። አዎን፣ ከአንዴም ሁለቴ የገዛ ምኞቴን ተከትዬ የተጓዝኩበት የሥጋ መንገዴ የማልረሳውን መራራ ጽዋ በተደጋጋሚ አስጨልጦኛል። ነገር ግን ለምልክትና ለመታሰቢያ የሆኑ በሕይወቴ የማልረሳቸው ታላላቅ መመሪያዎች ቀርጾ በማለፉ ለጥቅሜ ሆኖልኛል። እንኳንስ ትዳርን ለሚያህል ታላቅ ጉዳይ ቀርቶ ዕለት ዕለት ለሚገጥሙኝ ጉዳዮች ሁሉ የጌታዬን ምሪትና ፈቃድ አበክሮ ማወቅን ልቤ አጥብቆ ይጠማው ጀመር። አምላኬም ወደ እኔ ለሚያመጣቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ለሚሹ ወገኖቼ ሁሉ የሚቃትትን፣ የሚማልድንና አበክሮ የሚመክርም ሕይወት አበዛልኝ። ለሌሎች የሚጠቅምና የሚረባ ነገር ከእንደኔ ዓይነቷም ደካማ መገኘቱ ያጽናናኝ ጀመር።

****

## *"እንደርቢ ! ?"*

የተያያዝኩትን የሕይወት ጉዞ ወላጆቼም ሆኑ ቤተዘመዶቼ ባጠቃላይ አልወደዱትም! ዓለም ልትሰጠኝ ከደገሰችልኝ ክብርና ሥልጣኔ ራሴን በራሴ እንዳገደልኩና እንደተጎዳሁ ቆጠሩት፤ ክርስቶስ ጌታዬ ሞቴን ሞቶልኝ ኃጢአቴን በክቡር ደሙ ደምስሶልኝ ያቀዳጀኝን አዲስ ሕይወት እነርሱም እንዲቀዳጁልኝ የምሥራቹን ይገዬ የሮጥኩት በመጀመሪያ ወደ ወላጆቼና ቤተሰቦቼ ነው፤ በድፍረትና በደስታ የምተርክላቸውን የመዳኔን ታሪክም ሆነ እግዚአብሔር ዛሬም እንደመጽሐፍ ቅዱሱ ዘመን በጸሎት ቤታችን የሚያደርገውን ተአምር ስመሰክርላቸው ሊቀበሉት ተሳናቸው። በእኔ ሕይወት የተካሄደውን ሥር ነቀል ለውጥ ማየት አላቃታቸውም። ችግሩ ግን በዚያን ዘመን እንደ ሰደድ እሳት በወጣቶች መኻል በመዝመት ላይ ስለነበረው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሕብረተሰቡ የተቀበለው የተሳሳተ ኢንፎርሜሽን ነበር።

> *"በመርከብ ተጭኖ የመጣ መጤ ሃይማኖት . . ኢየሱስ ከእኛ ይወለዳል እያሉ በጨለማ ቤት ዝሙት የሚያደርጉ... በሃሰት አጋንንት እናስወጣለን... በሽተኞች እንፈውሳለን እያሉ ሰዎችን በገንዘብ እየገዙ የሚያጭበረብሩ ሃሳውያን... መጥተዋል"* የሚል።

መቼም እኔንና ጓደኞቼን በቅርብና በግልጽ ሕይወታችንን ሲከታተሉት ወላጆቼ እኛ በሃሰት የሚወራብንን ዓይነት ሰዎች አለመሆናችን ገብቷቸዋል። ነገር ግን እንዲያ የሚወዱኝ ልጃቸው ከዚህ መመደቤ፣ ሕዝብ ከጠላቸው አንዷ መሆኔ ደስ አላሰኛቸውም። ስለዚህም፡- ሙያ በልብ ነው እንዲሉ አንቺም እምነትሽን በልብሽ ይዘሽ ሕዝቡን መስለሽ ለምን አትኖሪም? ለምንስ በተከበርንበትና በተወደድንበት ሕብረተሰብ መካከል ታሽማቅቂናለሽ? የቤተሰበቦቼ ጥያቄ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ብዙ ጊዜ ተነጋግረናል። እንዲያውም ይሄው ጉዳይ ተነስቶ እኔም እነርሱም በእንባ ተሞልተን የመጨረሻውንና ቁርጠኛውን አቋሜን የተናገርኩበትን አንድ ምሽት አልረሳውም፤

> *"ምን ያህል እንደምወዳችሁና እንደማከብራችሁ ታውቃላችሁ። በሕይወቴ እግዚአብሔር ያደረገው ለውጥ ግልጽ ነው። ለእናንተ የምጸልየው እኔ የያዝኩትን የዘላለም ሕይወት መንገድ ይዛችሁ እኔ የምለማመደውን ዕረፍትና ሰላም እንድትቀዳጁ ነው። ስለሆነም እናንተ ወደጌታ መንገድ ትመጣላችሁ እንጂ እኔ ወደ ዱሮ ሕይወቴ አልመለስም!"*

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የቤተሰቦቼ ልብ በእኔ ላይ ከብዷል። መስከሬላት የመጀመሪያ ምርኮዬ በመሆን ጌታን መከተል የጀመረቺውን ታናሽ እህቴን ስንዱን፡- "በራስዋ ለመወሰን ዕድሜዋ ስለማይፈቅድላት ያንቺን ዕምነት ተከታይ ልታደርጊያት አትችይም" ሲሉ እሷን ከእኔ ለመለየት የተለያየ ዕቅድ አወጡ። ፈረስ ግልቢያ እንድትማር በእሁድ በቅዳሜው በተለያየ ፕሮግራም እንድትጠመድ ታላቅ ወንድሜ ገብሩ የኔና የሷ ግንኙነት ውሱን እንዲሆን ጥረት አደረገ። እህቴ ስንዱ ግን በበራላት የመዳን ብርሃን ከዓለም ጨለማ አመለጠች። በእግዚአብሔር ቃል ሥር በመስደድ ቆመች። በአንፃሩ ደግሞ የተቀሩት ቤተሰቦቼ የመዳን ጉዳይ የሰማይ ያህል የራቀ ይመስል ጀመር። ስለዚህ ከገሃነም ያመልጡልኝ ዘንድ ጥልቅ ወደሆነ የምልጃና የጸሎት ሕይወት ውስጥ ገባሁ። ከሥራ ሰዓት ውጪ ባለኝ የትርፍ ጊዜ ሁሉ አድራሻዬ ከቻፕላችን "ጸሎት ክፍል" ውስጥ ነበር። ሲመሽ ደግሞ እቤት በመኝታ ክፍሌ ጋቤጣ ላይ በሆዴ ተዘርግቼ ወይንም ተንበርክኬ በአምላኬ የምሕረት ዙፋን ሥር አሳልፋለሁ። ስለቤተ ክርስቲያን ስለመሪዎቻችን በምድራችን ተነፍገን ስለነበረው መንፈሳዊ ነጻነት . . ብቻ መንፈስ ቅዱስ በውስጤ ለመቃተት በሚፈልገው አቅጣጫ ሁሉ በእንባ እጸልያለሁ። ዓይኖቼ አባብጠው የተጋጠሙ እስኪመስሉ። ብዙ ወገኖች ስለእኔ ያላቸውን የድሮ ትዝታ ሲናገሩ በተንበረከኩበት አካባቢ በዕንባ ርሶ ስለሚያዩት ጋቤጣ ይጠቅሳሉ። እናም ስለቤተሰቦቼ ደህንነት ጉዳይ በአምላኬ ፊት ሳነባ ሙሴ በብሉይ፣ ጳውሎስ ደግሞ በአዲስ ኪዳን፣ ሕዝባቸው ድኖ እነርሱ ከሕይወት መዝገብ መፋቅን እስኪያስመርጣቸው ያደረሳቸውን የምልጃ ሕይወት ቅምሻ ያየሁ ይመስለኛል።

ከእነዚህ በአንዱ እሁድ ከሰንበት አገልግሎት በኋላ ቶሎ ብዬ ወደጸሎቱ ክፍል ገብቼ ተንበረከክሁ። ቤተሰቦቼን በእግዚአብሔር ፊት ይገቡ ቀረብኩ እንደልማዴ። እንባዬ ዱብ ዱብ ማለት ጀመረ። አንድ ወንጌልን ለቤተሰቦቼ ለማድረስ ብዙ ጥረትና ጸሎት ያደርግ የነበረ ወንድም ስለነርሱ ያለው ትዝ ብሎኝ ነው።

> *"ሊሽ ያንቺ ቤተሰቦች በጣም ያሾፋሉ እንዲሁ እንዳሾፉ ወደ መቃብር እንዳይወርዱ እሰጋላቸዋለሁ።" ስለዚህ ወደርህራሄ ሁሉ አምላክና አባት ፊት ቀርቤ አንተ ግን የምሕረት ቃል አለህ! የሟቹን ሞት የማትወደው አምላኬ ሆይ እባክህ ጥልቅ በሆነው ይቅርታህና ርህራሔህ ወደ ቤተሰቦቼ ና!"* እያልኩ በጸሎትና በምልጃ ምጥ ውስጥ ገባሁ። ድንገትም የጌታ የእግዚአብሔር ድምጽ እንዲህ ሲል ወደእኔ መጣ።
>
> *"ልጄ ሆይ እንባሺን ላብስ ወዳንቺ መጥቻለሁ። በቅርብ ጊዜ ውስጥ አፋቸውን በእኔ ላይ ያላቀቁት እነዚህ ቤተሰቦችሽ በዚያው እንደበታቸው ያከብሩኛል።"*

ያቺ ሰንበት ስለቤተሰቦቼ የመዳን ተስፋ የሰማሁባት ቀን ሁና ዋለች!! የተከተሉት ሁለት ሦስት ቀናት ግን ከምላኬ የተቀበልኩትን የተስፋ ቃል ሊያደበዝዙብኝ በጽኑ ተፈታተኑኝ።

በዚያው ሳምንት ሐሙስ ሐምሌ 1 ቀን 1963 ዓ.ም. ከጠዋቱ 12 ሰዓት ከእንቅልፌ ተነስቼ ለጸሎት ተንበርክኬያለሁ። የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት የእንግሊዘኛ ዜና አዘጋጅ ሆኜ የምሠራበት ወቅት ነው። ያን ዕለት ተረኛ የዜና አዘጋጅ ሆኜ የተመደብኩበት ቀን ነው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ግን ተነስቼ ወደ ናዝሬት (አሁን አዳማ) በፍጥነት መሄድ እንዳለብኝ ይናገረኝ ጀመር።

"ዛሬ ተረኛ ዜና አዘጋጅ ነኝ። ይህ ሃሳብ ከእግዚአብሔር ነው ከራሴ? ከሆነስ ሥራዬን የሚሠራልኝና ተረኝነታችንን የምንለዋወጠው ፈቃደኛ ሰው አገኛለሁ ወይ? ደግሞስ ለምን ባስቸኳይ ወደናዝሬት?"

ከራሴ ጋር ብዙ ተነጋገርኩ። ልቤንም ደጋግሜ አደመጥኩት፣ ፈተሽኩት... ያለጥርጥር የእግዚአብሔር ድምጽ መሆኑን ልቤ አምኖ ለመታዘዝም ቆርጦ ተነሳ። ሥራዬን የሚሸፍንልኝ ለማግኘት ስልክ አንስቼ የደወልኩለት የመጀመሪያው ሰው ተረኛነታችንን እንድንለዋወጥ ፈቃደኛ ሆነ። ገረመኝ! ጠዋት በማለዳ ቦርሳዬንና መጽሐፍ ቅዱሴን ይዤ ከመኝታ ቤቴ ስወጣ ወንድሜንና ነርስ እህቴን፣ ያጎቴን ልጅ ለቁርስ ሲጠብቁኝ አገኘኋቸው።

" ናዝሬት ለደርሶ መልስ መሄዴ ነው።"

ብዬ ለፌዝና ለትችታቸው ጀርባዬን ሰጥቼ ውልቅ አልኩ። ከቤት እንደወጣሁ በአካባቢዬ ወደሚኖሩት የቅርብ የጸሎት ጓደኞቼ ቤት ስለዚህ ገና ስላልገባኝ ልዩ ጉዞ በጸሎት እንዲደግፉኝ ልነግራቸው ወደየቤታቸው ብሄድ ሁሉንም አጣኋቸው። ይሁን እንጂ "የእግዚአብሔር መንፈስ አዞኝ ወደናዝሬት ለማላውቀው ጉዳይ መሄዴ ነውና ጸልዩልኝ" የሚል ማስታወሻ ጽፌ እየተውኩላቸው ወጥቻለሁ። ናዝሬት ትምህርት ቤት አጠገብ ወደነበረው ቻፕላችን (ሙሉ ወንጌል) ሄድኩ፤ አሁንም ለመጸለይ! በዚያ ያገኘሁት የቤተክርስቲያን አገልጋይ ወንድም አሸናፊ ዘውገም፣ ልቤን ስለሞላው ስለ ናዝሬት ጉዞ እንደገና ጸለየልኝ። ታክሲ ተሳፍሬ የናዝሬቱን ጉዞዬን ለመጀመር ለገሃር ሎንቺና ተራ እንደደረስኩ የሞላ መኪና አጋጠመኝ!

ወላጆቼ ቤት ሠርተው ኑሯቸውን ከጂማ ወደ አዳማ ካደረጉ ሦስት ዓመት ያህል ሆኗቸዋል፤ ለጀመሩት የእርሻ ሥራ ለጤናቸውም ሆነ ልጆች ለማስተማር፣ ለአዲስ አበባ ባላት ቅርበትና የእናቴም አባት አዛዥ እንግዳወርቅ ገብሬ የነበሩባት ከተማ ስለሆነች ወላጆቼ ናዝሬት ለመኖር መርጠዋል።አባቴ ጥሩ ጥሩ የእርሻ ቦታዎች በአድአና በአርሲ አካባቢ ስለነበሩት ውጤታማ የሆነና እርካታም የሚያገኝበት የግል ሥራ ሆኖለታል። የተደላደለ ኑሮ የሚመሩት እነዚህ ወላጆቼ ደሞዝተኞች የነበርነውን እኔንና ወንድሜን ገብሩንም ከእህልና ጥራጥሬ ሸመታ አውጥተውናል። ባለፈው ሳምንት ውስጥ ወላጆቼ አ.አ. ከእኛ ጋር ሰንብተዋል ወንድሜ ገብሩ የኩላሊት ጠጠር ኦፕራሲዮን ማድረግ ስለነበረበት። እናቴ ሕመምተኛው ወንድሜ እስኪያገግም እንድትቆይ ተስማምተው አባቴ እሁድ ወደናዝሬት ተመልሷል። በማግስቱ ሰኞ ዕለት ግን አባቴ ስልክ ደውሎ የሰባት ወር ሕፃን የነበረውን ወንድሜ ብንያምን <<ጉንፋን ይዞት ይነጫነጫልና ብትመጪ ይሻላል>> ሲል እናቴን ጠርቷት ሄዳለች። ታዲያ እኔን ወደናዝሬት እንድሄድ በዚህ ሐሙስ ዕለት የሚያቻኩለኝ ምክንያቱ ምን ይሆን እግዚአብሔር ሆይ ?

ብቻ ወደናዝሬት በሚወስደኝ ሎንቺና ላይ ተሳፍሬ እየጸለየኩና መልስ ያላገኘሁላቸውን ጥያቄዎቼን እያብላላሁ ሳላውቀው ናዝሬት ገብቼ በጋሪ ወደወላጆቼ ቤት ገሠገሥኩ። የግቢውን በር ከፍቼ ስገባ እናቴ ትንሹን ወንድሜን ብንያምን አቅፋ በረንዳ ላይ አገኘኋት። መደነቅ ከሚታይባት እናቴ ጋር እየተሳሳምን፣ "በዛሬው ቀን እንዴት ልትመጪ ቻልሽ?" ስትለኝ ከመልሴ በፊት እኔም በልቤ የሞላው ጥያቄዬን ዘረገፍኩላት። "ደህና ናችሁ? ሁሉ ሰላም ነው? ብንያም ታመመ እንዴ?" አልኳት። እናቴ ግን የሰጠቺኝ መልስ አስገረመኝ።

"እሱ ሙሉ ጤነኛ ነው ልጄ። ግን ምን ሰላም እንዝሆናለን እቤታችን እንደርቢ ተነስቶ? ይኸውና ካለፈው እሁድ ጀምሮ ሰው ሁሉ ጭንቅ ውስጥ ነው!"

"እንደርቢ??"

ስለዚህ ዓይነት የአጋንንት አሠራር አንድ ጊዜ የሰማሁትን ነገር ለማመን ወይንም አጋንንት እንዲህ በገሃድ ይሠራል ብዬ ለመቀበል አቅቶኝ "ሊሆን አይችልም" ብዬ ትቼዋለሁ። ዛሬ ግን ጭንቅ ውስጥ ለገባቺው እናቴ ጆሮዬን መስጠት ስለተገደደኩ ይበልጥ ስለሁኔታው ለመረዳት ነገሩ እንዴት እንደጀመረ ጠየቅኋት።

"የእንደርቢው አሰማት የተሠራባት ሠራተኛችን እቴነሽ ናት። እስከሁን እንዳየነው የሚያጠቃውም እሷኑ ብቻ ነው። በገባችበት ክፍል ሁሉ የቤት ዕቃዎች፣ በግቢያችን የሌሉ የወንዝ ዳር ዓይነት ድንጋዮች ባየር እየተምዘገዘጉ ይወግሯታል። ኩንታል ጤፍ እንኳን እሷን ሊያጠቃ ከተቀመጠበት ይነቃነቃል! የምትበላበትን ሳህን ትላትል ኩስ ምናምን ይጨምርባታል፤ ከእጇ ያስረግፋታል፤ የምትጠጣውን ውኃ ይደፋባታል። አልጋዋ ላይ እንዳትተኛ አልጋዋን ይገለብጥባታል። ቢቸግረን አንድ ክፍል ቤት ባዶ አድርገን እዚያ ብናስቀምጣትም ከየት እንደመጡ የማይታወቁ ድንጋዮች እየተወረወሩ ያስጨንቋታል። ኸረ ስንቱ ልጄ!!"

ጆሮቼ የሚሰሙትን ማመን ተሳናቸው። የምትነግረኝ ግን የገዛ እናቴ ባይኗ በብረቱ ያየቺውን ስለሆነ፣ ልቤ ፍጥነቱን ሲጨመር እየተሰማኝ አቋረጥኳትና፥-

"እማዬ እኔ አሁን ብሄድ ይሄን የምትዪውን ሁሉ ሲያደርግ አያለሁ?"

"ታዲያስ! ሰው ሲከባትማ ትርኢት የሚያሳይ ነው የሚመስለው!"

"በቃ ይሄን ጉድ ማየት አለብኝ ውሰዱኝ ወዳለችበት!"

እናቴንና ለጊዜው እቤት ውስጥ የነበሩትን ታናናሾቼን ተከትዬ በፍጥነት እቴነሽ ወደምትገኝበት ክፍል እንደደረስኩ፣ "እቴነሽ እንዴ ብቅ በይ እስቲ!" በማለት እናቴ ተጣራች። እቴነሽ አንገቷን አቀርቅራ ደጃፉ ላይ እንደቆመች ድንገት የድንጋይ እሩምታ በላይዋ ላይ ተለቀቀባትና ድንጋዮቹ በፊቴ እየተንከባለሉ ወደቁ። አሁንም አፍጥጬ እያየሁ በኃይለኛ ጥፊ ጉንጬቿ ሲመቱ፣ "ወይኔ ዐይኔን ተወጋሁ!" እያለች በድንጋጤ ስትጮኽና ደም የሚመስል ፈሳሽ እንደ እንባ ሲወርድ ተመለከትኩ።

በተፈጥሮዬ ፈሪና ድንጉጥ መሆኔን መላው ቤተሰቤ ያውቃል። እንደ ቀድሞው ማንነቴ ቢሆን ኖሮ <እግሬ አውጪኝ> ብዬ መፈርጠጥ ነበረብኝ! በፊንታው ግን አስደናቂ የሆነ የድፍረትና የእምነት ኃይል ውስጤን ሞላው!

"ራሱ የተቀጠቀጠው ዘንዶ፣ በቀራንዮ መስቀል ላይ የተሸነፈው ዲያቢሎስ ሰይጣን ያን ዓይነት ክፉ አስደንጋጭና ዘግናኝ ትርኢት ማሳየት ከቻለ፣ እሱን ድል ያደረገው፣ መቃብሩን ፈንቅቅሎ ሞትን ድል ነስቶ የተነሳው መድኃኒቴ ክርስቶስ ኢየሱስማ ምን ያህል ተአምር ያደርግ!!" የሚል ጽኑ የሆነ የእምነት ኃይል አደረብኝ።

ወዲያውም መንፈስ ቅዱስ፥- "ጠዋት ጸሎት ላይ ሳለሽ ወደ ናዝሬት በፍጥነት ሂጂ ያልኩሽ ለዚህ ነው" አለኝ።

መጽሐፍ ቅዱሴን ይዤ እቴነሽ ወደ ተሰጣት ክፍል ገባሁ። በዚህ ጊዜ አባቴ ለጉዳይ ከቤት እንደወጣ ገና አልተመለሰም ነበር። እናቴና ሌሎቹም በግቢው የነበሩት ቤተሰቦቼ ግን ያቺን ዲያብሎስ ሽብር ሲፈጥርባትና ሲያስጨንቃት የከረመች ምስኪን እጅበው ገቡ። ጊዜም ሳልፈጅ ወንጌልን ባጭሩ

መሰከርኩላት። ክርስቶስ ጌታን እንደ ግል አዳኟና መድኃኒቷ አምና ወደልቧ ልትጋብዘው ፈቃደኛ ሆነች። የንስሐ ጸሎት አስጸለይኳት።

ምግብና ውኃዋን ከቆሻሻ እየቀላቀለባት አራት ቀን ሙሉ እንደተሰቃየች እናቴ የነገረቺኝ ትዝ አለኝ። እንዲያመጡልኝ የጠየቅኋቸውን ምግብ በተሰበሰቡት ፊት እንድትበላ በክርስቶስ ኢየሱስ ስም ጸልዬ ሰጠኋት። በተራበ አንጀቷ ስታቀላጥፈው የተመለከቱት ሁሉ፣ የሆነ ነገር እንደተካሄደ ገብቷቸዋል። ያለምንም ችግር መብላት መጠጣቷ! ያም ብቻ አልነበረም እነሱ ያስተዋሉት፤ ባለፉት ቀናት እንዳዩት ከሆነ የሰይጣን የዲያብሎስ አተራማሽና አስደንገጭ ትርኢት ተቋርጧል። ስለዚህም በፊታቸው ስለቆምኩት ሰው የነበራቸው አስተሳሰብና የተሳሳተ ግምት እጅግ አሳፍሯቸዋል።

እኔ ደግሞ በዚያች ቅጽበት ትዕቢተኛውና አስቸጋሪው የቤተሰቦቼ ልብ በእግዚአብሔር ፊት ሲቀልጥ አየሁ። የሃሰት እምነት ተከታይ አድርገው እኔን ያዩበት ዐይናቸው ሲያቀረቅር አየሁት፤ መገለሌ ቀርቶ ወደተፈላጊ ሰውነት ተቀየረ። በእኔና በነርሱ መካከል ሰይጣን የገደገደው ግድግዳ ሲፈራርስ፣ የጌታ የእግዚአብሔር ፍርሃት ሲወድቅባቸው መመልከት አስገራሚ ትዕይንት ነበረ።

በመንፈስ ቅዱስ ታዝዤ እንጂ እግር ጥሎኝ በመካከላቸው እንዳልተገኘሁ ከማለዳ ጀምሮ ስለሆነው አስደናቂ የእግዚአብሔር ምሪት መሰከርኩላቸው። እስከዛሬ በንቀትና በማንኳሰስ ያዩት የነበረው የክርስትና ሕይወቴ የከበረውን የጌቶቹን ጌታ እንደተሸከመ ተመለከቱ። ለእነርሱም አስፈላጊ የሆነውን የወንጌሉን እውነት ገለጥኩላቸው። በሄዱበት የዓለምና የኃጢአት መንገድ ቢቀጥሉ ነፍሳቸው የዘላለም ገሃነም እንደሚጠብቃት ግልጽ ሆነላቸው። ስለዚህም ክርስቶስ ጌታን ወደ ልባቸው ለመጋበዝ አብረውኝ ጸሎት ሲያደርጉ በእውነተኛ ንስሐና በእንባ ነበር። የወንጌሉን እውነት ለመስማት የቤተሰቦቼ ጆሮ ዛሬ ተከፈተ። "አሁን ደግሞ እስቲ ምሳ ይቅረብና ትንሽ ዐረፍ በይ" ተብዬ ምሳዬን ገና አንድ ሁለት እንደጎራረስኩ ታናሽ ወንድሞቼ እየተሯሯጡ መጥተው፡-
"እቴነሽ እንደገና ጀመራት ቶሎ ድረሺ!!" አሉ።

ወዲያውኑ ሮጬ ወደእቴነሽ ሄድኩ። ከዚህ የዲያቢሎስ ፍላፃ እሷን ፍጹም ነፃ ሊያወጣት የሚችል ሙሉ ዋጋ ክርስቶስ ጌታ እንደከፈለላት ለማስረዳት ረዘም ያለ ጊዜ አብሬያት ቆየሁ። ከርሷ ጋር ባሳለፍኩት ጊዜ ሁሉ ውስጥ አንድም የሰይጣን ሁከታ አልነበረም። ተመልሼ ወዳቋረጥኩት ምሳና ቡና እንደሄድኩ አሁንም < <የቶሎ ድረሽ! > > ጥሪ መጥቶ ወደእቴነሽ ሮጥኩ። ይሄ ብዙ ጊዜ ሆነ በዚያች በማትረሳ ዕለት። በእቴነሽ ዙሪያ ሰው ባየ ቁጥር ሰይጣን የሚያሳየውን ከፋና አስጨናቂ ትርኢት እኔ ስደርስ ማቆሙና ኃይሉ ሊሠራ አለመቻሉ ለምን ይሆን? እኔን ፈርቶ? በአካልና በቁመናዬ ብታይ በሰው ዐይን እንኳ የማልሞላ አጭርና ቀጭን! የሰው ልጆችን ሰላምና ደህንነት የማይወደው ይህ የጨለማ ኃይል ዲያቢሎስ ማንን ሥጋ ለባሽ ፈርቶ? ከእርሱ በላይ ኃያል ሥልጣን ያለውን የጌቶቹን ጌታና የነገሥታቱን ንጉሥ፣ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በማየቱ እንጂ!! እኔ በማመልከው በዚህ አምላኬ ፊት እንዴት ሊቆም ይችላል?? ሰይጣን ጭካኔውንና ክፋቱን ሁሉ የሚገልጥበት የገሃነም ሥቃይ ጎልቶ የታየኝ ያን ቀን ነው። በአንፃሩም የጌታ ከሕዝቡ ጋር አብሮነት፣ ለተቀበሉት ሁሉ በእርሱም ለሚያምኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይባሉ ዘንድ የሰጠው ኃያል ሥልጣንና ክብር፣ ጭላንጭሉ የታየኝ ያን ዕለት ነበር። እናም አምላኬን ለምጠይቀው ጥያቄ ሁሉ መለኮታዊ መልስ እንደማገኝ ውስጤ በእምነት ተሞልቶ እግዚአብሔርን እንዲህ አልኩት፤

*"እግዚአብሔር ሆይ አባክህ እቴነሽን ስትፈውሳት ምስክር እንዲሆን ለራሱም መዳን እንዲሆንለት አባቷን ወይም እናቷን አምጣልኝ። ደግሞም እግዚአብሔር ሆይ አብሮኝ*

*በእምነት የሚቆም በዚች መግቢያ መውጫያዋን በማላውቀው ከተማ አንድ ሰው ስጠኝ። በከተማዋ ብዙ አማኞች እንዳሉ አውቃለሁ አንዳንዶቹን እንዲያውም በቅርብ የማውቃቸው ወገኖች፣ ግን እግዚአብሔር ሆይ፤ የአንዳቸውን ቤት ወይንም ስልክ እንኳ አላውቅም።"*

በዚያች ልዩ ቀን ሁለቱንም የጸሎት ጥያቄዎቼን በማከታተል ሲመልስልኝ ዓይኜ ተደነቅሁ! የእቴነሽ አባት ከእርሻ ቦታው የወላጆቼን ግቢ ሲገባ በደቂቃዎች ልዩነት የደረሰቹው ከአዲስ አበባ ከመነሳቴ በፊት ጠዋት ወደየቤታቸው ሄጄ ከጣኋቸው ጓደኞቼ መኻል አንዷ እህቴ በቀለች ባቾሬ ነበረች። አመጣጧም ያስገርማል፤ ለካስ ከሁለት ቀን በፊት አሰላ እህቷን ለመጠየቅ ሄዳ ኖሯል። ወደ አዲስ አበባ የምትመለስበትን ሎንቺና ከመያዟ በፊት ግን አንድ ሃሳብ ወደ አእምሮዋ መጣ። *"እግረ መንገዴን ለምን የሊሽን ቤተሰቦች አይቼ አልሄድም"* የሚል።

በዚህ ድንገተኛ ሃሳቧ ላይ ውሳኔ አድርጋ ወደ ወላጆቼ ቤት አቀናች። የእኔን ከአዲስ አበባ መምጣት እንዳች ያላወቀቺውን የጸሎት ጓደኛዬን እንዲህ አድርጎ ሲያመጣት ምን ልበል! የሆነውን ሁሉ ስማቼኝና ወዲያውኑ፣ *"የሌሎች ወገኖች የጸሎት ኃይል ያስፈልጋልና እነሱን ፍለጋ እንውጣ"* አለች። እርሷ በናዝሬት ከተማ ያሉትን የቤተክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ታውቃለች አድራሻቸውንም ጭምር። እሷን በማግኘቴ ብረክም *"ለተጨማሪ እርዳታ ፍለጋ የወገኖችን አድራሻ አመልካች ሰው እግዚአብሔር አንቺን ከሰጠኝ መልክም!"* አልኩና አጋየ ወገኖች ፍለጋ ከበቄ ጋር ተያይዘን ወጣን።

የናዝሬትን ከተማ አገልጋዮች ቤት አድራሻ በነቂስ የምታውቀውን በቄን በስጠኝ እግዚአብሔር እየተገረምኩ፣ በዚያ ምሽት ከቤት እቤት አሉ የተባሉትን አገልጋዮች በር አንኳኳን፤ አንዳቸውም እንኳን በቤት አልተገኙም እንጂ! በውስጤ ጎልቶ ይታየኝ የነበረው ያጠፋነው ጊዜ።በቄ የፀሎቴ መልስ እንደመሆኗ ወዲያውኑ በግቢያችን ወደተጀመረው የእግዚአብሔር ታላቅ ሥራ አገልግሎት መግባት ነበረብን። በቄን ወደ ቤት እንድንመለስ ግድ አልኳት። በመንገድ እያለን ግን፣ በቄ አሁንም አንድ የቀራትን ሃሳብ አመጣች።

*"ቆቃ ግድብ የሚሰሩት ወንድሞቻችን! ለምን ወደ እነሱ እንደውልም ከሦስት አንዳቸውን አናጣም! በአብዛኛ የምሽት ተረኛ የሚሆኑት አንዳቸው ብቻ ስለሚሆኑ። እነሱ ጋ ደውለን ከሆነ ሁለቱን ባይሆን አንዳቸውን እንኳ ብናገኝ በጸሎት ያግዙናል... እንደውልላቸው።"*

በቄ የእነዚህም ወንድሞች ስልክ ቁጥር ነበራት። ወደቤታችን ከመድረሳችን በፊት ከመንገድ ቴሌ ገብተን ስልክ ወደ ቆቃ ደወልን

*"ሃሎ ሃሎ እንዴት ከረማችሁ በቀለች ነኝ . . . ."*

ስልኩን ያነሳው ወንድም የምሽቱ ተረኛ አሰፋ ሰዩም የምንለው ወንድማችን ነበር። እናም በቄ ከመሃከላቸው ለጸሎት እርዳታ አንዳቸው እንኳ እንዲደርሱልን ጥሪ አቀረበችለት። የወንድም አሰፋ መልስ፡-

*"የሚገርምሽ በዚህ ምሽት ያለሁት እኔ ብቻ ነኝ። ወንድም ካሳ እና ታምሬ ወንጂ ሽዋ ሄደዋል፤ እዛ በሚደረገው ኮንፍራንስ ላይ ለመገኘት። እኔ ደግሞ ተረኛ ስለሆንኩ ልደርስላችሁ አልችልም። እንግዲህ እግዚአብሔር ይርዳችሁ"* ብሎ ስልኩን ዘጋ።

እኛም የወገን ጦር ለማሰባሰብ የምናደርገውን አደናችንን ዘግተን በአስቸኳይ ወደ ወላጆቼ ቤት መመለስ እንዳለብን መንፈስ ቅዱስ ተናገረኝ፤ እንዲያውም ከወቀሳ ጋር። የሚሠራው የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ድንቅ አድራጊ ስም እንጂ የእኛ ብዛትና ማነስ አይደለምና። የልቤን ነግሬያት

እግሮቻችን ወደ ቤት ፈጠኑ። በመንፈስ እየቃተትንና እየፀለይን ሳናውቀው ደረስን። ግቢያችንን ከፍተን ስንገባ በቀን ውሎዬ እስካሁን ያላየሁት አባቴም ገብቷል። እኔ ከመድረሴ በፊት እግዚአብሔር አምላክ በቤታችን መሥራት ስለጀመረውም ድንቅ ሥራ የዐይን ምስክር የነበሩት እናቴና ሌሎቹም በአድናቆት የነገሩትንም ሁሉ ሰምቷል።

*"እሷን ተያት"*

እናም እግሮቻችን እቤት እንደረገጡ ከአባቴ ጋር ከተሳሳምን በኋላ በአስቸኳይ ለእቴነሽ ወደ ተዘጋጀላት ክፍል ቤተሰብ በሙሉ ከትንሽ እስከ ትልቅ ወንበሮች እያያዝን እንድንገባ ጥያቄ አቀረብኩ። አባቴ እስካሁን የሆነውን ቢሰማም በልቡ ይቺ ልጅ ይሄን ነገር ባትነካካው ይሻላል ብሎ ተጨንቋል። ይሁን እንጂ ሁኔታዬን እና የልቤን ሙላት ሲያይ ከመከተል እና ያልኩት እንዲሆን ሌሎችን ከማቻኮል ወደ ኋላ አላለም።

በዚያች በእቴነሽ ክፍል ውስጥ ቤተሰብ ሁሉ ተከማቸ። እቴነሽ በእኔና በበቀለች መኻል፣ አባቴም ከጎኔ ሆነው የእግዚአብሔርን ቃል ለመናገር ተነሳሁ። በእለቱ ላልነበሩት ለአባቴና ለቀሩትም እግዚአብሔር ሁሉን የሚችል አምላክ እንደሆነ። ለሰው ልጆች ሁሉ መዳን ይሆን ዘንድ በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ የመጨረሻውን ዓይነት መሥዋዕት ስለኛ መክፈሉን። ይህቺም በአምሳሉ የተፈጠረች ሰው ሙሉ ዋጋ በከፈለላት በእግዚአብሔር ስም ፍጹም ነፃነቷን እንድትቀዳጅ የእግዚአብሔር ፍጹም ሃሳብ መሆኑን ተናገርኩ።

> *"እግዚአብሔር ዛሬ ቀን ላይ የጀመረውን ሥራ በዚህ ምሽት እንቀጥላለን። በቀን ውሏችን የክርስቶስን የስሙን ታላቅነት በማየታችሁ እምነት የሆነላችሁ አሁን ከእኛ ጋር መጸለይ ትችላላችሁ። ብትፈልጉ ዓይናችሁን ከፍታችሁ ወይም ዘግታችሁ። ሌሎቻችሁ ደግሞ ማየት የምትፈልጉ ያልገባችሁ ካላችሁ ነፃነታችሁ የተጠበቀ ይሆናል። እንድታውቁ የምፈልገው የምንጸልየው እቴነሽን ነፃ ሊያወጣ በሚችል ከስሞች ሁሉ በላይ ስም ባለው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው።"*

ወዲያው እኔና በቁ እጆቻችንን በመጫን የጌታን ስም ጠራን። እግዚአብሔርም ስሙን አከበረ! በውስጧ የነበረው የአጋንንት ኃይል በክርስቶስ ኢየሱስ ስም ፊት መቆም አልቻለም። እንዲያ ሰው ሲሰበሰብ ያሳይ ለነበረው አስጨናቂ ትርዒቱ መድረክ አላገኘም። አባቴ ከልጅቷ አቅራቢያ ስለነበረ ዓይኖቹን ገልጦ ሁሉን ይመለከት ነበር። ልጅቷን እንደ እንዝርት አሹሮ በውስጧ ከጮኸ በኋላ እንደሞተ ሰው ተዘረረች። እግዚአብሔርም አለኝ፡- "እሷን ተያት ነፃ አወጣታለሁና! ይህ ሁሉ ያስፈለገው ስለቤተሰቦችሽ መዳን ነው፤ ቃሌን ተናገሪ" ።

እኔም ገብቶኝ የእቴነሽን ነገር እስከጊዜው ትቼ ከተገለጠው የእግዚአብሔር ክብር የተነሳ መሬት ላይ ተደፍተው ለነበሩት ቤተሰቦቼ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጤ እየተቀጣጠለ መናገር ጀመርኩ።

> *"የምወዳችሁ ወላጆቼና ቤተሰቦቼ ሆይ እንግዲህ የማመልከውና ሕይወቴን የለወጠልኝ ይሄንን ታላቅ አምላክ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉትን የሐዋርያትን የነጳውሎስንና የነጴጥሮስን አምላክ እንጂ ሌላ እንዳይደለ በሁላችሁም ዘንድ የታወቀ ይሁን። እንደመሰላችሁና ብዙዎችም በሃሰት እንደሚናገሩትም በመርከብ ተጭኖ የመጣ ሃይማኖት ተከታይ አይደለሁም። ሳይገባችሁ ብትቃወሙኝና ብትዘብቱብኝም*

ከእግዚአብሔር ዞር ማለት ያልቻልኩበት ምክንያት ይህን ዛሬ በፊታችሁ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ክንድ ስላየሁ እንጂ የምወዳችሁን ወላጆቼን ላለማክበርና ላለመታዘዝ እንዳልሆነ ዛሬ ግልጽ ይሁንላችሁ፤" በማለት ስለተገለጠልኝ የወንጌል ብርሃን፣ በእርሱም ስለተቀዳጀሁት ሰላምና ዕረፍት መሰከርኩላቸው።

ከእንዲህ ያለ የሰይጣን ሥራና ከገሃነም እሳት የሰው ልጆችን ለማዳን እግዚአብሔር አምላክ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዘረጋው የሕይወት መንገድ ፈጥነው እንዲገቡ እንዲያመልጡ ስናገር አንዳንዶቹ በጸጸት፡- "ሳናውቅ እግዚአብሔርንና አንቺን በድለናል እና ይቅር በዪን" እያሉ ያለቅሱ ነበር።

እኔም ለራሴ ይቅር የተባልኩ ኃጢያተኛ መሆኔን በእነርሱም ላይ የምይዘው በደል እንደሌለ ገልጬላቸው በይቅርታው ዙፋን ፊት እንዲቀርቡ ወደ እግዚአብሔር መራኋቸው። በዚያች አስደናቂ ሌሊት ወላጆቼን ጭምር አሥራ ሁለት የቤተሰቤ አባሎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ፈለሱ ! ! ከብዙ እንባና ንስሃ ጋር። አምላኬም የአምስት ዓመት እንባዬን እንዲህ አድርጎ አበሰልኝ።

እቴነሽ ግን አሁንም ገና እንደተዘረረች ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ በእያንዳንዶቹ የቤተሰቤ ሕይወት ውስጥ ሌሊቱን የሚሠራውን ሥራ ቀጠለ።

- አንዳንዶች በቤታችን ለዘመናት ያላወቅናቸውን የጨሌ ሙዳያቸውን ከደበቁበት አወጡ።
- አንዳንዶች ስለእኔ በነበራቸው የተሳሳተ ግምት በሰይጣን መተት ይህን በእግዚአብሔር ያለኝን ሕይወት ለማስጣል ሙከራ አድርገው አለመሳካቱን ተናዘዙ።
- አንዳንዶች መድኃኒት ፍለጋ ወደ ጠንቋይ ቤት መሄዳቸውን ገለጹ።
- የዘቀጠ ጥላቻና መራራ ሥር በጌታ መስቀል ሥር ከቤተሰቦቹ ልብ እየተንለገለ ተከሰከሰ።

በዐይኔ ፊት የቤተሰቦቼ ነገር ሲቀየር አየሁ። ውስጣቸው በደሙ ጠርቷልና ያ ሌሊት ሲነጋ በእያንዳንዱ ሰው ገፅታ ላይ የረበበውና እኔም የማየው የንጋት ወጋገን የመሰለ ፀዳል አስደናቂ ነበር።

ጠዋት ላይ ጓደኛዬ በቄ አሁንም መሪዬ በመሆን ወደዚያ ኮንፍራንስ ቦታ ወንጂ ሸዋ የአገልጋዮችን ተጨማሪ እርዳታ ለማግኘት ተጓዝን። ከቤት ከመውጣታችን በፊት ግን በእቴነሽ ውስጥ የሚሠራውን የክፉ ኃይል የትም ይዟት እንዳይሄድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዘዝነው። ወንጂ ሸዋ የመጀመሪያ ክፍለ ጊዜውን ተካፍለን በእረፍቱ ሰዓት በእኔ ቤተሰቦች ውስጥ ስለተጀመረው የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ነግረናቸው ወንድሞቻችንን ጋሼ አሰፋ ዓለሙንና ወንድም ታደሰ ነገዎን ይዘን ተመለስን።

ግቢውን ገና ስንገባ እንደሞተ ሰው የነበረችው እቴነሽ ተነሳች። እፍታም ሳንቆይ ይዘናት ለጸሎት ወደዚያችው ክፍሏ ገባን። ሌሎችም ቤተሰቦች እንዲሁ በአስቸኳይ ተሰባሰቡ። በዚህ መኻል ድንገት አከታዋን እንደምትተፋ መስላ እቴነሽ ወጣ አለችና እንደነፋስ እየበረረች ከግቢው ከነፈች። ለአንዴና ለመጨረሻ ለቋት የመሰናበቻ ሰዓቱ እንደደረሰ ያወቀ ሰይጣን አንድ የመጨረሻ ሙከራውን ለማድረግ አበረራት፤ ከቶስ ማን ይድረስባት ! ? የተገኘችው በአንድ እሩቅ ስፍራ ጉሮሮዋን በጣቶቿ አንቃ እራሷን ልትገል በሞትና በሕይወት መካከል ሆና ነበር። አሥር ደቂቃ ባልሞላ ጸሎት በጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ኃያልና ድንቅ ስም መዳን ለእቴነሽ ሆነ። ታላቅ ሐሴትና ደስታ ለቀናት ሲታመስ በነበረው ቤታችን ወረደ። በእነዚያ አስደናቂ ሰሞናት አባቴ ለአጋጠሙት ሰዎች ሁሉ፡-

"እግዚአብሔር እኮ እቤታችን ድረስ መጣ" እያለ ይመሰክር ነበር።

በወቅቱ በቤተሰባችን በተገለጠው የእግዚአብሔር ክንድ ምክንያት ወደ መንግስቱ የፈለሱ እስከዛሬ በቤቱ ፀንተው ቆመዋል። ወላጆቼ በጌታ ሆነው ወደዘላለም መኖሪያቸው ተሻግረዋል። በተለይ እናቴ ከ36 ዓመት በላይ ታላቅ የጸሎት ሰው ነበረች። አቶ ኃይሉ እንግዳወርቅ የተባለው (የእናቴ ታናሽ ወንድም) በአሰላ የታወቀ የቀድሞው ጠንቋይ ነጋነቱን ከተቀዳጀ ወዲያ የሰይጣንን መንግሥት በማፈራረስ የታወቀ ወንጌላዊ ሆኖ አገልግሎ ተሻግሯል። በዕለቱ ከዳኑት መኻል አክስቴ ወ/ሮ ሙሉ ወርቅ ካሣ በአጋሮ ከተማ ቤተክርስቲያን ከመትከል እንስቶ ዛሬም በቤቱ የተወደደች እናት የጸሎት ሰውም ናት። ከእነዚህም መሀል የሁለተኛው ትውልድ ሙሉ አገልጋዮች ወጥተዋል!! የቀሩት በሰደትና በፈተና ሁሉ አልፈው በአመኑበት ጌታ ጸንተው ወደ ዘላለም እረፍታቸው ተሻግረዋል። ሃሌሉያ!! ክብር ሁሉ ለገናናውና ለዘላለማዊው እግዚአብሔር ይሁን!!

****